# መሠረተ ሕይወት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የልጆች መማሪያ መጽሐፍ

## አሥረኛ ክፍል

አዘጋጅ - ቀሲስ ሰሎሞን መሉጌታ

www.zeorthodox.org

ሰኔ

፲፱፻፺ ዓ.ም.

© ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ ፳፻፮ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት፣ ሥርዓት እና ትውፊት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት

አድራሽ፦
ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ
ፖ.ሳ.ቁ 43200
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Email:- kesisolomon@gmail.com
Website:- www.zeorthodox.org


www.zeorthodox.org

የኮምፒውተር ሌይ አውት ዲዛይን
ልደት አስፋው

# ምስጋና

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ በቀጥተኛ ተሳታፊነት የተሰለፉትን ዲ. ዘላለም ረድኤትና ዲ. ዮናታን ኢያሱን፣ መጽሐፉን በማረም የተባበሩትን መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብርን፣ መምህር ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔርን፣ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን፣ እና አቶ አስራት ከበደን እንዲሁም በኮምፒዩተር የለቀማ ሥራ ያገለገሉትን ልደት አስፋውን፤ መጻሕፍቱን ለማጠናቀቅ ሳደርግ በነበረው ጥረት ውድ ባለቤቴና ልጆቼ የእንቅልፍና የእረፍት ሰዓታቸውን ሳይቀር መሥዋዕት በማድረግ ስላሳለፉ ስለ ከፈሉት መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ዋጋ ከፋይ ነውና ዋጋቸውን ይክፈላቸው እላለሁ፡፡ በመጨረሻም የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚያከናውኑ የመርሐ ግብራችን አስተባባሪ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሰንበቴ የሥራ አስፈጻሚ አባላትን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቅልኝ ሳልል አላልፍም፡፡

# መታሰቢያነቱ



ዘወትር ጸሎታቸው ላልተለየችኝ በግብጻውያን ክርስቲያኖች ዘንድ አርአያነታቸው ለሚታወስ ለአባ ገብረ ሕይወት ምሕረት (አቡነ ሐያት) ይሁንልኝ፡፡

# ማሳሰቢያ

www.zeorthodox.org

ይህ መጽሐፍ ተሰራጭቶ የሚገኘው ገቢ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም፣ በቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣ በቦሌ ሰሚት መካነ ሰላም መድኃኔዓለም እና ወደ ፊትም በተለያዩ አጥቢያዎች ለሚከናወኑ የሕፃናት፣ አዳጊዎች፣ ወጣቶችና ወላጆች ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትና ተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውል ይሆናል፡፡

# ማውጫ


| ተ.ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| | መቅድም | I | | | |
| | መግቢያ | III | | | |
| 1. | ቅዱስ ቄርሎስ | 1 | | አንደኛ | |
| 2. | የኢያሱ ሕይወት | 3 | | ሁለተኛ | |
| 3. | ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምባቸው መጻሕፍት | 5 | | ሦስተኛ | |
| 4. | የሐዋርያት ሥራ ጥናት ፩ | 7 | | አራተኛ | |
| 5. | የሐዋርያት ሥራ ጥናት ፪ | 10 | | አምስተኛ | |
| 6. | ጠንካራ ሰብእና | 12 | | ስድስተኛ | |
| 7. | የሰማዕታት ድል | 14 | | ሰባተኛ | |
| 8. | ኃጢአትና መዘዙ | 16 | | ስምንተኛ | |
| 9. | መጽሐፍ ቅዱስ | 18 | | ዘጠነኛ | |
| 10 | መጽሐፈ ኢዮብ ፩ | 21 | | ዐሥረኛ | |
| 11. | መጽሐፈ ኢዮብ ፪ | 23 | | ዐሥራ አንደኛ | |
| 12. | የመታዘዝ ሕይወት | 25 | | ዐሥራ ሁለተኛ | |
| 13. | ንጹሕ አምልኮ | 27 | | ዐሥራ ሦስተኛ | |
| 14. | ትምህርተ አበው | 29 | | ዐሥራ አራተኛ | |
| 15. | የእግዚአብሔር መገለጥ | 31 | | ዐሥራ አምስተኛ | |
| 16. | ስሜታችንን እንዴት መግዛት እንችላለን? | 34 | | ዐሥራ ስድስተኛ | |
| 17. | የቅድስና አገልግሎት | 36 | | ዐሥራ ሰባተኛ | |
| 18. | የከበረ ደም | 38 | | ዐሥራ ስምንተኛ | |
| 19. | ንስሐ መግባት | 40 | | ዐሥራ ዘጠነኛ | |
| 20. | ደገ ሳምራዊ | 42 | | ሃያኛ | |
| 21. | ጥምቀት | 44 | | ሃያ አንደኛ | |
| 22. | የትንሣኤ በዓል | 47 | | ሃያ ሁለተኛ | |
| 23. | ዕርገትና በዓለ ሃምሳ | 49 | | ሃያ ሦስተኛ | |
| 24. | መጀመሪያው የጢሞቴዎስ መልእክት | 51 | | ሃያ አራተኛ | |
| 25. | ሁለተኛው የጢሞቴዎስ መልእክት | 53 | | ሃያ አምስተኛ | |
| 26. | የድንግል ማርያም ሕይወት | 55 | | ሃያ ስድስተኛ | |
| 27. | ቅዱስ ጴጥሮስ በሰማዕትነት ሞተ | 57 | | ሃያ ሰባተኛ | |


www.zeorthodox.org

| ተ.ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| 28. | ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን | 59 | | ሃያ ስምንተኛ | |
| 29. | ከክፉ ነገር መሸሽ | 61 | | ሃያ ዘጠነኛ | |
| 30. | መጽሐፈ ምሳሌ | 63 | | ሠላሳኛ | |
| 31. | ሕመምተኛ ሰውን ቅብዓ ቀንዲል መቀባት | 65 | | ሠላሳ አንደኛ | |
| 32. | አቡነ ተክለ ሃይማኖት | 67 | | ሠላሳ ሁለተኛ | |
| 33. | ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ | 69 | | ሠላሳ ሦስተኛ | |
| 34. | በክረምት የዕረፍት ጊዜዬን እንዴት ልጠቀምበት እችላለሁ? | 71 | | ሠላሳ አራተኛ | |
| 35. | የመንፈሳዊ ሕይወት ማነቆዎች | 73 | | ሠላሳ አምስተኛ | |
| 36. | መንፈሳዊ ቅንዓትና ትጋት | 75 | | ሠላሳ ስድስተኛ | |
| 37. | የብዙኃን መገናኛ ተፅዕኖ | 77 | | ሠላሳ ሰባተኛ | |
| 38. | በጎ ሥራ | 79 | | ሠላሳ ስምንተኛ | |
| 39. | በጎ ሕሊና | 81 | | ሠላሳ ዘጠነኛ | |
| 40. | ቃልን ማክበር | 83 | | ዐርባኛ | |
| 41. | ገንዘብና ክርስቲያናዊ ሕይወት | 85 | | ዐርባ አንደኛ | |
| 42. | የሥጋ ፍላጎቶችን ማወቅና ማሸነፍ | 88 | | ዐርባ ሁለተኛ | |
| 43. | ሕግን ማክበር | 90 | | ዐርባ ሦስተኛ | |
| 44. | የእምነት ኃይል | 92 | | ዐርባ አራተኛ | |
| 45. | ቅዱስ ጊዮርጊስ | 95 | | ዐርባ አምስተኛ | |
| 46. | ሱሰኝነት | 98 | | ዐርባ ስድስተኛ | |
| 47. | ወጣቶችና ፈተናዎቻቸው | 100 | | ዐርባ ሰባተኛ | |
| 48. | ወጣትነትን መገንዘብ | 102 | | ዐርባ ስምንተኛ | |
| 49. | ሴቶች በሐዲስ ኪዳን | 104 | | ዐርባ ዘጠነኛ | |
| 50. | ሴቶች በብሉይ ኪዳን | 107 | | ሃምሳኛ | |


www.zeorthodox.org

# መቅድም

በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች ቤተ ክርስቲያናቸውን እያወቁ በመልካም ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚያደርግ፣ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ብሎም ችግሮቻቸውን የሚፈታ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት የመኖሩ አስፈላጊነት በብዙዎቻችን ዘንድ ይታመንበታል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ዙሪያ በርካታ ተግባራትን እንደምታከናውን እምነቴ ነው፡፡

ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመላክ ለተስተካከለ ዕድገታቸው አስተዋጽዖ በማድረግ የወላጅነት ሓላፊነታቸውን ለመወጣት ፍላጐቱ አላቸው፡፡ ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣም ይሁን በሌላ ምክንያት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እንዲማሩላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ ምእመናን እጅግ ጥቂቶች መሆናቸውን የተለያዩ አጋጣሚዎች ማሳያዎች ሆነውኛል፡፡

ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ በምሥራብት መሥሪያ ቤት በኩል ለተዘጋጀ ሙያዊ ሥልጠና ከአገር ውጪ ባደረግሁት ጉዞ ዘወትር አብረውኝ የሚቆሙ ቤተሰቦቼ ምክንያት ሆነው ግብጽንና ገዳማቱን የመጐብኘት ዕድል አገኘሁ፡፡ ይህም የተቀደሰ አጋጣሚ ስለ ልጆች፣ በቅድመ ጋብቻ ስላሉ ወጣቶችና በትዳር ስለሚኖሩ ኦርቶዶክሳዊያን የተናጠል መርሐ ግብር እንዳስብ አደረገኝ፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃድም በኅዳር ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቀ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን የልጆች መርሐ ግብር በሃያ አራት ልጆች ተጀመረ፡፡ አሁን ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሆኑ ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ልጆች፤ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ቀን ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ይከታተላሉ፡፡ በርካታ ምእመናንም በየሳምንቱ ረቡዕ ከምሽቱ አሥራ ሁለት እስከ ሁለት ሰዓት ለአዋቂዎች በተዘጋጀው የትምህርት መርሐ ግብር ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ ሁሉንም ልጆች በየትምህርት ደረጃቸው በመመደብ ማስተማር የሚያስችል መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነበር፡፡ በመሆኑም ቀድመው የተዘጋጁትን ትምህርቶች ተካተውበት ለዚሁ ሥራ እገዛ የሚያደርጉ ወንድሞች ጋር በመመካከር ዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ዲያቆን ዘላለም ረድኤት ተገኝተውበት ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ መጻሕፍትን ለማዘጋጀት ጥረት ተጀመረ፡፡ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ከአራት ዓመታት ጥረት በኋላ፤ ለሥርዓተ ትምህርቱ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ በኋላ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ የሆኑ አሥራ ሦስት ጥራዝ የማስተማርያ መጻሕፍት ዝግጅት ተጠናቅቆ ለኅትመት

www.zeorthodox.org

እንዲበቁ ለማድረግ ወደ ማተሚያ ቤት ገብተዋል፡፡

በማስተማርያ መጻሕፍቱ ዝግጅት፤ ለመረጃ የምንገለገልባቸው ምንጮች፣ የምእመናን የኑሮና የትምህርት ደረጃ፣ የመኖሪያ ሥፍራዎችና የባህል ልዩነቶች፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ እና ከሀገር ዉጪ በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መካከል ያሉ የአኗኗርና የሥራ ሁኔታዎችና አካባቢያዊ ልዩነቶችን ታሳቢ በማድረግ ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገቡ ተሞክሮአል፡፡ በዚህ ሥራ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላደረጉት ለዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ለዲያቆን ዘላለም ረድኤት፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን እላለሁ፡፡

ይኸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ላሉ ወጣቶች ለሚሰጠዉ ‹‹መሠረተ ሕይወት›› መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት ለንትመት በቅተዉ ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሆናቸውን በታላቅ ደስታ እገልጻለሁ፡፡

***"እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል፡፡" ፩ኛ ሳሙኤል ፯ ፥ ፲፪***

www.zeorthodox.org

# መግቢያ

የዚህ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ትውፊተ ቤተክርስቲያን ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት ጥርት ያለውን የቅድስት ቤተ ክርስቲንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ታሪክ ከመልካም ሥነ ምግባር ጋር፤ በዓለማዊ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች እንዲደርስ ለማድረግ፤ በየትምህርት ደረጃቸው እና ዕድሜአቸው እንዲመጥን ሆኖ የሥርዓተ ትምህርት አዘገጃጀትን ስልት በመከተል ለማዘጋጀት ተሞክሮአል፡፡ አንዳንዶቹ ትምህርቶች ልጆች ትምህርቱን በሚገባ ተረድተዉ ማስታወስ እንዲችሉ በየደረጃዉ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በድጋሚ ተካትተዋል፡፡

ትምህርቶቹ በየወሩ ተከፋፍለው በቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላትም ጋር እየተቀራረቡ እንዲዘጋጁ ጥረት ተደርጎአል፡፡ በየመካከሉ ለሚኖሩ ክፍተቶች በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቅደም ተከተል አገልግሎት ላይ እንዲውል ሆኖ የማሟያ ትምህርቶቹ ተወስደው ተካትተዋል፡፡ ያም ሆኖ እንደየ ጊዜው ሁኔታ ዘመኑን እንዲዋጅ መሻሻልና መዳበር ያለበት መሆኑ ግን የማይዘነጋ ነው፡፡

በሙዓለ ሕፃናት የሚገኙ ልጆች በጣም አጫጭር ታሪኮችን ብቻ ሰምተው ጥቂቶቹን ብቻ ማስታወስ የሚችሉ ናቸው፡፡ ረጅም ጽሑፍና ሐሳብ በትኩረት አንብበዉ በቀላሉ ለመረዳትም ሆነ ለማስታወስ ስለማይችሉ ወይም ስለሚቸገሩ በመምህራን እንዲሁም በወላጆች መታገዝ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በተረት፣ በታሪክ፣ በሕልምና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት አገናዝቦ ለመረዳት ይቸገራሉ፡፡ በጣም ፈጠራ የታከለባቸው የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የሚያስፈልጓቸው ቢሆኑም መምህራ ኖቻቸው የሚዘምሩላቸዉን መዝሙሮች ማስታወስና በአእምሮአቸው መያዝ፣ በትምህርታዊ ጨዋታዎቻቸውም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ መምሰልና ማስመሰል ይችላሉ፡፡ በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች የሚንቀሳቀሱና የተለያዩ ድምፆች ያሉባቸውን ነገሮች እንዲሁም ከሌሎች ጋር መጫወትንና ያዩትን በተግባር ማሳየትን ይወዳሉ፡፡

ልጆች ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸው ደስታን እንዲፈጥርላቸውና ፈጽመውም የሚወደዱ መሆናቸውን እንዲሰማቸው ማድረግ እንጂ ቶሎ ሊያስደነግጣቸው ወደ ሚችል አቀራረብና ቅጣት ማዘንበል አይገባም፡፡ በየደረጃው የሚገኙ ልጆችን የሚያስተምሩ መምህራን በተፈጥሮ ለልጆች ፍቅር ያላቸውና ፍቅራቸውንም መግለጽ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል፡፡ በዚህ ትምህርት የሚጠበቁ መልካም ውጤቶችም በሚቀርቡላቸው መርጃዎችና በመምህራኑ ጥረት ላይ የተመረኮዙ ናቸው፡፡ መምህራኑ ልጆችን ለመሳብ ብሩህ ፈገግታና ፍቅር ያለው አቀራረብ እንዲሁም፤ ደመቅ ያሉ ቀለማትን፣

www.zeorthodox.org

ድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ቢጠቀሙ መዝሙራትንም ቢያዘምሩላቸው ለትምህርቱ ታላቅ ኃይል ይሆናል። ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር መምህራን ልጆቹን በየዕለቱ የትምህርት መርሐ ግብሮች መዝሙራትን ሊዘምሩላቸውና ሊያስጠኑአቸው ያስፈልጋል። አንዳንድ ጊዜም ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሥዕላትን ቢያሳዩአቸዉ፣ ቢሰጡአቸው የተማሩትን ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስና ለሌሎችም ለማስረዳት የበለጠ ዕድል ይፈጥርላቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ልጆች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉና። ይህንኑ ለማገዝም በቀለም የሚቀቡ ሥዕሎችና የመዝሙር ጥራዞችን ዝግጅት አጠናቀናል። በሙዓለ ሕፃናት ደረጃ የሚገኙ ልጆች ከትምህርታቸዉ ጋር ተያያዥነት ያለውን ርእሰ ጉዳይ ሥዕሉን ቀለም በመቀባት የሚቀስሙት ትምህርት የበለጠ ስለሚሆን የተዘጋጁትን ሥዕሎች በአግባቡ ቀለም እንዲቀቡአቸው የወላጆች እገዛ እጅግ አስፈላጊ ነው።

በዓመቱ ውስጥ ባልተካተቱት ሁለት ሳምንታትም ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን መጎብኘታቸውና ክትትል ባለበት ሁኔታ በማኅበራዊ ነገሮች ተሳታፊ መሆናቸውም እጅግ ጠቃሚ ነው። ከሁሉም በላይ ግን መምህራን ለዚህ አገልግሎት በትጋት መጸለይና በየመካከሉ የሚቀሩ ወይም ጨርሰው ያልመጡ ልጆችንም መጎብኘት ይጠበቅባቸዋል። መምህራንን ማግኘት በማይቻልባቸው ሥፍራዎች ወላጆች በሥርዓተ ትምህርቱ በመመራት ልጆችን ማስተማር ይችላሉ። ልጆች በመንፈሳዊው ትምህርት እስከአሁን ድረስ ያደጉበት ሁኔታ ያልተመጣጠነ ስለሆነ የክፍል ደረጃቸው ከፍ ቢልም ከሙዓለ ሕፃናት መጽሐፍ ደረጃ ጀምረው መማራቸው ለመንፈሳዊዉ ዕዉቀታቸዉ መሠረት ስለሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በዚህ አጋጣሚም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶችም ይህንን ሥርዓተ ትምህርት መጠቀማቸው ልጆች በየደረጃው ቤተ ክርስቲያናችንን እያወቁ፣ ሃይማኖታቸውን ተረድተውና በበጐ ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

በመጨረሻም ይኽን ዝግጅት የበለጠ ለማሻሻል የሁሉም አስተያየትና ምክር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እገዛችሁ እንዳይለየኝ እያልኩ አስቀድሞ በተጠቀሱት አድራሻዎች አስተያየቶቻችሁን እንድትልኩልኝ ስል በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ።

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ቄርሎስ

**የትምህርቱ ዓላማ:-** በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የቅዱስ ቄርሎስን አስተዋጽኦ ወጣቶች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ:-** "መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፤ ሩጫዬን ጨርሻአለሁ፤ ሃይማኖቴን ጠብቄአለሁ፡፡" **፪ጢሞ.** ፬÷፯

**ተጨማሪ ምንባብ:-** ዕብ. ፲፩÷፴፮-፴፰ እና (ሃይማኖተ አበው ዘቅዱስ ቄርሎስ)

## መግቢያ

- ስለ ቅዱስ ቄርሎስ የምታውቁት ምንድን ነው?
- በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የቅዱስ ቄርሎስ ሚና ምንድን ነበር?
- ከቅዱስ ቄርሎስ ትምህርቶች የምታስታውሱትን ግለጹ?

## የሳምንቱ ትምህርት

ቅዱስ ቄርሎስ በ፫፻፸፮/376/ ዓ.ም ተወለደ፡፡ የምንኩስና ሕይወትን የጀመረው በግብጽ ምዕራባዊ ክፍለ ግዛት በረሐ ውስጥ በሚገኙ ገዳማት ነው፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ በሕይወቱ የተመሰከረለት ታላቅ መምህር ነበር፡፡ በ፬፻፲፪/412/ **ዓ.ም የታላቋ እስክንድርያ ሃያ አራተኛ** ፓትርያርክ ሆነ፡፡

የቁስጥንጥኒያው ጳጳስ ንስጥሮስ የኑፋቄ ትምህርት ማስተማር ሲጀምር ቅዱስ ቄርሎስ ተቃወመው፡፡ ንስጥሮስ "ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ ነው፡፡ ማርያም ወላዲተ አምላክ አትባልም፡፡" በማለት አስተማረ፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ ሁለት መቶ ኤጲስ ቆጶሳትን ሰብስቦ አስወገዘው፡፡ ይህ ጉባኤ ጉባኤ ኤፌሶን ይባላል፤ በ፬፻፴፩/431/ **ዓ.ም በቅዱስ ቄርሎስ ሰብሳቢነት የተደረገ ነው፡፡**

ቅዱስ ቄርሎስ "ክርስቶስ አንድ ባሕርይ ነው፡፡ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ (ቴዎቶኮስ) ናት፡፡" በማለት እውነትን መሠከረ፡፡ "ክርስቶስ ከእውነተኛ ብርሃን የተገኘ ብርሃን ነው፡፡ ድንግል ማርያም የእውነተኛው ብርሃን እናት (እሙብርሃን) ናት፡፡" እያለ ያስተምር ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ቄርሎስ "ማኅተመ አበው"፤ "የቤተክርስቲያን ጠበቃ" እና "ዳግማዊ አትናቴዎስ" እየተባለ ይጠራል፡፡

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የጎላ ሚና አለው፡፡ መጻሕፍትን በመጻፍ፣ መናፍቃንን በትምህርቱ በመርታት፣ ወንጌልን በመስበክ፣ አማኞችን በማጽናናት፣ የቤተክርስቲያንን ሁለንተናዊ ጥቅም፣ ትምህርትና ልዕልና በማስጠበቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## የቅዱስ ቄርሎስ የጽሑፍ ሥራዎች

፩. የመጽሐፍ ቅዱስን አንድምታ ትርጓሜ (ኮመንተሪ) ሠርቷል፡፡ አንድምታዎቹ የሙሴ መጻሕፍት፣ ትንቢተ ኢሳይያስ፣ የዐሥራ ሁለቱ ደቂቀ ነቢያት የትንቢት መጻሕፍት፣ መዝሙረ ዳዊት፣ መጽሐፈ ምሳሌ፣ መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን፣ ትንቢተ ዳንኤል፣ ትንቢተ ሕዝቅኤል፣ ትንቢተ ኤርምያስ፣ የዮሐንስ ወንጌል፣ የሮሜ መልእክት፣ የዕብራውያን መልእክትና ሁለተኛ የቆሮንቶስ መልእክት ናቸው፡፡

፪. የበዓል መልእክታትን ጽፏል፡፡ ከ፬፻፲፬-፬፻፵፪/414-442/ዓ.ም ሃያ ዘጠኝ የበዓል መልእክታት ለአማኞች ጽፏል፡፡

፫. በጽሑፍ ስብከቶችን አዘጋጅቶ ለምእመናን ልኳል፡፡ ሃያ ሁለት ጥልቅ የሆኑ ሃይማኖታዊ ስብከቶቹ በመጽሐፍ ታትመው ይገኛሉ፡፡

፬. ስለ ነገረ መለኮት፣ ነገረ ክርስቶስ፣ ነገረ ማርያምና ክርስቲያናዊ ኑሮን በሚመለከት ብዙ መጻሕፍትን ጽፏል፡፡

፭. በቤተክርስቲያናችን አገልግሎት ከሚሰጡት የቅዳሴ መጻሕፍት መካከል የቅዱስ ቄርሎስ የቅዳሴ መጽሐፍ አንዱ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ቅዱስ ቄርሎስ የቤተክርስቲያንን ትምህርት በመናፍቃን ክፉ ዘር እንዳይበከል የጠበቀ፣ በሃይማኖታዊ ትምህርቱ የተመሰከረለት ታላቅ አባት ነው፡፡ የሃይማኖት ቅንዓትን፣ በዓላማ መጽናትን፣ ለእውነት መቆምንና በቅድስና መትጋትን ከቅዱስ ቄርሎስ ሕይወት እንማራለን፡፡

## ተግባር

መምህሩ የቅዱስ ቄርሎስን ትምህርቶችወጣቶች ከሃይማኖተ አበው መጽሐፍ አጥንተው ለጓደኞቻቸው እንዲያካፍሉ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# የኢያሱ ሕይወት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በእግዚአብሔር ጽኑ እምነት ያለው በሕይወቱ ስኬትን በተሰለፈበት ሁሉ ድልን እንደሚቀዳጅ ለወጣቶች ማሳወቅ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "በምትሄድበት ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደቀኝም ወደግራም አትበል፡፡" ኢያሱ ፩÷፯

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** መጽሐፈ ኢያሱ ፩-፳፬

## መግቢያ

እስራኤላውያን ከግብጽ ከወጡ በኃላ ለአርባ ዓመታት በምድረ በዳ ተጓዙ፡፡ ወራሾቹ የበረሐውን ጉዞ ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ዮርዳኖስ ቀረቡ፡፡ ዮርዳኖስን በእምነት ተሻገሩ፡፡ የኢያሪኮን ቅጥር በእምነት ጣሉ፡፡ በኢያሱ የተመሩት ባለተስፋዎች እግዚአብሔር ቃል የገባላቸውን ወረሱ ኢያሱም በየነገዱ ርስትን አከፋፈለ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ኢያሱ በግብጽ የተወለደ እስራኤላዊ ነው፡፡ ሕዘበ እስራኤል ከግብጽ ወደ ምድረ ርስት ባደረጉት ጉዞ የሙሴ ዋና ረዳት ነበር፡፡ ከሙሴ ሞት በኋላ የእስራኤል አዲሱ መሪ ሆኖ ሕዝቡን መርቷል፡፡ ኢያሱ ከአማሌቃውያን ጋር በተደረገው ጦርነት የጦር አበጋዝ ነበር፡፡ ዘጸ.፲፯÷፰-፲፬፡፡ ኢያሱ ከዐሥራ ሁለቱ ሰላዮች መካከል አንዱ ሲሆን መልካም ወሬ ለሕዝቡ አመጣ፡፡ ዘዳ.፲፫÷፲፬፡፡

ኢያሱ በሙሴ ምትክ ሲሾም እግዚአብሔር "በሕይወትህ ምንም አይቋቋምህም ከሙሴ ጋር እንደ ነበርኩ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፡፡ አልጥልህም፣ አልተውህም፡፡" በማለት እንደማይለየው ገለጠለት፡፡ ኢያሱ ፩÷፭፡፡ ኢያሱ በብዙ ዓመታት የሥራ ልምዱ ያካበተው የአስተዳደር ችሎታና በጦርነት የአመራር ጥበብ ነበረው፡፡ ወደ ምድረ ርስት ለገቡት እስራኤላውያን ርስት ያከፋፈለው እርሱ ነው፡፡ ይህንን ታላቅ ተግባር ያከናወነው በብርታት፣ በእምነት፣ በታዛዥነትና በታማኝነት ነበር፡፡ ለሕዝቡ ርስት ሲያከፋፍል ስለመሸ ፀሐይን በገባኦን አቁሟል፡፡ ኢያ.፲÷፲፪፡፡ ኢያሱ በጽኑ እምነት ጠላትን የተቋቋመ ወገኖቹን በጥበብ የመራ መልካም መሪ ነበር፡፡ በኢያሱ ዘመን ሕዝቡ እግዚአብሔርን ተከተለ፡፡ ኢያሱ እርም የሆነውን እንዳይነኩ ሕዝቡን ያስጠነቀቀ፣ የነካውን አካንን የቀጣ፣ የባዕድ አምልኮን ፍቅር ከትውልዱ ፊት ያራቀ፤ እግዚአብሔርን በማምለክ አርአያነት ያለው መስፍን ነበረ፡፡

www.zeorthodox.org

በሕይወቱ ፍጻሜ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ያለውን ታማኝነት እንዲጠብቅ አስጠንቅቋል፡፡ ኢያ ፳፬÷፲፬፡፡ "እኔና ቤቴ እግዚአብሔርን እናመልካለን፡፡" በማለት ራሱን አርአያ አድርጎ ሕዝቡ ከአምልኮተ እግዚአብሔር እንዳይወጡ አስተምሯል፡፡ ሕዝበ

እስራኤልም "እግዚአብሔርን እናመልካለን፡፡ ድምፁንም እንሰማለን" በማለት ቃል ኪዳናቸውን አጽንተዋል፡፡

ኢያሱ የመታዘዝ፣ የእምነት፣ የጽንዓት፣ የመልካም መሪነትና የትጋት አርአያችን ነው፡፡ ኢያሱ ለእግዚአብሔር የሚያደላ ለወገኑ የቆመ ሰው ነበር፡፡ ኢያሱ ከሙሴ ሕይወት የተማረ ዕውቀቱን ልምዱንና አርአያነቱን የወረሰ የሕግ ጽሑፎችን የተቀበለና ራእዩን የፈጸመ መሪ ነው፡፡

ኢያሱ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ኢያሱ የዮርዳኖስን ባሕር እንደከፈለ ኢየሱስ የሞትን ባሕር ከፍሏል፡፡ ኢያሱ ሕዝቡን ወደ ርስቱ እንዳስገባ ኢየሱስም ከጨለማ ግዞት ነጻ አውጥቶ የዘላለም ርስትን አውርሶናል፡፡ ኢያሱ ሕዝቡን በሕይወቱም እንዳስተማረ ኢየሱስም የሕይወት መምህር ነው፤ በቃሉ ሐሰት በኑሮው እብለት በሥራው ክፋት የለበትምና፡፡

## ማጠቃለያ

ኢያሱ ጠንካራ መሪ፣ እውነተኛ ምስክር ትጉህ አማኝ፣ ጥበበኛ መስፍንና ታዛዥ አገልጋይ ነበረ፡፡ ኢያሱ ከሙሴ ቀጥሎ ሕዝበ እስራኤልን መርቷል፡፡ ለሕዝበ እስራኤል ርስት ያከፋፈለም እርሱ ነው፡፡ ኢያሱ ሕዝበ እስራኤል በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንተው እንዲድኑ አድርጓል፡፡

## ተግባር

መምህሩ ከኢያሱ ሕይወት ምን እንደተማሩ ወጣቶቹን ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምባቸው መጻሕፍት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ መጻሕፍት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "መጻሕፍትን ካላመናችሁ ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ?" ዮሐ.፭÷፵፯

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፪ጢሞ.፫÷፲፭-፲፯

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጥንታዊት፣ ሐዋርያዊትና ዓለም አቀፋዊት ነች፡፡ የራሷ የሆነ ቋንቋ፣ ፊደል፣ ዘመን መቁጠሪያ፣ ትውፊት፣ ሥርዓት፣ ዜማ፣ የዜማ መሣሪያና መጻሕፍት አሏት፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በትውልዱ ልብ ሃይማኖትን በሀገሪቱ ታሪክና ቅርስን ጉልህ አሻራን አትማለች፡፡ የትውልዱ የማንነት መገለጫና የኢትዮጵያ መልክ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ናት፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቤተክርስቲያን የምትጠቀምባቸው መጻሕፍት በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም መጽሐፍ ቅዱስና አዋልድ መጻሕፍት ይባላሉ፡፡ አዋልድ መጻሕፍት የዜማ፣ የቅዳሴ፣ የትርጓሜ፣ የታሪክ፣ የተአምራት፣ የስብከት፣ የገድል፣ የነገረ ሃይማኖትና የሥርዓት ወዘተ መጻሕፍት ናቸው፡፡

የቤተክርስቲያን መጻሕፍት በቀኖና ቤተክርስቲያን የተለኩ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፡፡ ለትውልዱ ትምህርትና ተግሣጽ ይሆኑ ዘንድ በቅዱሳን አባቶች የተጻፉ እውነተኛ ትምህርቶች በመጻሕፍት ይገኛሉ፡፡ ቤተክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮዋን የምትመራው በቅዱሳት መጻሕፍት ነው፡፡ የመምህራን የትምህርት ምንጭ ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው፡፡

***የነገረ ሃይማኖት መጻሕፍት፡-*** የቤተክርስቲያን መሠረታዊ ትምህርቶች የሚገኙባቸው መጻሕፍትን ያጠቃልላሉ፡፡ ሃይማኖተ አበውና ሌሎች የሊቃውንት መጻሕፍት በዚህ ክፍል ይጠቃለላሉ፡፡

www.zeorthodox.org

***የቅዳሴ መጻሕፍት፡- ለምሳሌ፡-*** ቅዳሴ እግዚእ፣ ቅዳሴ ማርያም፣ ቅዳሴ ሐዋርያት፣ ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ፣ ቅዳሴ ሠለስቱ ምዕት፣ ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ፣ ቅዳሴ ዮሐንስ፣ ወልደ ነጎድጓድና ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ይጠቀሳሉ፡፡

***የዜማ መጻሕፍት፡-*** የሰዓታትና የማኅሌት ሥርዓት የሚከናወንባቸው የዜማ መጻሕፍት ይባላሉ፡፡ ከእነዚህም የቅዱስ ያሬድ አምስቱ የዜማ መጻሕፍትና የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ መጽሐፍ ሰዓታት ይጠቀሳሉ፡፡

***የትርጓሜ መጻሕፍት፡-*** በተለያዩ ዘመናት ሊቃውንት የተረጎሙአቸው መጻሕፍት ናቸው፡፡ **ለምሳሌ፡-** የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

ድርሳን ይጠቀሳል፡፡

***የሥርዓት መጻሕፍት፦*** የቤተክርስቲያን ሥርዓት የተገለጸባቸው መጻሕፍት ናቸው፡፡ መጻሕፍተ መነኮሳት፣ ሥርዓተ ጽዮን፣ አብጥሊስ፣ ዲድስቅልያ፣ ትእዛዝና ግጽው ሲኖድ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

***የተአምራት መጻሕፍት፦*** የኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራት፣ የድንግል ማርያም ተአምራት፣ የመላእክትን ድርሳናትና የቅዱሳን ሰዎችን ገድላት የያዙ መጻሕፍት ናቸው፡፡ ድርሳን፣ ገድል፣ ተአምረ ኢየሱስና ተአምረ ማርያም በዚህ ክፍል ይጠቃለላሉ፡፡

***የታሪክ መጻሕፍት፦*** ቤተ ክርስቲያን ያሳለፈቻቸውን ጉዞ የመዘገቡ የቤተክርስቲያን ታሪክ መጻሕፍት በዚህ ክፍል ይጠቃለላሉ፡፡

***የስብከት መጻሕፍት፦*** በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች አባቶች ያስተማሯቸው ትምህርቶች በዚህ ክፍል ይታወቃሉ፡፡ **ለምሳሌ፦** የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስብከቶች ይጠቀሳሉ፡፡

## ማጠቃለያ

የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ እውነት የገለጡ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸውና ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር የማይጣረሱ ትምህርቶችን የያዙ መጻሕፍትን ቤተክርስቲያን ትጠቀማለች፡፡

## ተግባር

*መምህሩ ወጣቶች የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትን ከአባቶች በመጠየቅ ዝርዝር እንዲያወጡ ያድርግ፡፡*

www.zeorthodox.org

# የሐዋርያት ሥራ ጥናት ፩

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የጥንቷን ቤተክርስቲያን አገልግሎትና ጥንካሬ ወጣቶች እንዲያውቁ ማድረግ

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቆረሱ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፡፡" ሐዋ.፩÷፵፮

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** የሐዋርያት ሥራ ፩-፲

## መግቢያ

የሐዋርያት ሥራ የሐዲስ ኪዳን ብቸኛው የታሪክ ክፍል ነው፡፡ የሐዋርያት ሥራ የመጀመሪያዎቹን አማኞች ኑሮ፣ የደቀ መዛሙርቱን የአገልግሎት ውሎና የክርስትና ጉዞ አጀማመር የምናነብበት ሕያው የታሪክ ሰሌዳ ነው፡፡ የሐዋርያት ሥራ ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ በኋላ የትንሣኤው ምስክሮች የሠሩትን ሥራ ይገልጻል፡፡ የሐዋርያት ሥራ ክርስትና የሮምን ድንበር እንደተሻገረ፣ የምስክሮቹ ድምፅ አድማሳትን እየተሻገረ መላው ዓለምን በማዳረስ የመንግሥቱ ወንጌል እንደተሰበከ ይተርካል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ሐዋርያ ማለት መልእክት የያዘ መንገደኛ ማለት ነው፡፡ ሐዋርያት የንጉሡን የክርስቶስን መልእክት የያዙ፤ ለመልእክቱ የታመኑና የተላኩ የጽዮን መንገደኞች ናቸው፡፡ የሐዋርያት አገልግሎት በከፊል በሐዋርያት ሥራ ተመዝግቧል፡፡ የሐዋርያት ሥራ የደቀ መዛሙርቱን ተግባር፣ የፈጸሙትንም ተልዕኮ ይተነትናል፡፡ የሐዋርያት ሥራ የክርስቶስን የሰንበት ቃል፣ በክብር ማረጉን፣ የመላእክትን ምስክርነት፣ የመንፈስ ቅዱስን መውረድ፣ የደቀ መዛሙርቱን በምልክትና በተአምራት የታጀበ በተጋድሎ የተዋበ አገልግሎት መዝግቧል፡፡ የሐዋርያት ሥራ የክርስቶስን ደቀ መዛሙርት ፍሬ አዝሏል፡፡ የሐዋርያት ሥራ የክርስቶስ ወንጌል የዘላለም ምክሩና የማዳኑ ቃል ብዙዎችን እንደማረከና አድማሳትን እንዳካለለ ይመሰክራል፡፡ በወንጌል ክርስቶስን በሐዋርያት ሥራ ተከታዮቹን (ክርስቲያኖችን) እናገኛለን፡፡ ወንጌል የክርስቶስን ሥራ ይነግረናል፤ የሐዋርያት ሥራ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ይገልጽልናል፡፡ የሐዋርያት ሥራ "የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል" ይባላል፡፡

www.zeorthodox.org

የሐዋርያት ሥራ የጥንቷን ቤተክርስቲያን የተጋድሎ ውበትና የማይናወፅ ጽናት ያሳየናል፡፡ የክርስትና አሻራ የታተመባቸውን ከተሞች ያስጎበኙናል፡፡ የሐዋርያት ሥራ የሐዋርያት ዜና መዋዕል ነው፡፡

**፩. የመጽሐፉ ጸሐፊ፡-** የመጽሐፉ ይዘትና ብዙ ማስረጃዎች እንደሚያትቱት ጸሐፊው ባለመድኃኒቱ /የሕክምና ባለሞያው/ ሉቃስ ነው፡፡ ይህ የታሪክ መጽሐፍ የሉቃስ ሁለተኛ መጽሐፍ ነው፡፡ የሉቃስን ጸሐፊነት የጥንቷ ቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ መስክሯል፡፡

**፪. ተደራሲ፡-** የመጽሐፉ ተደራሲ ቴዎፍሎስ የሚባል ሰው ነው፡፡ ሐዋ.፩÷፩፡፡

**፫. የተፃፈበት ዘመን፡-** በ፸/70/ ዓ.ም እንደተጻፈ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡

***፬. የመጽሐፉ ዓላማ፡-*** ከምሥራቹ ልደት ጀምሮ ቅዱስ ጳውሎስ የዓለም ፖለቲካና የባህል ማእከል ወደሆነችው ሮም አደባባይ እስከደረሰበት ጊዜ ድረስ ያለውን የክርስትና ታሪክ ማቅረብ ነው፡፡ ክርስትና በብዙ መከራ ቢከበብም ጉዞውን በድል አድራጊነት እንደመራ መግለጽ ዋና ዓላማው ነበር፡፡ በክርስትናው ጉዞ የተከናወኑ ዓበይት ድርጊቶችን ለተተኪው ትውልድ ማሳወቅ ዓላማው ነው፡፡

***፭. የጽሑፉ ባሕርይ፡-*** በየጊዜውና ቦታው ሁኔታ የተፈጸመው ታሪክ ሥነ-ጽሑፋዊ ውበቱን ድርጊታዊ እውነቱን ሳይለቅ በትክክል የቀረበ ቅደም ተከተላዊ ትረካን ይከተላል፡፡

**፮. የመጽሐፉ አከፋፈል**

***ምዕራፍ ፩***- የክርስቶስ ዕርገት፣ የሐዋርያት ጸሎትና የማትያስ መመረጥ

***ምዕራፍ ፪*** - የመንፈስ ቅዱስ መውረድ፣ የቅዱስ ጴጥሮስ ስብከትና የአማኞች መጠመቅ

***ምዕራፍ ፫*** - የሺባው መፈወስና የሐዋርያት ጽኑ ቃል

***ምዕራፍ ፬*** - የአማኞች ኅብረት፣ የሐዋርያት የእምነት ጥንካሬና በጕዦዎች ፊት መቅረብ

***ምዕራፍ ፭*** - የሐዋርያት መታሰርና መገረፍ

***ምዕራፍ ፮*** - የዲያቆናት ምርጫና የእስጢፋኖስ መያዝ

***ምዕራፍ ፯*** - የእስጢፋኖስ ስብከትና ሰማዕትነት

***ምዕራፍ ፰*** - የአማኞች መበተን፣ የፊልጶስ አገልግሎትና የጃንደረባው ጥምቀት

***ምዕራፍ ፱*** - የጳውሎስ ወደ ክርስትና መምጣትና የጴጥሮስ አገልግሎት

***ምዕራፍ ፲*** - ቅዱስ ጴጥሮስና ቆርኔሌዎስ

***ምዕራፍ ፲፩*** - ክርስትና በአንጾኪያ

***ምዕራፍ ፲፪*** - የያዕቆብ ሰማዕትነት፣ የጴጥሮስ መያዝ፣ የመልአኩ እርዳታና የሄሮድስ ሞት

***ምዕራፍ ፲፫*** - ፳፰ የጳውሎስ አገልግሎት በተለያዩ አገሮች

***፮.፩. የመጽሐፉ መልእክት፡-*** የሐዋርያት ሥራ ሦስት ዋና ዋና የክርስትና ቁልፍ መልእክቶችን ይዟል፡፡ እነርሱም፡- ኅብረት፣ ምስክርነትና ሰማዕትነት ናቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች ለእኛም ያስፈልጉናል፡፡

www.zeorthodox.org

***፮.፪. ኅብረት፡-*** ክርስትና ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር ኅብረት የምናደርግበት የፍቅር አደባባይ ነው፡፡ ክርስትና እግዚአብሔርን የምናከብርበትና ሰዎችን የምንወድበት ሕይወት ነው፡፡ አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር በአምልኮ ኅብረት ያደርጋል፤ ከሰዎች ጋር በፍቅር አንድ ሆኖ ይኖራል፡፡ በሐዋርያት ሥራ አማኞች ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የነበራቸውን የጸና የመንፈስ ኅብረትና እርስ በርሳቸው የነበራቸውን አንድነት ይገልጻል፡፡ "በአንድ ልብ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ድምፃቸውን ከፍ አደረጉ፡፡" "ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፣ ያላቸውን ሁሉ በአንድነት አደረጉ፣ በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ ተጉ" በማለት በሰላም ማሰሪያ

የተጠበቀውን አንድነታቸውን ይገልጻል፡፡ በሰላም ማሰሪያ ኅብረታችንን መጠበቅ፣ ዘመኑ ሲቀርብ እያየን አብልጠን በአንድነት መሆንን ገንዘብ ማድረግ አለብን፡፡ ዕብ. ፲÷፳፬፡፡

***፮.፫. ምስክርነት፡-*** ምስክርነት የመፈጠራችን ዓላማና የማመናችን ማስረጃ ነው፡፡ በቃል በኑሮ፣ በዜማ በሆነ ምስጋናና በነገር ሁሉ መመስከር አለብን፡፡ የተለያየ ዓይነት ሕዝብ ያደረገን በጎነቱን ለዓለም እንድንመሰክር ነው፡፡ **፩ጴጥ.** ፪÷፱፡፡ **የሐ**ዋርያት ሥራ ክርስቶስ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን የዓይን ምስክሮቹ እንደሆኑ ማረጋገጡን፣ የሐዋርያትን ምስክርነትና የጳውሎስን ስብከት መዝግቧል፡፡ በልቡ ያመነ በአፉ ሊመሰክር ይገባዋል፡፡

***፮.፬. ሰማዕትነት፡-*** ሰማዕት ማለት ምስክር ማለት ነው፡፡ ሰማዕትነት ምስክርነትን በደም ማተም ማለት ነው፡፡ የክርስትና ተጋድሎ የተጠበቀ ነው፡፡ የትንሣኤው ምስክሮች ለምሥራቹ ቃል ሕይወታቸውን እንደከፈሉ፣ ለማዳኑ ዜና ደማቸውን እንዳፈሰሱ የሐዋርያት ሥራ ይተነትናል፡፡ እስጢፋኖስና ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ ሰማዕትነትን እንደጀመሩ ይነግረናል፡፡ ክርስቲያን ስለ እምነቱ ሊመሰክር በእምነት ጸንቶ ሊኖርና እስከ መጨረሻው ሊዘልቅ ይገባዋል፡፡ ክርስትና የሮምን ድንበር የተሻገረው በምስክሮቹ ደም ነው፡፡

## ማጠቃለያ

የሐዋርያት ሥራ የክርስቶስ የማዳን ዜና፣ የትንሣኤው ወንጌልና የምስክሩ ቃል በብዙ መከራ ቢከበብም በድል መሻገሩንና የትንሣኤው ምስክሮች የከፈሉትን መሥዋዕትነት ይተርካል፡፡ ከክርስቶስ ዕርገት ጀምሮ ያለውን የክርስትና ጉዞ ለዓለም ያስነብባል፡፡ የሐዋርያት ሥራ በክርስቶስ ያመኑ በኅብረት ሊኖሩ ያመኑበትን ሊመሰክሩና ለእውነት በደስታ መሥዋዕት ሊሆኑ እንደሚገባ ያትታል፡፡ የሐዋርያት ሥራ የሐዋርያት ዜና መዋዕልና የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ነው፡፡

## ተግባር

መምህሩ ወጣቶች የሐዋርያትን ሥራ ከምዕራፍ ፩-፲ ያለውን አጥንተው በአጭሩ እንዲተርኩና የተማሩትን እንዲያካፍሉ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# የሐዋርያት ሥራ ጥናት ፩

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ክርስትና እንዴት እንደተስፋፋ እንዲያውቁ ማድረግ

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "ደቀመዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ፡፡" ሐዋ.፲፩፥፳፮

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ሐዋ.፲፩-፳፰

## መግቢያ

የሐዋርያት ሥራ የክርስትና የመጀመሪያ ታሪክ የተጻፈበት መጽሐፍ ሲሆን፡፡ ሐዋርያት ከክርስቶስ የተማሩትን በተግባር የገለጹበትን ሐዋርያዊ ጉዞ የሚያስረዳ ነው፡፡ የሐዋርያት ሥራ መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ አድሮ ያፈራውን ፍሬ ይዟል፡፡ የሐዋርያት ሥራ የክርስቶስ የማዳን ዜና ከኢየሩሳሌምና ከሮም አልፎ ምድርን እንደሸፈነ ይገልጻል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

የሐዋርያት ሥራ ስለ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ አገልግሎት፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ ርዳታ፣ ስለ ሰዎች ከጨለማ ግዛት መውጣት፣ ስለ ቤተክርስቲያን እድገት፣ በአማኞች መካከል ስለ ነበረው ኅብረት፣ በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ስለ ነበረው ግጭት፣ የክርስትናን ስደትና መከራ፣ የአይሁድና የሮማውያን ዛቻና የምስክሮቹን መሥዋዕትነት ይተርካል፡፡

- የሐዋርያት ሥራ የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች ስለ ቅዱስ ጴጥሮስ ምስክርነትና የፈውስ አገልግሎት ሲናገሩ የመጨረሻዎቹ ምዕራፎች ደግሞ ስለ ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞዎች ይመሰክራሉ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ሦስት ሐዋርያዊ ጉዞዎችን አድርጓል፡፡ በክርስቶስ የተለወጠ ሕይወቱ፣ ጠንካራ አገልግሎቱና ወደ ተለያዩ አህጉራት ያደረጋቸው ሐዋርያዊ ጉዞዎቹ በሐዋርያት ሥራ ተመዝግበዋል፡፡
- የጳውሎስ መመለስ፤ ሐዋ.፱
- የጳውሎስ የመጀመሪያ ሐዋርያዊ ጉዞ ሐዋ.፲፫ - ፲፬
- የጳውሎስ ሁለተኛ ሐዋርያዊ ጉዞ ሐዋ. ፲፭÷፴፮ - ፲፰÷፳፪
- የጳውሎስ ሦስተኛ ሐዋርያዊ ጉዞ ሐዋ. ፲፰÷፳፫ - ፳፩÷፲፮ ተመዝግቧል፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያው ሐዋርያዊ ጉዞው በቆጵሮስ፣ በጲስድያ፣ በሊቃኦንያ፣ በታናሽ እስያ፣ በአንፆኪያና በልስጥራን ሰብኳል፡፡ በሁለተኛው ሐዋርያዊ ጉዞው በሶርያ፣ በኪልቅያ፣ በፊልጵስዩስ፣ በተሰሎንቄ፣ በቂሳርያ፣ በቤርያና በመቄዶንያ

አስተምሯል፡፡ በሦስተኛው ሐዋርያዊ ጉዞው ደግሞ በገላትያ፣ በፍርግያ፣ በኤፌሶን፣ በቆሮንቶስና በኢየሩሳሌም ሰብኳል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን የጻፈውና ብዙ አማኞችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ያመጣው በእነዚህ ጉዞዎቹ ነው፡፡

ከቅዱስ ጳውሎስ፤ ከልብ መመለስን፣ በዓላማ ጸንቶ እስከ ሞት ድረስ መዝለቅን ለእግዚአብሔር እውነት መቅናትን፣ የአገልግሎት ጥበብን፣ የተለወጠ ሕይወትንና የአገልግሎት ብርታትን እንማራለን፡፡

## ማጠቃለያ

የሐዋርያት ሥራ በአራቱ ወንጌሎችና በመልእክቶቻቸው መካከል የሚገኝ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መገናኛ ድልድይ በመሆን ስለ ቤተ ክርስቲያን መመሥረት፣ መስፋፋትና ማደግ ይገልጣል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የጀመረው አገልግሎትና የማስተማር ተግባር በብዙ ተአምራት ታጅቦ በሐዋርያት መቀጠሉን ያሳያል፡፡ የሐዋርያት ሥራ ለቅዱስ ጳውሎስ አገልግሎት ሰፊ ስፍራ ሰጥቷል፡፡

## ተግባር

መምህሩ "የሐዋርያት ሥራ አስፈላጊነት" በሚል ርእስ ወጣቶች አጭር ጥናታዊ ጽሑፍ እንዲያዘጋጁ ያድርግ፡፡ በተጨማሪም የሐዋርያት ሥራ ፲፩-፳፰ ያለውን በግላቸው እንዲያጠኑ ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ጠንካራ ሰብእና

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች በነገር ሁሉ ጠንካራ ሰብእናን እንዲጎናጸፉ ማስገንዘብ

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "መንፈሳዊ ሰው ሁሉን ይመረምራል፤ ራሱ ግን በማንም አይመረመርም" ፩ቆሮ.፪÷፲፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃስ ፪÷፶፪፣ ፪ጴጥ.፩÷፭-፰፣ ገላ.፪÷፳ እና ምሳ.፳፬÷፭

## መግቢያ

- ሰብእና ምንድን ነው?
- ጠናካራ ሰብእናን እንዴት ማዳበር ይቻላል?
- የጠንካራ ሰብእና መገለጫዎች ምንድን ናቸው?
- የጠንካራ ሰብእና አብነቶች እነማን ናቸው?

## የሳምንቱ ትምህርት

### ፩. ሰው ምንድን ነው?

ሰው በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረ ክቡር ፍጡር ነው፡፡ ሰው ፈጣሪውን የሚመስል ብቸኛ ፍጡር ነው፡፡ ሰው ሥጋና ነፍስ ሲሆን፤ የሚናገርና የሚያስብ ነጻ አእምሮ ያለው ፍጡር ነው፡፡ የፍጥረታት ሁሉ ዘውድ ነው፡፡ እግዚአብሔር በፈጠረው ፍጥረታት ላይ የሾመው ባለሥልጣን (ገዥ) ነው፡፡ እርሱ ደግሞ የገዥዎች ሁሉ ገዥ ለሆነው ለእግዚአብሔር ይገዛል፡፡ መዝ. ፪÷፲፩፡፡

ሰው ነጻነት፣ ነጻ ፍቃድ፣ አሳቢ አእምሮና ሐሳቡን መግለጫ አንደበት አለው፡፡ አምላኩን የሚመስለው በነፍስ ባሕሪው ነው፡፡ ሰው ኑሮውን በአምላኩ ፍቃድ የሚመራ መሆን አለበት፡፡

### ፪. ጠንካራ ሰብእና፡-

www.zeorthodox.org

ሰው በሥጋም በነፍስም ሙሉ ሲሆን፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱና በሥጋዊ ኑሮው በጥበብ ሲመላለስ እንዲሁም በመንፈስ ፍሬዎች ያጌጠ ማንነት ሲኖረው ጠንካራ ሰብእና አለው ይባላል፡፡ የጠንካራ ሰብእና መገለጫዎች ትዕግሥት፣ ይቅር ባይነት፣ ልበ ሰፊነት፣ ጽንዓት፣ ራስን መግዛትና የዋህነት ናቸው፡፡ ሰው ዕውቀቱን፣ ጉልበቱንና ጊዜውን በአግባቡ መጠቀም ሲችል፤ በጎነትን ሲያበዛ፤ በክፉዎች ላይ የመልካምነት ተፅዕኖ ሲያደርግ፤ ጠንካራ ሰብእናን አዳብሯል እንላለን፡፡

### ፫. ሰው ጠንካራ ሰብእናን እንዴት ያዳብራል?

ሰው በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ጠንካራ ለመሆን ሙሉ ሰው ወደ መሆን ማደግ አለበት፡፡ በሥጋዊ ሕይወቱ ሥጋዊ ዕውቀት መጨመር፣ ማኅበራዊ ሕይወትን በጥበብ መምራት፣ በጥንቃቄና በማስተዋል መጓዝ፣ በልባምነትና በየዋህነት መመላለስ ጊዜና ኃይሉን በአግባቡ መጠቀም አለበት፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወቱ በክርስቶስ ማመን፤ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት ማድረግ፣ በመንፈስ ፍሬዎች ማንነቱን ማስጌጥ፣ ከክብር ወደ ክብር መሻገር አለበት፡፡ ለሌሎች ያለውን ፍቅር ማሳደግ በመልካም ሥራው መግለጽ አለበት፡፡ ጠላታችንን እስከ መውደድ ፍቅራችን ሊያድግ ይገባል፡፡ ሥጋዊ ፍላጎቶችን ድል መንሣት፣ በትሕትና ዝቅ ብሎ ማገልገል፣ ችግሮችን መቋቋም፣ ልበ ሰፊ (ብልህ)ና የዋህ መሆን፣ ዕውቀትን መጨመርና የመልካምነት ተፅዕኖ መፍጠር የመንፈሳዊ ሰው ጠንካራ ሰብእና መገለጫዎች ናቸው፡፡ ጠንካራ ሰብእናን ለማዳበር ጥበብን መፈለግ፣ ዕውቀትን መጨመር፣ በጽድቅ ፍሬ ለማደግ መበርታትና የእግዚአብሔርን ፈቃድና ርዳታ በጸሎት በመጠየቅ በእምነት ወደ ሙሉነት መገስገስ ያስፈልጋል፡፡

ጠንካራ ሰብእና የሚለካው ምቹ ባልሆነ ጊዜ ባለን ማንነት ነው፡፡ ችግር ሲያጋጥማችሁ ምን ታደርጋላችሁ? ሰው ክፉ ሲናገራችሁ ምን ታስባላችሁ? ለራሳችሁ ያላችሁ አመለካከት ምንድን ነው? ራሳችሁን በሚገባ ተቀብላችኋል? ሌሎችን ዝቅ ብሎ ማገልገል ያስደስታችኋል? የተቸገሩትን ለመረዳት ያላችሁ ቁርጠኛነትና ቀና መንፈስ ምን ያህል ነው? ሥጋዊ ፍላጎት ሲሰማችሁ ስሜታችሁን፣ ፍላጎታችሁን በመቆጣጠር በትክክለኛው መንገድ በተረጋጋ መንፈስ ለመዝለቅ ትወስናላችሁ? ... በእነዚህ ጥያቄዎች ራሳችሁን በመመዘን ጠንካራነታችሁን ፈትኑ፡፡

## ማጠቃለያ

ጠንካራ ሰብእና በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት የምንቆምበት ሞገስ ነው፡፡ ጠንካራ ሰብእና የመከራን ሌሊት በጥበብ እና በትዕግሥት በማለፍ የምናነጋበት ጉልበት ነው፡፡ ጠንካራ ሰብእና በሥጋዊም በመንፈሳዊም ሕይወት ሙሉ ወደ መሆን መምጣት ነው፡፡ ሰይጣንን በጸሎት፤ ጠላትን በፍቅር የምናንበረክክበት ኃይል ነው፡፡ ጠንካራ ሰብእና የመንፈሳዊ ሰው መገለጫ ነው፡፡

## ተግባር

መምህሩ ወጣቶቹን ጠንካራ ሰብእናን እንዴት ማዳበር እንደሚቻል ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የሰማዕታት ድል

**የትምህርቱ ዓላማ:-** ወጣቶች ሰማዕታትን አብነት በማድረግ የድል አድራጊነትን ሕይወት እንዲጎናፀፉ መምከር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ:-** "ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፡፡" ራእ.፲፪፥፲፩

**ተጨማሪ ምንባባት:-** ራእይ ፯፥፱-፲፭፣ ዕብ.፲፫፥፲፫ እና ፊልጵ ፫፥፯

## መግቢያ

ሰማዕት ማለት ምስክር ማለት ነው፡፡ የክርስቶስ የቃል፣ የሕይወትና የተግባር ምስክሮች ሰማዕታት ይባላሉ፡፡ "ሰማዕታት የዚህን ዓለም ጣዕም ናቁ፤ ስለ መንግሥተ ሰማያት መራራ ሞትን ታገሡ፤ ደማቸውን ስለ ክርስቶስ ፍቅር አፈሰሱ፡፡" ቅዱስ ኤፍሬም

## የሳምንቱ ትምህርት:-

ሰማዕታት ራሳቸውን በመካድ ነቀፌታውን (መስቀሉን) ተሸክመው ክርስቶስን ተከተሉ፡፡ የዚህን ዓለም ክብርና ጥቅም ስለክርስቶስ እንደ ጉዳት ቆጠሩ፡፡ ሰማዕታት የትንሣኤውን ኃይል በማወቅ በሞቱ የመሰሉት አገልጋዮቹ ናቸው፡፡ እስከሞት በመታመን የሕይወትን አክሊል የተቀበሉ እውነተኛ የተግባር ምስክሮች ናቸው፡፡ ሰማዕታት ክርስቶስ በአባቱ ፊት እንደሚመሰክርላቸው አምነው በሰው ፊት መሰከሩለት፡፡ ሉቃ. ፲፪፥፰፣ ራእ. ፫፥፯፡፡ ሰማዕታት የሥጋ ፍላጎትንና የዓይን አምሮትን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ድል አድርገዋል፡፡ የዓለም መከራንና የአላውያን ነገሥታትን ዛቻ በእምነት አሸንፈዋል፡፡ ዲያብሎስን በምስክሩ ቃልና በበጉ ደም ድል ነሥተውታል፡፡ ራእይ ፲፪፥፲፩፡፡

ሰማዕታት ታላቁን መከራ በጽናት ሰንጥቀው ያለፉት፣ የሞትን ባሕር የተሻገሩትና የወንድሞችን ከሳሽ ዲያብሎስን የጣሉት በበጉ ደም ነው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በራእዩ "የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ፤ ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከስሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና፡፡ እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፣ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም" በማለት የታላቁን ዘንዶ ሽንፈት የወንድሞቻችን የሰማዕታትን ድል ገልጿል፡፡ ራእ ፲፪፥፲-፲፪፡፡ ሰማዕታት ዲያብሎስን ድል ነሥተዋል፡፡ የድል አድራጊዎቹ ኃይል ደግሞ የበጉ ደም ነበር፡፡ በጉ የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በሸፍቶቹ ፊት ዝም እንደሚል በግ ለሞት የተነዳው፣ ስለሁላችን መተላለፍ የቆሰለው፣ በቁጣ ሲስቡት በፍቅር የተከተለው፣ ኃጢአታችንን ሊያስወግድ የታረደው የእግዚአብሔር በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ኢሳ.፶፫፥፯ እና ዮሐ.፩፥፳፱፥፴፯፡፡

የሰማዕታት ድል፣ የሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር መንግስት መቅረብ፣ የሞት ደጆች መንቀጥቀጥ፣ የሲኦል መሠረት መናወጥ፣

www.zeorthodox.org

የሞት መውጊያ መሰበርና የዲያብሎስ መንበርከክ በደሙ ኃይል የተደረገ ነው፡፡ የሰማዕታቱ የድል ምንጭ የበጉ ደምና የምስክራቸው ቃል ነው፡፡ የጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደምና የምሥራቹ ቃል ከሳሾችን አንበርክኳል፣ የዲያብሎስን ትጥቅ አስፈትቷል፡፡

ሰማዕታት በቃልም በሕይወትም የክርስቶስ ምስክሮች ነበሩ፡፡ እስከሞት በመታመን ምስክርነታቸውን በደም አተሙ፡፡ ከሰማዕታት ሕይወት ጽንዓትን፣ ንጽሕናን፣ ምስክርነትን፣ ባመኑበት ጸንተው መኖርንና ላመኑት መሞትን እንማራለን፡፡ የዘመኑ ሰማዕትነት ኃጢአትና ክፉትን በማሸነፍ ራስንም በመግዛት በቅድስና መኖር ነው፡፡

## ማጠቃለያ

የሰማዕታቱ ድል ከክርስቶስ ደምና ሕያው ቃል የተገኘ ነው፡፡ በእምነት ጽንዓት ንጽሕናንም ገንዘብ በማድረግ ራስን በመግዛት በፈቃዱ መኖር ትልቅ ሰማዕትነት ነው፡፡ ድል መንሣትን የምናገኘው በሰማዕታቱ የኃይል ምንጭ ነው፡፡ የሰማዕታቱ የኃይል ምንጭ ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ኃይልን በሚሰጠን በክርስቶስ ሁሉን እንችላለን፡፡

## ተግባር

መምህሩ ክርስቶስ ለምን በበግ እንደተመሰለ ወጣቶችን ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ኃጢአትና መዘዙ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ከኃጢአት በመራቅ በቅድስና እንዲኖሩ መሞከር

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "እነዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ፣ አትንኩትም፡፡" ዘፍ.፫÷፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሮሜ. ፭÷፲፪-፳ እና ፩ዮሐ. ፫÷፬-፲

## መግቢያ

እግዚአብሔር ሰውን አክብሮ ፈጥሮ በገነት አስቀመጠው፡፡ የተገዥነት ምልክት የሆነችውን ዕፀ በለስ "እንዳትሞቱ ከእርሷ አትብሉ" ብሎ ከለከላቸው፡፡ ሰው የተከለከለውን አደረገ፡፡ የእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፉ ኃጢአት ሠራ፡፡ የኃጢአቱም መዘዝ ሞት አመጣበት፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ፤ በኃጢአትም ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ" በማለት ኃጢአትና መዘዙን አብራርቷል፡፡ ሮሜ ፭÷፲፪-፳፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በመንፈስ ኅብረት እያደረገ በጽድቅ ሥርዓት ይኖር ነበር፡፡ የቃል ኪዳኑን ማረጋገጫ ሕግ በመተላለፍ በመንፈሱ ሞተ፡፡ የሕጉ ዓላማ መታመኑን በሥራ መግለጫ፣ ፍቅሩን ማሳያና መገዛቱን ማስመስከሪያ ነበር፡፡ አዳም ግን የጠላትን ምክር ሰምቶ የአምላኩን ቃል ኪዳን አፈረሰ፡፡ በኃጢአት ካደፈ ማንነት የተገኘን ሁሉ የኃጢአቱ ተጠያቂ ሆንን፡፡

**ኃጢአት ምንድን ነው?**

ኃጢአት ማለት አመፀኝነት፣ መተላለፍ፣ ውለታ መርሳት፣ በርኩሰት ኃይል መያዝና ዓላማን መሳት ማለት ነው፡፡

ኃጢአት ማለት በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ የሚያደርግ ትእዛዛቱን በማፍረስ የረከሰ ***አኗኗር*** ማለት ነው፡፡ የኃጢአት ምንጭ ለእግዚአብሔር አለመታመን ነው፡፡ አዳም የአምላኩን ቃል ቸል በማለት ባለመታመኑ ለኃጢአት ተዳርጓል፡፡

**የኃጢአት መዘዝ፡-** የኃጢአት የመጀመሪያ መዘዙ ከእግዚአብሔር ጋር ጠላትነትን መመሥረት ነው፡፡ ሰው ኃጢአት ሲሠራ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው የፍቅር ግንኙነት ይቋረጣል፡፡ ለሰው ትልቅ ሞቱ ከአምላኩ መለየቱ ነው፡፡ የኃጢአት ሁለተኛ መዘዙ ከራሳችን ጋር እንኳን ሰላም እንዳንሆን ማድረግ ነው፡፡ ኃጢአት የሠራ ሰው ኅሊናው አያርፍም፤ ሰላም የለውም፡፡ አዳም ኃጢአት ከሠራ በኋላ ሰላሙን አጣ፣ ጸጋው ተገፈፈ፣ ፈራ፣ ተደበቀ፡፡ የኃጢአት ውጤት ቅጣት፣ ፍርሃት፣ ሞት፣ ኩነኔ፣ ጭንቀትና መከራ ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

**የኃጢአት ደመወዝ ምንድን ነው?** የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው፡፡ ሮሜ ፮÷፳፫፡፡ **ኃጢ**አት የምኞት የበኩር ልጅ ናት፡፡

ኃጢአት ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለችና ሞት የኃጢአት ልጅ ነው፡፡ ያዕ. ፩÷፲፭፡፡ **ኃጢ**አት ለሚሠሩ ሰዎች የኩነኔ ብያኔ ይጠብቃቸዋል፡፡

**ከኃጢአት እንዴት መውጣት ይቻላል?** ኃጢአት በራሱ ኃይል አለው፡፡ በእግዚአብሔር ያለን እምነት ሳስቶ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለን ኅብረት ከላላ በኃጢአት ተሸንፈን ታስረን እንወድቃለን፡፡ የኃጢአት ኃይል የሚሸነፈው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው፡፡ ሰው በክርስቶስ አምኖ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት ሲያደርግ በኃጢአት ላይ የመሠልጠን ጸጋን ይቀበላል፡፡ ሮሜ ፰÷፱ - ፲፫፡፡

ከልብ ተፀፅቶ በመመለስ ንስሐ መግባትና የኃጢአት ስርየት ማግኘት ይቻላል፡፡ ከኃጢአት ነጻ ለመውጣት ብቸኛው መንገድም ይኸው ነው፡፡

## ማጠቃለያ

የኃጢአት መዘዝ ሰውን ጎድቷል፡፡ የእግዚአብሔር የመሆናችን ምልክት ኃጢአትን ድል መንሣት ስንችል ነው፡፡ **፩ዮሐ.፫÷፮፡፡ ኃጢአትን በማሸነፍ በቅድስና መኖር ይጠበቅብናል፡፡ ድካም የሚስማማው ሰውነታችን በኃጢአት ሲወድቅ** በንስሐ እንነሣ፡፡

## ተግባር

✍መምህሩ ወጣቶች የንስሐ አባት እንዲኖራቸውና ኃጢአታቸውን መናዘዝ እንዲችሉ ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# መጽሐፍ ቅዱስ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንዲተዋወቁ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "የምታነበውን ታስተውለዋለህን?" ሐዋ.፰÷፴

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ኢያ.፩÷፰፣ ሕዝ.፫÷፩-፫

## መግቢያ

መጽሐፍ ቅዱስ ማለት የተለየ መጽሐፍ ማለት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን የዘላለም ምክር የያዘ የቅዱሳት መጻሕፍት መዝገብ፤ የተቀደሰና የሚቀደስ መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው ልጅ የሕይወት መመሪያ ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ከአርባ በማያንሱ ቅዱሳን ሰዎች የተጻፈ የመለኮት ድርሰት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የመጻሕፍት ሁሉ ራስ፤ የቃል ኪዳን መዝገብ ነው፡፡ እግዚአብሔር ከልጆቹ ጋር ያደረጋቸውን መሀላዎች መዝግቧል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የአምላካችንን ፍቃድ የምናውቅበት፣ በረከትን የምንቀበልበትና ኃይል የምንታጠቅበት የሕይወት መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሁለቱ ኪዳናት ሰነድ ሲሆን ብሉይ ኪዳን በዕብራይስጥ፤ ሐዲስ ኪዳን በግሪክ ቋንቋ ተጽፈዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ከ፲፬፻፹፮/1486/ዓ.ዓ - ፻/100/ ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ የተጻፈ መጽሐፍ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**፩. መጽሐፍ ቅዱስን ለምን እናነባለን?**

- የእግዚአብሔርን ድምፅ ለመስማትና ፈቃዱን ለማወቅ፤ ምሳ. ፩÷፴፫፡፡
- ሕግና ትእዛዛቱን በማወቅ ለመፈጸም፡፡ ማቴ. ፳፪÷"7፡፡
- በክርስቲያናዊ ሕይወታችን ለማደግ፡፡ መዝ.፩÷፪-፫፡፡
- በጽድቅ ቃል የጽድቅ ሥራ ለመሥራት፡፡ ዕብ.፭÷፲፫፡፡
- የዘወትር ምግባችን ስለሆነ፡፡ ማቴ.፬÷፬፡፡
- መንገዳችን እንዳይጨልም በሕጉ ብርሃን ለመመላለስ፡፡ መዝ.፻፲፰÷፻፭፡፡
- እግዚአብሔርን በማወቅ እርሱን ወደ መምሰል ለማደግ፡፡ ፩ጢሞ.፬÷፰፡፡
- ታሪክን፣ሃይማኖትን፣ የጥንቱን ማኅበረሰብ ባህልና የክርስቲያኖችን አኗኗር ለማወቅ፡፡

www.zeorthodox.org

**፪. መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እናነባለን?**

- መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች እንከተል፡፡
- እግዚአብሔር ምስጢር እንዲገልጥልን መጸለይ፡፡
- በይዘትና በታሪክ ላይ ተመሥርተን ማጥናት፡፡
- ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ ደብተራችን መመዝገብ፡፡
- ቃሉን ማክበርና ለቃሉ ያለንን ፍቅር ማሳደግ፡፡
- በመምህራንና በመጻሕፍት መታገዝ
- ቃሉን በሕይወታችን ለመተርጎም በሙሉ ፍቃድ መቀበል፡፡ ሐዋ.07÷01፡፡

**፫. የመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ አከፋፈል፡-**

መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን በመባል በሁለት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል፡፡

፫.፩. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በአጠቃላይ ብዛታቸው አርባ ስድስት ነው፡፡ ዝርዝራቸው እንደሚከተለው ነው፡፡

፫.፩.፩.የሕግ መጻሕፍት .......................... 5 (ዘፍጥረት፤ ዘጸአት፤ ዘሌዋውያን፤ ዘኁልቍ፤ ዘዳግም)

፫.፩.፪.የታሪክ መጻሕፍት ....................... 17

፫.፩.፫. የጥበብና የመዝሙር መጻሕፍት .................. 8

፫.፩.፬. የትንቢት መጻሕፍት ..................................... 16

፫.፩.፭ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብዛታቸው ሠላሳ አምስት ነው፡፡ በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

፫.፪.  የወንጌል ክፍል ........................... 4 (ማቴ፤ ማር፤ ሉቃ፤ ዮሐ)

፫.፪. ፩. የታሪክ ክፍል ............................. 1 (የሐዋርያት ሥራ)

፫.፪.፪. የትምህርት ክፍል (መልእክታት) .............. 21 (ዓለማቀፋዊ፣ የአብያተ ክርስቲያናትና የግለሰቦች)

፫.፪.፫.የትንቢት ክፍል (የራእይ መጽሐፍ ) ............... 1 (ራእየ ዮሐንስ)

፫.፪.፬.የሥርዓት ክፍል .................................. 8

**፬. መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ቋንቋ ምንድን ነው?**

ብሉይ ኪዳን በዕብራይስጥ፤ ትንቢተ ዳንኤል ብቻ በአራማይክ ቋንቋ ተጽፏል፡፡
ሐዲስ ኪዳን በግሪክኛ (ፅርዕ) ቋንቋ ተጽፏል፡፡

www.zeorthodox.org

**፭. መጽሐፍ ቅዱስን ማን ጻፈው?**

ብሉይ ኪዳንን ሠላሳ ሁለት ቅዱሳን አባቶች፣ መሳፍንት፣ ነቢያትና ነገሥታት ጻፉት፡፡

ሐዲስ ኪዳንን ስምንት ቅዱሳን ሐዋርያትና አርድእት ጽፈውታል፡፡

**፮. የመጽሐፍ ቅዱስ ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሞአል**

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከጌታችን ልደት በፊት በ፪፪፻፹፬/284/ ዓ.ዓ ወደ ግሪክኛ ቋንቋ ተተርጉሙዋል፡፡ ቅዱሳን መጻሕፍት በግእዝ ቋንቋ በንግሥት ሳባና በዘጠኙ ቅዱሳን ዘመን ተተርጉመዋል፡፡ አባ አብርሃም (ሮሜ) ከ፲፰፻፲፮-፲፰፴፪/1816-1832/ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አማርኛ ቋንቋ ተርጉመውታል፡፡ አለቃ ተወልደ መድኅን ወደ ትግርኛ የተረጎሙት ሲሆን አኔሲሞስ ነሲቡ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ኦሮምኛ ተርጉመውታል፡፡

## ማጠቃለያ

መጽሐፍ ቅዱስ የአማኞች የሕይወት መመሪያ ነው፡፡ በዕለታዊ ኑሮአችን የቅዱስ ቃሉን ድጋፍ ለማግኘትና በዘመናችን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት ለማጠናከር መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ አለብን፡፡

## ተግባር

መምህሩ ወጣቶች መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ እንዲጀምሩ ይምከራቸው፡፡ በጋራ እንዲያጠኑ ያበረታታቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# መጽሐፈ ኢዮብ ፩

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ሕይወት ደስታና ሐዘን፣ ማግኘትና ማጣት ችግርና መከራ ሁሉ የሚፈራረቁበት እንደመሆኑ ወጣቶች ይህን ተገንዝበው ለመከራ እንዳይሸነፉ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔርም ነሣ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን፡፡" ኢዮብ. ፩÷፳፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መጽሐፈ ኢዮብ ፩-፵

## መግቢያ

ኢዮብ በዘመነ አበው ከአብርሃም በኋላ የኖረ አባት ነው፡፡ ኢዮብ ብዙ መከራ እየተፈራረቀበት በእምነቱ እንደጸና እግዚአብሔርን ያከበረ የትዕግሥት አርአያ ነው፡፡ ቅዱስ ያዕቆብ "የመከራና የትዕግሥት ምሳሌ የሆኑትን በጌታ ስም የተናገሩትን ተመልከቱ፡፡ እነሆ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፡፡ ኢዮብ እንደታገሠ ሰምታችኋል፤ ጌታም እንደፈጸመለት አይታችኋል፡፡" በማለት የኢዮብን የጽናት ምሳሌነት ጠቅሷል፡፡ ያዕ. ፭÷፲፩፡፡ **ኢዮብ ሃብትና ንብረቱ የተትረፈረፈለት በልጆች የተከበበና** የተከበረ ዝነኛ ሰው ነበር፡፡ የኢዮብ የሆነው ሀብትና ንብርቱ ሁሉ በድንገት እንደበረዶ ክምር አየተንሸራተተ ቀልጦ ጠፋ፡፡ ኢዮብ ሰፊ ሀብትና ንብረቱ ባክኖ ምንም የሌለው ድሃ ሆነ፡፡ ብቻውን የዓለምን መከራ ሁሉ ተሸከመ፡፡ የልጆቹን ሞት፣ የንብረቱን መበተንና የሚስቱን ክህደት በአንድ ጀንበር አስተናገደ፡፡ የኢዮብ መልስ "እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሣ የእግዚአበሔር ስም የተባረከ ይሁን፡፡" የሚል በጥበብ የተሞላ ቃል ነበር፡፡ ኢዮብ ሰውነቱ በቁስል ተወርሶ፣ ልጆቹን በሞት ተነጥቆ፣ ሀብትና ንብረቱ ጠፍቶ፣ ሚስቱ ጥላው ሄዳ ሁሉም ሰው ሸሽቶትና በወዳጆቹ መራራ ቃል ተሰብሮ በእምነቱ እንደጸና እግዚአብሔርን ያመለከ አማኝ ነው፡፡ በኢዮብ የሕይወት ገጾች ክፉና ደግ፣ ደስታና መሪር ሐዘን፣ ማግኘትና ማጣት፣ መከራና ችግር እየተፈራረቁ በሚገባ ተጽፈዋልና እንማርባቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

www.zeorthodox.org

### ***፩.የመጽሐፉ ይዘት***

መጽሐፈ ኢዮብ በእምነቱ ጸንቶ በትዕግሥት ተደግፎ የደረሰበትን መከራና ችግር ያለፈ ፈተናውን በድል የተወጣው የታላቁ አባት የኢዮብ ታሪክ ተመዝግቦ የሚገኝበት ማኅደር ነው፡፡ መጽሐፈ ኢዮብ የእግዚአብሔርን ጥበቃ፣ እንክብካቤ፣ ምሕረት፣ ግርማ፣ ፍርድና ሁሉን ቻይነት ከቸርነቱ ጋር የሚገልጽ መጽሐፍ ነው፡፡ በዚህ የጥበብ መጽሐፍ ሰይጣን በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ማብቂያ የሌለው ጠብና ጥላቻ ለመፍጠር ቀን ከሌሊት ሳያርፍ የሚጥር የሰው ልጆች ሁሉ ጠላት እንደሆነ ተገልጿል፡፡ የባለ

ታሪኩም ጽናት እግዚአብሔርን በእግዚአብሔርነቱ እንደሚወድ በደስታም ሆነ በሐዘን ጊዜ በፍጹም ታማኝነትና በጽናት እንደሚያመልክ አስመስክሮአል፡፡ እግዚአብሔር በሁሉን ቻይነቱ ጻድቁን ከመከራ መንጋጋ እንደሚያወጣ፤ ጥበቃውና ቸርነቱን ሳያቋርጥ በበረከት እንደሚያትረፈርፈው አሳይቷል፡፡ ኢዮብም ይህን የእግዚአብሔርን ቸርነትና ማዳኑን በሕይወቱ መስክሮአል፡፡

### ፪. የመጽሐፉ ዓላማ

የመጽሐፉ ዋና ዓላማ ሰይጣን ለእግዚአብሔር ያለውን ተግዳሮትና በኢዮብ ላይ ያደረሰውን ጥቃት፤ የኢዮብን ፈተና መከራና በታማኝነት፣ በጽናትና በትዕግሥት የተዋበ የድል ፍሬ ማሳየት ነው፡፡

### ፫. የመጽሐፉ አከፋፈል

ምዕራፍ ፩÷፩-፫፡- የኢዮብ ደስታ

ምዕራፍ ፩÷፮-፪÷፲፫፡- የኢዮብ ድንገተኛ መከራ እና የሰይጣን ክስ

ምዕራፍ ፪÷፲፬፡- የኢዮብ የጸና እምነት፣ የሚስቱ ክህደትና የወዳጆቹ መምጣት

ምዕራፍ ፫፡- የኢዮብ ሰቆቃ

ምዕራፍ ፬- ፴፩፡- ሦስቱ ወዳጆቹ ያረጉት ክርክርና የኢዮብ መልስ

ምዕራፍ ፴፪-፴፯፡- የኤሊሁ አስተያየት

ምዕራፍ ፴፰-፵፩፡- የእግዚአብሔር መልስ

ምዕራፍ ፵፪፡- የኢዮብ መጸጸትና መጽናናት

## ማጠቃለያ

መጽሐፈ ኢዮብ የሰይጣንን የማያቋርጥ ፈተና፣ የእግዚአብሔርን ከለላና የኢዮብን ጽንዓት በሰፊው ይተርካል፡፡ መጽሐፈ ኢዮብ ማግኘትና ማጣት፤ ከፍታና ዝቅታ፤ ክብርና ውርደት በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት ሊለውጡት እንደማይገባ ይመክራል፡፡ በሕይወት ውስጥ እየተፈራረቀ የሚያጋጥመውን ደስታና ሐዘን፣ ችግርና መከራ ሁሉ በጸጋ በመቀበል እስከ መጨረሻው በእምነት መጽናት እንደሚገባ ይነግረናል፡፡

## ተግባር

- ✍ መምህሩ ወጣቶችን በሕይወት ውስጥ እየተፈራረቁ ስለሚያጋጥሙአቸው ፈተናዎች በማንሣት ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# መጽሐፈ ኢዮብ ፩

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በእምነት መጽናት በፈተና ውስጥ እያሳለፈ የድል ፍሬዎችን እንደሚያቀዳጅ ወጣቶች እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** *"ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ* እንደሆንክ አሳብህንም ይከላከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ፡፡" ኢዮብ. ፵፪ ÷ ፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** *መጽሐፈ ኢዮብ* ፴-፵፪

## መግቢያ

መጽሐፈ ኢዮብ በመከራ መጽናት የታሪክን ፍፃሜ እንደሚያሳምር ያመላክታል፡፡ ኢዮብ በእምነቱ እስከመጨረሻው ጸንቶ ተገኘ፡፡ እግዚአብሔርም በእጥፍ ባረከው፡፡ የኢዮብ የመከራ ሌሊቶች ነጉ፤ የመከራውን ዓላማ ያላስተዋሉት ወዳጆቹ ከጽናቱና ከትዕግሥቱ መልካም ፍሬዎች ተማሩ፤ የኢዮብ ደስታ ተመለሰ፡፡ "መስማትንስ በጀሮ በመስማት ሰምቼ ነበር፤ አሁን ግን ዓይኔ አየችህ" በማለት ኢዮብ ደስታውን ገለጸ፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ እንደሆነ አሳቡም ከቶ እንደማይከለከል መሰከረ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

መጽሐፈ ኢዮብ እግዚአብሔር የኢዮብን ሕይወት በመከራ ውስጥ እንዳስጌጠው የሚያሳይ የክብሩ አደባባይ ነው፡፡ መጽሐፈ ኢዮብ በእምነት ጸንተን የእግዚአብሔርን ቸርነት በመጠበቅ ታሪካችንን በድል መደምደም እንደምንችል ያሳያል፡፡ መጽሐፈ ኢዮብ እግዚአብሔርን በጤንነቱ ብቻ ሳይሆን በሕመምም ሆኖ፤ በሃብት ተከቦ ብቻ ሳይሆን በድህነትም ተመትቶ፤ በወዳጅ ዘመድ ተደግፎ ብቻ ሳይሆን ወዳጅም ሲሸሽ በብቸኝነት በችግርና በመከራ ውስጥም ሆነን ማምለክ ማመስገን እንዳለብን ያስተምራል፡፡

***፩. የኢዮብ ፈተና፡-*** ኢዮብ የመከራ ጅራፍ ተደጋግሞበታል፡፡ ሃብትና ንብረቱን ተዘረፈ፤ ቤቱ ተቃጠለ፤ ልጆቹ ሞቱ፤ ወዳጆቹ ከአጠገቡ ሸሹ እንደ ጉም በነኑ፤ ሚስቱ ከዳችው፤ ሰውነቱ በደዌ ተመታ፡፡ የቀሩት ወዳጆቹ (ኤልፋዝ፣ በልዳዶስና ሶፋር) በቁስሉ ላይ እንጨት ሰደዱበት፡፡ ኢዮብ የዓለምን መከራ በአንድ ወቅት ተሸከመ፡፡ በአንድ የሕይወት አጋጣሚ በዚህ የሕይወት ብርቱ መከራና ችግር የፈተና ሰልፍ በእምነታችን ጽናት ተደግፈን በድል እናልፋለን፡፡

www.zeorthodox.org

***፪. ለኢዮብ የማይነጋ የመሰለው የመከራ ሌሊት፡-*** ኢዮብ የተሻለ ዘመን የሚመጣ አልመሰለውምና "ዓይኔ ከእንግዲህ ወዲህ መልካም አያይም" አለ፡፡ የተወለደበትን ቀን ረገመ፡፡ ኃያሉን እግዚአብሔርን ተከራከረ፡፡ የመከራ ሌሊት የማይነጋ ቢመስልም ይነጋል፤ ብሩህ ቀን ይመጣል፡፡ የመጽሐፈ ኢዮብ ጭብጥ እግዚአብሔር በሁሉን ቻይነቱ ሁሉን እንደሚለውጥ ማስረዳት ነው፡፡

***፫. የእግዚአብሔር ጉብኝት፡-*** እግዚአብሔር ለኢዮብ መለሰለት፤ የኢዮብን ጽናት ባረከ፡፡ የኢዮብን ሃብት ሁለት እጥፍ አድርጎ ሰጠው፡፡ ያውቁት የነበሩት ሁሉ ወደ እርሱ መጡ፡፡ አጽናኑት፤ ስጦታ አቀረቡለት፡፡ ኢዮብ ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው በዛለት፡፡ ጤናው ታደሰ፤ ልጅ ወለደ፤ ክብሩ ተመለሰ፤ ዘመን ተሻጋሪ ባለታሪክና ሕያው አርአያ ሆነ፡፡ እግዚአብሔር ሲጎበኘን መልካሙ ሁሉ ይደረግልናል፡፡ የእግዚአብሔር ጉብኝት ሁሉን ይለውጣል፡፡

***፬. የመከራ ፍሬ፡-*** የመከራ ፍሬ ይጣፍጣል፡፡ እግዚአብሔር በረከትን በመከራ ውስጥ ሰውሮአል፡፡ መከራው ሲነካን በረከቱ ይገለጥልናል፡፡ የኢዮብ መከራ ያመጣለትን የበረከት ለውጥ አይተናል፡፡ መከራን በጽናት ካሳለፍነው የማያልፍ ዘለዓለማዊ ክብር ያስገኝልናል፤ ካልጸናን ግን በሚያልፈው መከራ ወድቀን በረከታችንን እናጣለን፡፡ ለመከራ ያለን ትርጉም የተዛባ በመሆኑ እንፈራዋለን፡፡ መከራ የጥንካሬ ምንጭ፣ የማንነት መገለጫ፣ የክብር መገለጫ፣ የስኬት ድልድይ፣ የበረከት መሰላልና የከፍታ ምስጢር ነው፡፡ በመከራ ውስጥ ካላለፍን እምነታችን እንዴት ይፈተናል? ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን በመከራ እየተፈተን እንጠራለን፡፡ የመከራን ጊዜ በጽናትና በትዕግሥት ማለፍ ያስከብራል፤ በአንደበታችን መሳት የለብንም፡፡ ጽናት የድል ፍሬ ያመጣልና እንጽና፡፡

## ማጠቃለያ

መጽሐፈ ኢዮብ የኢዮብን ፈተና፣ የመከራ ወራት፣ የእግዚአብሔርን መልስና የኢዮብን የጽናት ፍሬ መዝግቦአል፡፡ መጽሐፈ ኢዮብ ከሳሻችን ሰይጣን እንዳፈረ እግዚአብሔር እንደከበረና ኢዮብ እንደተባረከ ይመሰክራል፡፡ ለእግዚአብሔር ያለንን እምነት በማሳደግ ዲያብሎስን እናሳፍር፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶቹን ከባለታሪኩ ምን እንደተማሩ ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የመታዘዝ ሕይወት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች በደስታ በመታዘዝ ክብርን እንዲያገኙ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** *“መታዘዝ ከመስዋዕት ይበልጣል፡፡”* ፩ሳሙ. ፲፭÷፳፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃ.፪÷፶፩ እና ፩ዮሐ. ፭÷፩-፫

## መግቢያ

*መታዘዝ የትሕትና ፍሬ ነው፡፡ መታዘዝ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅርና ለሰው ያለንን ክብር ያሳያል፡፡ የጽድቅን በረከት እየተቀዳጁ በመንፈሳዊነት ዘለዓለማዊ ክብር ለማዳግ መሠረቱ መታዘዝ ነው፡፡ መታዘዝ ማለት የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት፣ ሥልጣኑን መቀበልና ትእዛዙን አክብሮ መፈጸም ነው፡፡ ዘጸ. **፬÷፴፭-፵**፡፡* **ለሚታዘዙት በረከቱ ይደርሳቸዋል፡፡** ለማይታዘዙት ደግሞ መርገም በመንገዳቸው ይጠብቃቸዋል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

***ለእግዚአብሔር መታዘዝ፡-*** *እግዚአብሔር የቅዱሳን መናፍስት አባት፣ የነገሥታት ንጉሥና ፈጣሪ ዓለማት ነው፡፡ ሰው በደስታ ሊታዘዝለት ይገባል፡፡ ለእግዚአብሔር መታዘዛችን የምንገልጠው ድምፁን በመስማት፣ ሕጉን በመጠበቅ፣ በፍቅሩ በመኖር፣ በምሕረቱ በመተማመን፣ በፈቃዱ በመመላለስና ፍጥረቱን (ሥራውን) በማክበር ነው፡፡*

*የአዳም አለመታዘዝ በሰው ልጆች ላይ ጥፋት አመጣ፡፡ የእስራኤል አለመታዘዝ በምድረ በዳ አስቀራቸው፡፡ ዕብ. **፫÷፲፰**፡፡* ***ለእግዚአብሔር የማይታዘዙ ሕይወታቸውን በጅምር ያስቀራሉ፡፡ የማይታዘዙ ልጆች መድረሻ በረከትና*** *የስኬት ጫፍ ሳይሆን መርገምና የሲኦል ደጃፍ ነው፡፡ ክርስቶስ ኢየሱስ በሥጋ ሲገለጥ በሥጋ ለባሾች መካከል እንደ እግዚአብሔር እየሠራ እንደሰው ሲመላለስ ያስተማረን የጽድቅ ሥርዓት መታዘዝ ነው፡፡ ይስሐቅ ለአባቱ እስከሞት እንደታዘዘ ክርስቶስም ለመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ፡፡ በመታዘዙ ዓለምን አዳነ፡፡ ፊልጵ. **፪÷፯-፱**፣ **ዕብ. ፭÷፰**፡፡* ***ለምናምነው ሁሉ ፍለጋውን ትቶልናል፡፡***

www.zeorthodox.org

*በሁሉም ሥፍራ ያሉ ሰዎች ንስሐ እንዲገቡና በልጁ እንዲያምኑ እግዚአብሔር አዟል፡፡ ማር. **፩÷፲፭**፣ **ሐዋ. ፲፯÷፴**፣ **፩ዮሐ. ፫÷፳፫**፡፡* ***በክርስቶስ አምኖ የጽድቅ ሥርዓትን መፈጸም ትልቁ ታዛዥነት ነው፣፣ የእግዚአብሔርን ቃል እያወቀ*** *የማይታዘዝና እግዚአብሔርን “እወዳለሁ” የሚል ሰው ራሱን ያታልላል፡፡ እግዚአብሔርን በመውደድ በትሕትና መታዘዝን የሚለማመድ ሰው የጽድቅ አገልጋይ ይሆናል፡፡ ዮሐ. **፲4÷፲፭**፣* ***ያዕ. ፩÷፳፪-፳፭፡፡***

እግዚአብሔር የሚታዘዙትን ይባርካል፤ ያከብራልም፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ፀሐይ የሚያበሩት በምድር ታዘው ያከበሩት ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ወዳጆቹን የሚለይበት ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡ ትዕዛዙን በደስታ ተቀብሎ መፈጸም በረከትን ያስገኛል፡፡ በእግዚአብሔር ያለን ፍቅር የሚገለፀው በመታዘዛችን ነው፡፡

**ለወላጆች መታዘዝ፡-** ወላጆች ደክመው ያሳደጉን ባለውለታዎቻችን ናቸው፡፡ ወላጆቻችንን እንድንታዘዝ ሕግና ነቢያት፤ ተፈጥሮና ወንጌል መክረውናል፡፡ መታዘዝ ሁለቱም ኪዳናት በማኅተም ያጸኑት ቃል ነው፡፡ ኦሪት "አባትህንና እናትህን አክብር እግዝአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም፡፡" ትለናለች፡፡ ዘጸ. ፳÷፲፪፡፡ **ሐዲስ ኪዳን "ልጆች ሆይ ለወላጆቻችሁ** በጌታ ታዘዙ ይህ የሚገባ ነውና፡፡" ይለናል፡፡ ኤፌ. ፮÷፩፡፡ **ክርስቶስ ለእናቱ ይታዘዝ ነበር**፡፡ ሉቃ. ፪÷፶፩፡፡ **ለወላጆች ስንታዘዝ ፍቅራቸው** ይበዛልናል፤ እግዚአብሔር ይባርከናል፤ ዕድሜአችን ይረዝማል፤ ወደፊት ለእኛም ልጆቻችን ይታዘዙናል፡፡

**ለመሪዎች መታዘዝ፡-** የእግዚአብሔር ልጆች ለሥጋዊው ዓለምና ለመንፈሳዊው ዓለም (ለቤተ ክርስቲያን) መሪዎች እንዲታዘዙ እግዚአብሔር አዟል፡፡ ቲቶ. ፫÷፩፣ **ዕብ. ፲፫÷፲፯፡፡ መሪዎችን መልካም በሆነ ሁሉ** መታዘዝ ይገባል፡፡ ነገር ግን እንደ ናቡከደነፆርና ብልጣሶር "እግዚአብሔርን ካዱ ለጣዖት ስገዱ" ለሚሉ ትእዛዛት እንደ ሦስቱ ወጣቶች "በእምነት እምቢ" ማለት አለብን፡፡ ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይገባልና፡፡ ሐዋ. ፭÷፳፱-፴፡፡ **ዳን. ፫÷፲፫-፴፡፡ ለዓለም መሪዎች የምንታዘዘው** ሃገራዊ ሕጎችን በመጠበቅና በመፈጸም ነው፡፡ ሮሜ. ፲፫÷፩፣ **፩ጴጥ. ፪÷፲፫፡፡ ለቤተክርስቲያን መሪዎች የምንታዘዘው** የእግዚአብሔርን ሕግ በመፈጸም፣ የሃይማኖት ቤተሰቦችን በሚያሰፈልጋቸው በጎ ነገር በመርዳትና ለቤተክርስቲያን የሚያስፈልገውን በማሟላት ነው፡፡ ፊል. ፪÷፲፪፣ **ዕብ. ፲፫÷፯፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሠራተኞች ለአሠሪዎቻቸው** እንዲታዘዙ፣ ሽማግሌዎችንም እንድንታዘዛቸው ያዛል፡፡ ኤፌ. ፮÷፭፣ **፩ጴጥ. ፭÷፭**፡፡

## ማጠቃለያ

መታዘዝ የበረከት መንገድ ነው፡፡ ለእግዚአብሔርና ለሰዎች በመታዘዝ የሁለቱንም ኪዳናት ቃል እንፈጽም፡፡

## ተግባር

♦መምህሩ ወጣቶች ለሰውም ለእግዚአብሔርም በደስታ እንዲታዘዙ ይምከራቸው፡፡ የመታዘዝ ፍሬዎችንና የአለመታዘዝ መረገሞችን እንዲያነፃፅሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ንጹሕ አምልኮ

**የትምህርቱ ዓላማ፦** ወጣቶች እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ እንዲያመልኩ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፦** "ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፡፡" ያዕ. ፩÷፳፯

**ተጨማሪ ምንባባት፦** ዮሐ. ፬÷፳፬

## መግቢያ

አምልኮ ማለት በትሕትና መገዛት፤ በፍቅሩ ጥላ መውደቅ፤ ዘላለም ለሚኖረው አምላክ በፍጹም እምነት መንበርከክ፤ በመንፈስና በእውነት የሚፈጸም ሥርዓት ማለት ነው፡፡ አምልኮ ከልብ የሚመነጭና በፍጹም ፍቅር የሚፈጸም እንጂ ውጫዊ (አፍአዊ) ድርጊት አይደለም፡፡ አምልኮ ጸሎትን፣ ዝማሬን፣ ቅዳሴን፣ ስግደትንና ስጦታን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፦

አምልኮ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ እውነት ላይ የሚመሠረት በመንፈስ የሚፈጸም የሕይወት ሥርዓት ነው፡፡ አምልኮ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የምናደርግበት ምስጢር ነው፡፡ እግዚአብሔር ስላደረገውና ስለሚያደርገው ነገር መመስገንና መመለክ ይገባዋል፡፡ እግዚአብሔርን ማምለክ ማለት ከልዕልናው አገዛዝ ሥር መሆን ማለት ነው፡፡ የተፈጠርነው እግዚአብሔርን ለማምለክ ስለሆነ ፍጥረታት ሁሉ የሚያመልኩትን በጽድቅ ሥርዓት በማምለክ መጽናት፤ ለምስጋናም መትጋት አለብን፡፡

ንጹሕ አምልኮ በእግዚአብሔር ፊት ነውር የሌለበት መሥዋዕት፤ እግዚአብሔር የሚከብርበትና ሰው የሚባረክበት የጽድቅ ሥርዓት ነው፡፡ ንጹህ አምልኮ በእግዚአብሔር እውነት ተመሥርተን፣ በመንፈስ ተቃኝተን፣ በደስታና በፍቅር የምንፈጽመውን ማንኛውንም የአምልኮ ሥርዓት ያጠቃልላል፡፡ ንጹሕ አምልኮ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አለው፡፡

### *፩. ጸሎት*

በስሙ የሆነ ጸሎት በፈቃዱ ፊት ተቀባይነት አለው፡፡ መንግሥቱንና ጽድቁን መጠየቅ ተቀባይነት ያለው አምልኮ ነው፡፡ ማቴ. ፯÷፴፫፣ ዮሐ. ፲፮÷፳፯፡፡ **ጸሎት የአምልኮ መፈጸሚያ አንዱ ክፍል** ነው፡፡ የቤተሰብ፣ የግልና የማኅበር ጸሎት አለ፡፡ ሁሉም ጸሎቶች በስሙ፣ እንደ ፈቃዱ፣ በእምነትና በመንፈስ ይፈጸማሉ፡፡ ጸሎት የመንፈሳዊ ሕይወት እስትንፋስ በመሆኑ በፍጹም ተመስጦ ከእግዚአብሔር ጋር የምንነጋገርበት ንጹሕ አምልኮ ነው፡፡

### *፪. ስግደት*

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ትምህርተ አምልኮ"ን ለሳምራዊቷ ሲናገር "መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን፡፡

www.zeorthodox.org

እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል” በማለት አስተምሮናል፡፡ ዮሐ. ፬÷፳፬፡፡

ስለዚህ እግዚአብሔርን በማወቅ በመንፈስና በጽድቅ ልንሰግድለት ይገባል፤ ይህ የተወደደ ንፁሕ አምልኮ ነውና፡፡

### ፫. ድሆችን መጎብኘት፡-

ቅዱስ ያዕቆብ ንጹሕ አምልኮ ያለው “ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነቱን መጠበቅን” ነው፡፡ በደስታ መለገስ፣ ድሆችን መዘከርና ሰው ለሌላቸው መቆም ንጹሕ አምልኮ ነው፡፡

ድሆች መሥራት ከቻሉ የሥራ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤ ካልቻሉ ግን በኑሯቸው ማገዝ መንፈሳዊ ግዴታችን ነው፡፡ እግዚአብሔር የተራቡትን የሚያበሉትን፤ የተራቆቱትን የሚያለብሱትን፤ የወደቁትን የሚያነሡትን፤ ለድሆች የሚቆረቆሩትን ይወዳል፤ ያከብራልም፡፡ እግዚአብሔር ለድሆች ያደረግነውን በእጥፍ ስለሚመልስልን ለድሆች በመስጠት ውስጥ በረከት እንጂ ኪሳራ የለም፡፡

### ፬. ምስጋና፡-

እግዚአብሔር በባሕርይው ምስጉን ነው፡፡ ምስጉኑን ማመስገን ያስባርካል፡፡ ምስጋና አክብረን የምንከበርበት የከንፈራችን መሥዋዕት ነው፡፡ ምስጋና የተፈጠርንበትና የተጠራንበት ዓላማ ነው፡፡ ምስጋናችን በፊቱ ንጹሕ አምልኮ እንዲሆን በተመስጦ፣ በአዲስ ቅኔ፣ በከበረ ዜማና በደስታ ማመስገን አለብን፡፡ አፋችን ሳይሆን ልባችን ሊዘምር ይገባል፡፡ እግዚአብሔር ከልብ ያልቀረበን አምልኮ ይጸየፋል፡፡ የሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት የከንፈራችን ፍሬ ነውና ስሙን በምስጋና ከፍ እናድርግ፡፡ ዕብ. ፲፫÷፲፭፡፡

## ማጠቃለያ

ንጹሕ አምልኮ በእግዚአብሔር የዘላለም እውነት ተመሥርተን እርሱን በማወቅ በመንፈስና በጽድቅ የምናቀርበው የልብ ፍሬ፤ የጽድቅ ሥርዓት ነው፡፡ ንጹሕ አምልኮ በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ መሥዋዕት ነው፡፡

## ተግባር

♦ መምህሩ ወጣቶች እግዚአብሔርን በቅድስናና በጽድቅ እንዲያመልኩ ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ትምህርተ አበው

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች በእውነተኛ አባቶች እውነተኛ ትምህርት እንዲመሠረቱ ማስገንዘብ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በውሸት ዕውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቅህ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ፡፡" ፩ጢሞ. ፮፥፳

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፪ጢሞ. ፫፥፲፬-፲፯ እና ፩ዮሐ. ፬፥፩-፫

## መግቢያ

ትምህርተ አበው (ዜና አበው) በተለያዩ ዘመናት የተነሡ የታላላቅ አባቶችን ትምህርት፣ ምክርና ስብከት ያጠቃልላል፡፡ ራሱን ያለ ምስክር ያልተወው እግዚአብሔር በየዘመናቱ ከትውልዶች መካከል የለያቸው ታላላቅ ቅዱሳን አባቶች ክብሩን በሕይወታቸው ገልጠዋል፤ የገለጠላቸውን እውቀት በደም ቀለም ጽፈዋል፡፡ የትምህርተ አበው መሠረት የእግዚአብሔር መግለጥና መገለጥ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

መጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈ በኋላ በዘመናቸው የተነሡ አባቶች የእግዚአብሔርን እውነት ሰብከዋል፤ ጽፈዋል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቅዱስ አትናቴዎስ፣ ቅዱስ ጢሞቴዎስ፣ ቅዱስ ቄርሎስ፣ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ፣ ቅዱስ አግናጥዮስ፣ ቅዱስ ያዕቆብ፣ ቅዱስ ዮሐንስ ዘአንጾኪያ፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫና ሌሎች ታላላቅ አባቶች እውነተኛ የሆነ ትምህርተ እግዚአብሔር ለትውልዱ ጽፈው አልፈዋል፡፡ የትምህርታቸው እውነተኛነት በቤተክርስቲያን ቀኖና በምንጫቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ተረጋግጧል፡፡ የአበው ትምህርት በመጻሕፍት ይገኛል፡፡ የአብዛኛዎቹ አባቶች ትምህርት በሃይማኖተ አበው ተመዝግቧል፡፡

***፩. የቅዱስ አትናቴዎስ ትምህርቶች፡-*** ነገረ ሥጋዌ (On the Incarnation of the Word)፣ **ሕይወተ እንጦንስ** (The Life of St. Anthony)፣ **የፋሲካ መልእክታት** (Different Paschal Letters)፣ **የአርዮስ ታሪክና ውግዘት** (Defense against the Arians and History of Arianism)**ናቸው፡፡** **የጸሎተ ሃይማኖት የመጀመሪያዎቹ ሰባት** አንቀጾች የቅዱስ አትናቴዎስ ረቂቅ ናቸው፡፡

***፪. የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርቶች፡-*** ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ አንድምታ (ማብራሪያዎች)፣ የጋብቻና የማኅበራዊ ሕይወት ስበከቶችን ያካታል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በአራቱ ወንጌላውያንና የጳውሎስ መልእክታት ላይ አንድምታ ጽፏል፡፡ ነገረ ሥጋዌ በሰፊው የተብራራው በእነዚህ ጽሑፎቹ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

***፫. የቅዱስ ቄርሎስ ትምህርቶች፡-*** የሙሴ መጻሕፍት፣ የነቢያት ትንቢት፣ የጥበብ መጻሕፍት፣ ወንጌል፣ የሮሜ፣ የዕብራውያንና የቆሮንቶስ መልእክታትን አንድምታ አዘጋጅቷል፡፡ ነገረ ክርስቶስንና ነገረ መንፈስ ቅዱስን የሚያብራሩ መጻሕፍትንና የትንሣኤ ደብዳቤዎችን ጽፏል፡፡

***፬. የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ትምህርቶች፡-*** አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ነው፡፡ የምስጋና መጻሕፍት ጽፏል፡፡ መጽሐፈ ሰዓታት፣ አርጋኖን፣ ውዳሴ መስቀልና መዓዛ ቅዳሴ እሱ የጻፋቸው የምስጋናና የአምልኮ መጻሕፍት ናቸው፡፡ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ምስጢረ ሥላሴንና ነገረ ሥጋዌን የሚያብራሩ ብዙ መጻሕፍት ጽፏል፡፡ ለምሳሌ መጽሐፈ ምስጢርን ማስታወስ ይቻላል፡፡

## ማጠቃለያ

በየዘመናቱ የተነሡ አባቶች ትውልድ የሚያንጽ ትምህርትና ስብከት ጽፈዋል፡፡ የአባቶች ትምህርት በሃይማኖተ አበው፣ በመጻሕፍተ መነኮሳት፣ በትርጓሜ መጻሕፍትና በስማቸው ይገኛሉ፡፡ የአበው ትምህርት ምንጭ የእግዚአብሔር መገለጥና መግለጥ (Revelation & Inspiration) ነው፡፡

## ተግባር

- *መምህሩ ወጣቶች ‹‹ሃይማኖተ አበው›› መጽሐፍ እንዲያነቡና የአንዱን አባት ትምህርት በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያድርግ፡፡*

www.zeorthodox.org

# የእግዚአብሔር መገለጥ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የተገለጠውን እንዲያምኑና ራሳቸውም በሕይወታቸው፣ በእምነታቸው፣ በምግባራቸው እንዲገልጡ ማስገንዘብ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ዓይኖቻችሁ ስለሚያዩ ብፁዓን ናቸው፡፡ ብዙዎች ነቢያትና ጻድቃን የምታዩትን ሊያዩ ተመኝተው አላዩምና፡፡" ማቴ. ፲፫÷፲፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዕብ. ፩÷፩-፫፣ ዮሐ. ፩÷፲፰ እና ፪ጴጥ. ፩÷፲፯-፲፱

## መግቢያ

መገለጥ በግእዙ "አስተርዮ" በግሪክኛው "ኤጲፋኒ" በእንግሊዘኛው "Revelation" ይባላል፡፡ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን በብዙ ዓይነትና በብዙ መንገድ ተገልጧል፡፡ እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠው ግን የመገለጦች ሁሉ ዘውድ ነው፡፡ እግዚአብሔር ራሱን ለፍጥረቱ ባይገልጥ ኖሮ አናውቀውም ነበር፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እግዚአብሔር ተገልጧል፤ ታይቷል፡፡ የማይታየው የታየው፤ ያልተገለጠው የተገለጠው በሐዲስ ኪዳን ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በሕልም፣ በራእይና በአረጋዊ ተገልጧል፡፡ በቃልም በተግባርም በረድኤቱና በጥበቃው ከሕዝቡ አለመለየቱን አሳይቷል፡፡ የብሉይ ኪዳን መገለጥ ፍጹም አልነበረም፤ ፍጹም ልጁ በሐዲስ ኪዳን ሲገለጥ መገለጡ እሙን ሆነ፡፡

***1. የእግዚአብሔር አጠቃላይ መገለጥ (Objective Revelation)፡-*** እግዚአብሔር በፍጥረቱና በሰው ልጅ ኅሊና ራሱን ይገልጣል፤ ህልውናውን ይናገራል፡፡ ይህ መገለጥ ለማያምኑትም ዕዳ ነው፡፡ ሰው ዓይኑን ገልጦ ተፈጥሮን በማየት፤ ጆሮውን ከፍቶ ኅሊናውን በማድመጥ የእግዚአብሔርን ህልውና ሊረዳና ሊያምን ይችላል፡፡ ድንቅ የሆነው የተፈጥሮ ህልውናና ውበት የእግዚአብሔርን መኖርና መገለጥ ያሳያል፡፡ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ በፍጥረቱ ይገለጣልና፡፡ የሰው ልጅ ኅሊና እግዚአብሔርን የመፈለግ፣ የመሻት፣ የመናፈቅ አለው፡፡ ስለዚህ ኅሊናውን የሚያዳምጥ ሁሉ ወደ ፈጣሪው ፊቱን ማዞሩ የታወቀ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ የእግዚአብሔርን አጠቃላይ መገለጥ አስተምሯል፡፡ "የማይታየው ባሕርይ . . . ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያል" በማለት እግዚአብሔር በፍጥረታቱ እንደሚታወቅ ይሰብካል፡፡ ሮሜ. ፩÷፳፩፡፡ **እግዚአብሔር ራሱን ያለ ምስክር አልተወም፡፡ ፍጥረታት የእግዚአብሔር ሕያዋን ምስክሮች** ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ በሚያደርገው መግቦትና ጥባቆት ይታወቃል፡፡ ይህም በህልም፣ በራእይ፣

ቃል በመናገር፣ ድምፁን በማሰማትና በጸጋው ስጦታ ይገለጻል፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ የኅሊናን ምስክርነት ሲያብራራ “ሕግ ባይኖራቸው . . . ኅሊናቸው ሲመሰክርላቸው አሳባቸውም እርስ በርስ ሲካሰስ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ” ብሏል፡፡ ሮሜ. ፪÷፲፫፡፡ **እግዚአብሔር በኅሊናችን ሰሌዳ እርሱን** እንድንፈልግና እንድናከብር የሚያዝዝ ሕግ በደም ቀለም ጽፏል፡፡ ስለዚህ ኢ-አማንያን የሚያመካኙበት ምክንያት የላቸውም፡፡

እግዚአብሔር ራሱን የመግለጥ ግዴታ ሳይኖርበት ስለ ሰው ፍቅር በፈቃዱ ራሱን በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ገለጠ፡፡ ተፈጥሮ የእግዚአብሔርን ታላቅነት፣ ከሃሊነትና ጥበብ ይገልጣል፡፡ ኅሊና ክፉና ደጉን የምንለይበት ዕውቀት በልባችን ያስቀመጠበት ሰሌዳ ነው፡፡

***2. የእግዚአብሔር መገለጥ በክርስቶስና በቃሉ (በመጽሐፍ ቅዱስ)፦*** ይህ መገለጥ ለአማኞች ብቻ የሚናገር በመሆኑ ግላዊ መገለጥ (Subjective Revelation) **ይባላል፡፡ ይህ መገለጥ እግዚአብሔር** በቃሉ በኩል ያደረገውን መገለጥ ያሳያል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ (ቃሉ) የእግዚአብሔር መገለጥ ማሳያ ነው፡፡ እግዚአብሔር በቃሉ ያናገራቸው መገለጡን በመጽሐፍ ገልጠዋልና መጽሐፍ ቅዱስ የመገለጦች ሁሉ መዝገብ ነው፡፡ ቃሉ የተገለጠውን እንድናምንና እንድንገልጥ ማንቂያ ነው፡፡

የክርስቶስ ኢየሱስ መገለጥ የመገለጦች ማሳያ በመሆኑ የእርሱ መገለጥ የመገለጦች ሁሉ ዘውድ ነው፡፡ የእርሱ መምጣት ለጥያቄዎቻችን ሁሉ መልስ አስገኝቷል፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ሆኖ ሳለ ዝቅ ብሎ በሰዎች መካከል ራሱን ገለጠ፡፡ የአባቱን መልክ አሳየን፤ አባቱን ገለጠ፤ ለሥጋውያን የሚወደውን የጽድቅ ሥርዓት እና ዘለዓለማዊ ምክሩን አስተማረ፡፡ የእርሱ መገለጥ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው፡፡ እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ነውና፡፡ ፊልጶስ “አብን አሳየንና ይበቃናል” ሲለው “እኔን ያየ አብን አይቷል” አለው፡፡ እውነት ነው ክርስቶስን ያየ እግዚአብሔርን አይቷል፡፡ “ያዩ ዓይኖቻችሁ ብፁዓን ናቸው” ማለቱ ለዚህ ነው፡፡ ማቴ. ፲፫÷፲፮፣ **ዮሐ.** ፩÷፲፰፣ ፲፬÷፰፡፡

ክርስቶስን የሚያምኑ የእግዚአብሔር ሙሉ መገለጥ ይገባቸዋል፡፡ የተገለጠው ዳግም ሲገለጥ ከእርሱ ጋር በክብር እንድንገለጥ ፈቃዱን እንፈጽም፡፡ ቆላ. ፫÷፩-፫፡፡ **በሐዲስ ኪዳን ሰማያት ተከፍተው ከመጋረጃ ባሻገር ያለውን የተሰወረውን አይተናል፡፡** የሥላሴ ሦስትነት ለዓለም የተገለጠው በዚህ ጊዜ ሰሌዳ ነው፡፡ ከዘመናት አስቀድሞ የተሰወረው የዘላለም ምክር ተገልጧል፡፡ በዘመን መጨረሻ በአንድያ ልጁ ተናግሮናልና፡፡ ዕብ. ፩÷፩-፫፡፡

***፫. የእግዚአብሔር መገለጥ ጥቅም፦*** የእግዚአብሔር መገለጥ ለእምነታችን፣ ለሕይወታችን፣ ለዕውቀታችን፣ ለስብከታችን፣ ለመጽሐፎቻችንና ለአገልግሎታችን ሁሉ መሠረት ነው፡፡ እግዚአብሔር በፈቃዱ ራሱን ባይገለጥ ኖሮ እምነታችን መሠረት፤ ሕይወታችን ተስፋ፤ ስብከታችን እውነት፤ መጻሕፍቶቻችን ዋቢ አይኖራቸውም ነበር፡፡ የእግዚአብሔር መገለጥ የሃይማኖት መሠረት ነው፡፡ እምነታችን የተገለጠው በመገለጡ ነውና፡፡ ያመንነው አምላካችን የታመነ እንደሆነ ተገልጦ ሲያድነን አይተናል፡፡ ስለዚህ ደኅንነትና መረጋጋት የተሰማንና ሳናይ ያመለክነው በሚታይና በሚዳሰስ ሥጋ በመገለጡ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

መጽሐፉ ቅዱስ የእግዚአብሔር መገለጥ ማሳያ እንደመሆኑ የቃሉ ጸሐፊዎች በመገለጡ መሠረት ላይ በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ ጽፈዋል፡፡ ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት በእግዚአብሔር መገለጥ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ስብከታችንም የቆመበት እውነት የእግዚአብሔር መገለጥ ነው፡፡ መገለጡ እምነትን ያጸናል፤ ሕይወታችንን ያለመልማል፤ ተስፋን ያጠነክራል፡፡

## ማጠቃለያ

የእግዚአብሔር መገለጥ የእምነት መሠረት ነው፡፡ እግዚአብሔር ሁለቱንም ኪዳናት የሰጠውና ያጸናው በመገለጥ ነው፡፡ እግዚአብሔር በሕልም፣ በራእይ፣ ቃል በመናገር፣ በብዙ መንገድና በብዙ ዓይነት ራሱን ገልጧል፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ግን የመገለጦች ሁሉ ማረጋገጫ ማኅተም (ዘውድ) ነው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ "የእግዚአብሔር መገለጥ በብሉይ ኪዳን" በሚል ርእስ ወጣቶች አጭር ጥናታዊ ጽሑፍ እንዲያዘጋጁና እንዲያቀርቡ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ስሜታችንን እንዴት መግዛት እንችላለን?

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ራሳቸውን እንዲገዙ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የመንፈስ ፍሬ . . . ራስን መግዛት ነው፡፡" ገላ. ፭÷፳፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ቆሮ. ፲÷፳፫

## መግቢያ

ሰው ስሜት ያለው ፍጡር ነው፡፡ ሰው ነጻ ፈቃድና ነጻ አእምሮ አለው፡፡ በውስጣችን ባለው መሻት ላይ ባለሥልጣን ሆነን ነጻ ፈቃዳችን ለኃጢአት ተገዥነት አይዳረግም፡፡ ራሳችንን ስንገዛ ስሜታችንን መቆጣጠር እንችላለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በሰው ውስጥ ብዙ ሐሳብ፣ የጋለ ስሜት፣ ክፉና ደግን የመምረጥ ነጻ ፈቃድና ወሳኝ ነጻ አእምሮ አለ፡፡ እነዚህ ነገሮች የሥጋ ወይም የመንፈስ ፈቃድ መገልገያ ክፉ ወይም ደግ መሥሪያ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስሜት በራሱ ኃጢአት አይደለም፡፡ ስሜትን ያለቦታው አለአግባብ ስንጠቀም፣ ለሥጋ ፍላጎትና ለዓይን አምሮት ስንገዛ ኃጢአት እንሠራለን፡፡ **፩ዮሐ. ፪÷፲፮**፡፡

ስሜታችንን ለበጎ ሥራ ማዋል እንችላለን፡፡ ውስጣችን ለነገሮች ሁሉ የሚሰጠው ምላሽ ስሜት ነው፡፡ ለምናየውና ለምንሰማው ነገር ስሜታችን መልስ አለው፡፡ ባየነውና በሰማነው ነገር ስሜታችን ክፉ ወይም መልካም መነሣሣት ይፈጥራል፡፡ ውጫዊ እንቅስቃሴያችን ወይም ድርጊታችን የሚመነጨው ከውስጣዊ ስሜት ነው፡፡ ስሜታችንን በድርጊት እንገልጻለን፡፡ ውስጣዊ ስሜታችን በውጫዊው ነገር ይቀሰቀሳል፡፡ ስለዚህ የክፉው ዓለም የኃጢአት ሥርዓት ስሜታችንን ተጠቅሞ ከጽድቅ ጎዳና እንዳያወጣን ራሳችንን መግዛት አለብን፡፡ ከውስጥ የሚመነጩ ክፉ መሻቶችን ማሸነፍ ይጠበቅብናል፡፡

- ስሜቶችን እንዴት መግዛት እችላለሁ?
- ሳያቋርጡ በመጸለይ፡፡ **፩ተሰ. ፭÷፲፯**፡፡
- ራስን በቅድስና በመጠበቅ፡፡ **፩ጢሞ. ፭÷፳፪**፡፡
- ጠላትን በመውደድ፤ ክፉን በመልካም በማሸነፍ፡፡ ማቴ. **፭÷፵፬**፡፡
- የባልንጀራን ጥቅም በማስቀደም፡፡ **፩ቆሮ. ፲÷፳፬**፡፡
- ራስን በመግዛት፡፡ ገላ. **፭÷፳፫**፡፡
- በልበ ሰፊነት ከጥፋት ለመዳን በማሰብ፡፡ **፩ጴጥ. ፫÷፲-፲፫**፡፡
- ለራስ በመጠንቀቅና ራስን በመፈተን፡፡ **፩ቆሮ. ፲፩÷፳፰፣ ፩ጢሞ. ፬÷፲፮**፡፡

www.zeorthodox.org

ስሜት ጤናማ እንደሆነ እንዲቀጥል በመንፈሳዊ ሕይወት መጠንከር አስፈላጊ ነው፡፡ ዘወትር በጸሎት ስንተጋ መንፈስ ቅዱስ ራስን የመግዛት ጸጋን ያጎናጽፈናል፡፡ ራሳችንን መግዛት ከቻልን ከክፉ ተጠብቀን ዓይኖቻችን መልካሙን ቀን ያያሉ፡፡ ሰው ለስሜቱ ከተገዛ እንስሳ ይሆናል፡፡ ዛሬ የስሜቱን ጥያቄ ሲያሟላ ለነገ ሕይወቱ ፀፀትና መከራ ያተርፋል፡፡ ስሜትን መግዛት ግን ከብዙ ርኩሰትና ጥፋት ያድናል፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወት ስንኖር የዘወትር ልምምዳችን ስሜትን ለመንፈስ ፈቃድ ለማስገዛት መትጋትና ራስን በጾምና በጸሎት በመጎሰም በመልካም ሥርዓት መመራት አለብን፡፡

## ማጠቃለያ

ስሜት በራሱ ኃጢአት አይደለም፡፡ ሆኖም የምናየውና የምንሰማው ነገር ለክፉ ወይም ለመልካም ሥራ ስሜታችን ሊያነቃን ይችላል፡፡ በነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ እንድንገዛ ተግተን መጸለይና ጸንተን መገኘት አለብን፡፡ የስሜት ፈቃድና ክፉ ምኞች እንዳያሸንፈን መጠንቀቅ ይጠበቅብናል፡፡ ስሜትን አለመግዛት ፍጻሜያችንን ያበላሻል፤ ሕይወትን መራራ ፍሬ እንድትሸከም ያደርጋል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ‹‹ራስን መግዛት የሚያስችል የመንፈሳዊ ኑሮ ጥበብ›› በሚል ርእስ ወጣቶችን ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የቅስና አገልግሎት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ክብረ ክህነትን እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** *"የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻዎች* እሰጥሃለሁ፡፡" ማቴ. ፲፮÷፲፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘኁ. ፫÷፩-፲፣ ፩ጴጥ. ፪÷፱ እና ራእ. ፩÷፮

## መግቢያ

ቄስ (ካህን) በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሆኖ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ ነው፡፡ ካህናት ከሰዎች መካከል በእግዚአብሔር የተመረጡ አገልጋዮች ናቸው፡፡ ካህን ሰዎች በክርስቲያናዊ ሕይወት ጸንተው በጽድቅ ሥርዓት እንዲጓዙ የሚተጋ የእግዚአብሔር ልኡክ /ወኪል/ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እግዚአብሔር ሰውን የመንግሥቱ ወራሽ እንዲሆን አክብሮ ፈጥሮታል፡፡ ሰው የአምላኩን ክብርና የተቀደሰ ሕይወት ትቶ ወደ ኃጢአት አዘነበለ፡፡ እግዚአብሔር ወደጥፋት ያፈገፈጉትን ወደ ሕይወት ለመመለስ፤ በእርሱና በሕዝቡ መካከል የሚሥሩ አገልጋዮችን ከሰዎች መካከል ለሰው ጥቅም መረጠ፡፡

የቅስና (የክህነት) አገልግሎት ብዙ ነው፡፡ ካህናት የብዙ መከር ሠራተኞች ናቸው፡፡ የቅስና አገልግሎት እግዚአብሔርን በማክበር የምንከብርበት ሕይወት፤ ለእግዚአብሔር ክብርና ለሰው ጥቅም የምንኖርበት አገልግሎት ነው፡፡ የካህናት ርስት እግዚአብሔር ነው፡፡ ካህናት ለርስታቸው ይሠራሉ፡፡

***1. የክህነት (የቅስና) አገልግሎት በብሉይ ኪዳን፡-*** የብሉይ ኪዳን ካህናት ሌዊና ልጆቹ (አሮናውያን) ነበሩ፡፡ የብሉይ ኪዳን ክህነት በዘር የሚወረስ ነበር፡፡ የብሉይ ኪዳን ካህናት ዋና ተግባር መሥዋዕት መሠዋት ነበር፡፡ ዘጸ. ፳፰÷፩፡፡ አሮንና ልጆቹ ልዩ ልብስ ለብሰው በዘይት ተቀብተው ይሾሙ ነበር፡፡ ዘጸ. ፳፰÷፵፡፡ **የአሮንና የልጆቹ ተግባር በመቅደስ** ማገልገል፣ ሕግን ለሕዝቡ ማስተማር፣ በኡሪምና በቱሚም የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጠየቅና መርገም (ተላላፊ በሽታ) ያለባቸውን መለየት ነበር፡፡ ዘጸ. ፴÷፲፯-፳፩፣ **ዘኁ. ፲፮÷፵፣ ፪ዜና. ፲፫÷፫፣ ዘጸ. ፳፰÷"** እና ዘሌ. ፲፫÷፩-፫፡፡

የቤተ መቅደሱ አገልግሎታቸው ዕለታዊ፣ ሳምንታዊና ዓመታዊ ነበር፡፡ ዕለታዊ አገልግሎት ጧትና ማታ የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዋት፣ በቅድስት መብራቶችን ማብራት፣ ዕጣን ማጠንና የሰዎችን መብዓ መቀበል ነበር፡፡ ሳምንታዊ አገልግሎት፡- በየጊዜው የሰንበት ዕለት ዐሥራ ሁለት ኅብስት በገበታው ላይ የማኖር አገልግሎት ነበር፡፡ ዓመታዊ አገልግሎት፡- በማስተሥሪያ ቀን ልዩ

www.zoorthodox.org

ሥርዓትን የመፈጸም አገልግሎት ነው፡፡ ዘጸ. ፳፱÷፴፰፣ **ዘሌ.** ፳፬÷፩-፱፤ ፲፮፡፡

***2. የቅስና (የክህነት) አገልግሎት በሐዲስ ኪዳን፦*** የሐዲስ ኪዳን ሥርዓተ ክህነት በዘርና በቀለም አይወሰንም፡፡ የሐዲስ ኪዳን የቅስና አገልግሎት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ምርጫ (ጥሪ) ነው፡፡ የሐዲስ ኪዳን የክህነት (የቅስና) አገልግሎት ማዳኑን መመስከር፣ ማስተማር፣ ማጥመቅ፣ መቀደስ፣ ማስተዳደር፣ ማንጻትና የንሰሐ ሥርዓት መፈጸም ናቸው፡፡ በቤተክርስቲያናችን ምስጢራተ ቤተክርስቲያን የሚፈጸሙት በአባቶች ካህናት ነው፡፡

በሐዲስ ኪዳን በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ከሕዝቡ መካከል የሚመረጡት አገልጋዮች በማዕረገ ክህነት ሆነው እግዚአብሔርንና ሰውን ያገለግላሉ፡፡ የክህነት መዓርጋት ዲቁና፣ ቅስናና ጵጵስና ናቸው፡፡ ሐዋርያት ሰባት ዲያቆናትን መርጠው ሸመዋል ሐዋ. ፮÷፩-፯፡፡

የሐዲስ ኪዳን የክህነት መሥፈርት ዘር ሳይሆን የሕይወት ቅድስናና የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታ ውጤት ነው፡፡ የክህነት መስፈርት በቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት ተገናዝቧል፡፡ **፩ጢሞ. ፫÷፩-፲፫፣ ቲቶ. ፫÷፪-፯፡፡ የቅስና ሕይወት ከነገር፣ ከሱስ፣** ከመጠጥ፣ ከዝሙት፣ ከፍቅረ ንዋይ፣ ከትዕቢት፣ ከስስት፣ ከክህደትና ከክፋት መራቅን ይጠይቃል፡፡ ቅስና ለመቀበል ወይ በትዳር መወሰን ወይ መመንኮስ ያስፈልጋል፡፡ የካህናት (የቀሳውስት) አገልግሎት መንጋውን መንከባከብና መጠበቅ ነው፡፡ በቅዱስ ጴጥሮስ አማካኝነት ሓላፊነት ተስጥቷቸዋልና፡፡ ዮሐ. **፳፩÷፲፭-፲፰፣ ሐዋ. ፳፰÷፳** እና **፩ጴጥ. ፭÷፪-፬፡፡ ቀሳውስት የእምነታቸውን ሊቀ** ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን አብነትና ኃይል በማድረግ መንጋውን ከጉስቁልናና ከነጣቂ ተኩላ መጠበቅ አለባቸው፡፡

## ማጠቃለያ

የቅስና አገልግሎት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሰላማዊ ግንኙነት እንዲቀጥል የምንሠራበት የሕይወት አገልግሎት ነው፡፡ በሁለቱም ኪዳናት የካህናት አገልግሎት የተገለጠ ነው፡፡ ቀሳውስት የሰማያዊ መንግሥት ሠራተኞች ናቸው፡፡

## ተግባር

✍መምህሩ ወጣቶች ፍቅረ ክህነት እንዲያድርባቸው ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የከበረ ደም

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም የሐዲስ ኪዳን ጽኑ መሠረት የስርየታችን ዋጋ የዘለዓለማዊ ሕይወታችን ዋስትና መሆኑን ወጣቶች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻል፡፡" ፩ዮሐ. ፩÷፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዕብ. ፱÷፲፪-፳፰ እና ራእ. ፯÷፲፫፤፲፪÷፲፩

## መግቢያ

ደም ለሥጋዊ ሕይወታችን ከሚያስፈልጉት ዋና ዋና መሠረታዊ ነገሮች አንደኛው ነው፡፡ የደም ዝውውር ሲቆም የሥጋ ሕይወት ይቆማል፡፡ በሃይማኖታዊውም ሥርዓት ደም ሁለቱም ኪዳናት የጸኑበት ማኅተም ነው፡፡ ፊተኛው ኪዳን በእንስሳት ደም፤ ሐዲሱ ኪዳን ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ጸንተዋል፡፡ ደም ሳይፈስ ስርየት የለምና፡፡ ዕብ. ፱÷፳፪፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

***፩. ደም በሥጋዊ ሕይወት፡-***

ደም ሰውነታችን ጸንቶ ሕይወታችን እንዲቀጥል የሚያደርግ፤ ከልብ ወደ ተለያዩ የሰውነት ክፍሎች የሚረጭ፤ በደም ሥሮች አማካኝነት ተዘዋውሮ እየተዳረሰ ሰውነትን የሚዋጅና ከምግብ የሚገኝ የሰውነታችን አንደኛው ፈሳሽ አካል ነው፡፡ የደም ዝውውር ከቆመ የሰው እንቅስቃሴ ይገታል፡፡ ሥጋ በሕይወት የሚቆየው በውስጡ ባለው ደም ነው፡፡ ሰውነታችን በቂ ደም ይፈልጋል፡፡ ይህንም ደም ከተለያዩ ምግቦች ያከማቻል፡፡ ደም በውስጡ የተለያየ ቅርጽና ዓይነት ያላቸው ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰጡ ሴሎች አሉት፡፡ ነጭ የደም ሴል በሽታን ሲከላከል፤ ቀይ የደም ሴል አየርና ምግብን ያጓጉዛል፡፡

***፪. ደም በመጽሐፍ ቅዱስ፡-***

www.zeorthodox.org

በመጽሐፍ ቅዱስ ደም ሞትና ሕይወትን ያመለክታል፡፡ ዘኁ. ፴፫÷፲፱፤ ነገ. ፪÷፴፪-፴፫፡፡ **በሰውነት ውስጥ *የሚገኘው*** ደም የሚወክለው ሕይወትን በመሆኑ የፈሰሰ ደም የጠፋ ሕይወትን (ሞትን) ይወክላል፡፡

የብሉይ ኪዳን የስርየት ሥርዓት በእንስሶች ደም ነበር፡፡ በደምና በሕይወት መካከል የጸና ትስስር ስላለ እግዚአብሔር የእንስሶችን ደም ለኃጢአት ስርየት እንዲውል አደረገ፡፡ ከዚህ የተነሣ ደም መብላት የተከለከለ ነው፡፡ በኃጢአተኛው ምትክ የእንስሳት ደም ፈሶ በስርየት መከደኛው ይረጭ ነበር፡፡ ዘሌ. ፲፯÷፲፩፡፡

ደም የሕይወት ምንጭ ነው፡፡ ደም የኪዳናቱ ማረጋገጫ ማኅተም ነው፡፡ የብሉይ ኪዳኑ ሊቀ ካህናት በበጎች፣ በፍየሎችና በጥጆች ደም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባ ነበር፡፡ የሕዝቡን ኃጢአት ለመደምሰስ ደሙን በስርየት መክደኛው ይረጭ ነበር፡፡ ፊተኛው ኪዳን እንኳ ያለ ደም አልተመረቀም አልተረጋገጠም፡፡

ሙሴ የኪዳኑን ደም ሕዝቡን በመርጨት ቃልኪዳኑን አጽንቷል፡፡ ዕብ. ፱÷፲፪-፳፩፡፡ **የክርቶስ ደም ከሞተ ሕሊና** ያነጻል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በገዛ ደሙ ሕዝቡን ቀድሷል፡፡ የአብርሃምን ዘር ይዞ፤ ሥጋና ደም ከፍሎ፤ ቀዳሹ ከተቀዳሾቹ መካከል ተወልዶ፤ ያለ በደሉ ስለ ኃጢአተኞች ደሙን አፍስሶ፤ የዘላለም ስርየት ሰጥቷል፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም የሞትን ኃይል ሰብሯል፡፡ ከኃጢአት ሁሉ ያነጻል፡፡ የፋሲካውን በግ ደም አይቶ ሞት የእስራኤልን በኩር እንዳለፈ ሁሉ የክርስቶስ ደም የታተመበትን ሕይወት ሁለተኛ ሞት አይነካውም፡፡ **፩ዮሐ. ፩÷፯፣ ኤፌ. ፩÷፯** እና ሐዋ. ፳÷፳፰፡፡

ቤተክርስቲያን ተቀድሳ የተመሠረተችው በክርስቶስ ደም ነው፡፡ ኤፌ. ፫÷፳፮፡፡ **የክርስቶስ ደም ባለሥልጣን** ነው፡፡ የሞትን ደጅ ይሰብራል፡፡ በደሙ ማኅተም የታተምን ሁሉ የዘለዓለማዊ ሕይወትን ደጅ የማንኳኳት ሥልጣን አለን፡፡ ጥጦስ የመልአኩን ሰይፍ አልፎ ገነትን የወረሰው በደሙ ማኅተም ነው፡፡ ሰማዕታት ዲያብሎስን ድል የነሡት በበጉ (ከኢየሱስ) ደም ነው፡፡ ራእ. ፲፪÷፲፩፡፡ **ታላቁን መከራ ያለፉት ብፁዓን** በደሙ ኃይል ነው፡፡ ራእ. ፯÷፲፬፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ኃይል በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን የጠብ ግድግዳ ሰባብሮአል፤ መጋረጃውን ሰንጥቆ ለሁለት በመከፈል ግርጃውን ገፎታል፤ የዲያብሎስን ዝናር አስጥሎአል፡፡ ሐዲስ ኪዳን የጸናው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው፡፡ ማቴ. ፳፮÷፳፮፡፡ **ይህ ደም የምሕረት ደም ነው**፡፡ የአቤልና ሰማዕታት ደም በግፍ ፈሶ ለፍርድ የሚጮህ ደምነው፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ግን በግፍ ቢፈስም ምሕረትን ይናገራል፡፡ ራእ. ፮÷፲፡፡

## ማጠቃለያ

ደም የሕይወት ምንጭ ነው፡፡ የሥጋ ሕይወት ቀጣይነት የሚረጋገጠው በደም እንደሆነ ሁሉ መንፈሳዊ ሕይወት ኃይልን የሚታጠቀው በበጉ ደም ነው፡፡ ስለሁላችን የታረደው የበጉ ደም የምስክሮቹ ኃይል፣ የብፁዓን ማኅተም፤ የአማኞች ኃጢአት መደምሰሻና መንግሥቱን መውረሻ ነው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች የሁለቱን ኪዳናት መሥዋዕት እያነጻጸሩ እንዲያብራሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ንስሐ መግባት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የንስሐ ሕይወትን እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** **"ኃጢአት የለብንም ብንል** ራሳችንን እናስታለን፡፡ በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው፡፡" **፩ዮሐ. ፩÷፯-፲**

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ምሳ. ፳፰÷፲፫ እና ማቴ. ፫÷፰

## መግቢያ

ንስሐ "ነስሐ" ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ቃል ሲሆን መፀፀት መመለስ ማለት ነው፡፡ ንስሐ በበደላችን በመፀፀት ወደ እግዚአብሔር በፍጹም ልብ የምንመለስበት ሕይወት ነው፡፡ ንስሐ የልቡና ትንሣኤ ነው፡፡ ንስሐ እግዚአብሔር የምሕረት እጁን ለኃጢአን የዘረጋበት የዕርቅ ሥርዓት ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

***የንስሐ አስፈላጊነት፡-*** ንስሐ የእግዚአብሔርን የምሕረት ፊት ለማየት ዳግመኛ ዕድል የምናገኝበት ሕይወት ነው፡፡ ንስሐ ባይኖር ወድቀንና ጠፍተን እንቀር ነበር፡፡ መጥፋታችንን የማይፈልገው እና በመመለሳችን የሚደሰተው አምላካችን ከውድቀታችን የምንነሣበትንና ከኃጢአታችን የምንነፃበትን ሥርዓት ሰጠን፡፡ ንስሐ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት በዘላቂነት ለማጠንከር፣ ለልቡናችን ሰላም፣ ለጽድቅ ሥራና ዲያብሎስን ለማሳፈር ያስፈልገናል፡፡ ከአዳም የወረስነው በኃጢአት የተጎሳቆለ ሰውነት ደካማ በመሆኑና በክፉ ምኞቱም እየተነዳ ወደ ጥፋት ስለሚመራን እግዚአብሔር የሰጠን የንስሐ ጸጋ ያስፈልገናል፡፡

***ንስሐ ለመግባት ምን ማድረግ አለብኝ?***

፩. ራሳችንን በመፈተን /በመመርመር/፣ ኃጢአታችንን በማመን ዳግም ወደ ኃጢአት ላለመመላስ በመወሰን፡፡

፪. በደላችንን የሚደመስስ፣ ኃጢአታችንን ይቅር የሚል፣ በድካማችን የሚራራ ሊቀካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳለን በማመን ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት በመቅረብ፡፡ ዕብ. ፬÷፲፬-፲፮

፫. የእረኞች እረኛ የጌቶች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የክህነት ጸጋ ወደ ሰጣቸው አባቶች በመቅረብ ሳንደብቅ ኃጢአትን በመናዘዝ፡፡

የበደልናቸውን ይቅርታ በመጠየቅና የኃጢአታችንን ቅጣት (ቀኖና) በደስታ በመፈጸም፡፡ (ስለ ኃጢአታችን በጸጋ ራስን በመኀሰም)

www.zeorthodox.org

የኃጢአት ስርየት እንዳገኘን ፈጽሞ በማመን፡፡

የጽድቅ ሥራን በመንፈስ ቅዱስ በመታገዝ መሥራት በመጀመር በንስሐ ሕይወት እየተመላለስን ኃጢአትን ድል መንሣት ይጠበቅብናል፡፡

## ማጠቃለያ

ንስሐ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ፤ ከክፋት ወደ ደግነት፤ ከጨለማ ወደ ብርሃን የምንሸጋገርበትን የእግዚብሔርን ጸጋ (ርዳታ) የምናገኝበት ሕይወት ነው፡፡ ንስሐ ከእግዚአብሔር ጋር የምንታረቅበት ዕድል፤ የልቡና ትንሣኤ፤ የአዲስ ሕይወት መጀመሪያ ነው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ራሳቸውን በመፈተን ንስሐ እንዲገቡ ወጣቶችን ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ደጉ ሳምራዊ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ያለ አድልዎ ሌሎችን እንዲያገለግሉ ማሳሰብ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ" ሉቃ. ፲÷፴፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፳÷፵፫-፵፰ እና ሉቃ. ፲÷፳፱-፴፯

## መግቢያ

ሳምራውያን የአይሁድና የአሕዛብ ቅልቅል ዘሮች ናቸው፡፡ በሰሜን እስራኤል የነበሩት ዐሥሩ ነገደ እስራኤል በስልምናሶር ተማርከው ወደ አሦር ሄዱ፡፡ ከአሦራዊያን ጋር ጋብቻ ስለመሠረቱ ማንነታቸውን አጡ፡፡ ስለዚህ ሳምራውያን ተባሉ፡፡ በገሪዛን ተራራ መቅደስ ሠርተው እግዚአብሔርን እያመለኩ ይኖሩ ነበር፡፡ ሳምራውያን የሙሴን መጻሕፍት ብቻ ይቀበላሉ፡፡ አይሁድ ሳምራውያንን ይንቋቸው ስለነበረ በአይሁድና በሳምራውያን መካከል ዘመን የተሻገረ ጥላቻ አለ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

***፩. የሕግ አዋቂው ጥያቄና የኢየሱስ ክርስቶስ መልስ፡-*** በአንድ ወቅት አንድ ሕግ አዋቂ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን "ባልንጀራዬ ማን ነው?" ብሎ ጠየቀው፡፡ የጥያቄዎች ሁሉ መልስና የችግሮች ሁሉ መፍቻ ቁልፍ ባለቤት ነውና እንዲህ ሲል መለሰለት፡፡ "አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ሲወርድ በሽፍቶች እጅ ወደቀ፡፡ ደበደቡት፤ ገፈፉት፤ በሞትና በሕይወት መካከል ትተውት ሄዱ፡፡ አንድ ካህንና አንድ ሌዋዊ በዚያ ሲያልፉ አይተውት ገለል ብለው አለፉ፡፡ አንድ ሳምራዊ ግን በዚያ ሲሄድ አይቶት አዘነለት፤ ቀርቦም ዘይትና የወይን ጠጅ በቁስሎቹ ላይ አፍስሶ አሰረለት፡፡ በራሱ አህያ አስቀምጦት ወደ እንግዶች ማረፊያ አመጣው፤ ጠበቀውም፡፡ በማግሥቱም ሁለት ዲናር አውጥቶ ለባለቤቱ ሰጠና፡- ከዚህ በላይ የምትከስረውን ስመለስ እከፍልሃለሁና ጠብቀው፡፡ አለው፡፡ ከእነዚህ ከሦስቱ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ባልንጀራ የሆነው ማንኛው ይመስልሃል?" ሉቃ.፲÷፴-፴፯ አለው፡፡ ጌታም "ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ" አለው፡፡

**፪. የታሪኩ ምሳሌያዊነት (ትርጓሜ)**

www.zeorthodox.org

***፪.፩. ኢየሩሳሌም፡-*** ኢየሩሳሌም ማለት የሰላም ከተማ ማለት ነው፡፡ ኢየሩሳሌም የአምልኮ ማዕከል የቅዱሳን ሰፈር ናት፡፡ ኢየሩሳሌም የኤደን ገነት ምሳሌ፤ የልዕልና፣ የጽድቅና የክብር ምሳሌ ናት፡፡ ኢየሩሳሌም የቤተክርስቲያን ተምሳሌት ናት፡፡

***፪.፪. ኢያሪኮ፡-*** ኢያሪኮ የጨረቃ ከተማ፤ የሽፍቶች መንደር፤ የባዕድ አምልኮ ማዕከል ናት፡፡ ኢያሪኮ የኃጢአት፣ የከፋው ዓለም ምሳሌ፤ የአጋንንት ምርኮኞች ሰፈር ናት፡፡

***፪.፫. አንድ ሰው፡-*** አንድ ሰው የተባለው አዳም (የሰው ልጅ) ነው፡፡

***፪.፬. ወንበዴዎች፡-*** የአጋንንት ምሳሌዎች ናቸው፡፡ አጋንንት (ሰይጣን) የሰውን ልጅ (አዳምን) በሚያባብል ቃሉና መልካም በሚመስል ክፋቱ ከቅድስና ለይቶ፣ የጸጋ ልብሱን ገፎ፣ ኀሊናውን በበደል ሰብሮ በታሪክ የውድቀትና የጉስቁልና ጎዳና ላይ ትቶት ሄደ፡፡

***፪.፭. ሌዋዊና ካህን፡-*** የሕግና የነቢያት ምሳሌዎች ናቸው፡፡ በኩነኔ ተይዞ በአጋንንት ግዛት የወደቀውን አዳምን (የሰውን ልጅ) የሌዋውያን ካህናት መሥዋዕትና የካህናት መብዓ አላዳነውም፡፡

***፪.፮. አንድ ሳምራዊ፡-*** በአጋንንት የተንኮል በትር የቆሰለውን ሰው ከውርደት ወደ ክብር፤ ከሞት ወደ ሕይወት፤ ከጨለማ ወደ ብርሃን፤ የመለሰው ደጉ ሳምራዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በታሪክ ጎዳና የወደቀውን ሰው በጸጋው ያነሣው፣ ዘይትና የወይን ጠጅ የተባለ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደሙን የሰጠው፣ ከክብሩ ዙፋን ወርዶ ነፍሳችንን በከበረ ሰረገላ ያስቀመጠው ደጉ ሳምራዊ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡፡

***፪.፯. ሁለት ዲናር፡-*** የተባሉ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን ናቸው፡፡

***፪.፰. የእንግዶች ማደሪያ፡-*** የተባለች ቤተክርስቲያን ናት፡፡ ለአገልጋዮቹ አደራ ስጠን፡፡ ዋጋቸውንም ደግሞ ሲመጣ ይከፍላቸዋል፡፡

***፫. የታሪኩ ጭብጥ፡-*** ክርስትና የወደቁትን የምናነሣበት፣ የዛሉትን ጉልበቶች የምናጠነክርበት፣ የደከሙትን የምናበረታበትና ሰው ለሌላቸው የምንቆምበት ሃይማኖት ነው፡፡ የእኛ ርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሁሉ ጓደኞቻችን ናቸውና እንደ ሳምራዊ ዘርና ቀለም ሳንለይ የጥላቻ ድንበር ሳይከልለን ልንረዳቸው ይገባል፡፡ ደግነት ከክርስቶስ የተማርነው የእምነታችን መገለጫ ምግባር ነው፡፡ ደግነታችን ድንበር መሻገር አለበት፡፡ የተቸገሩትን እያየን ማለፍ የለብንም፡፡

## ማጠቃለያ

ደጉ ሳምራዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ሰውን ከውድቀት ወደ ስኬት፤ ከሞት ወደ ሕይወት፤ ከውርደት ወደ ክብር፤ ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን ያሻገረው እርሱ ነው፡፡ የሚያምኑት ሁሉ የወደቁትን በማንሣት ፍለጋውን ይከተላሉ፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶችን በጎ እንዲያደርጉ ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ጥምቀት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶችን ስለ ምስጢረ ጥምቀት ማሳወቅ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም፡፡" ዮሐ. ፫÷፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሮሜ. ፮÷፫፣ ገላ. ፫÷፳፯ እና ኤፌ. ፬÷፬

## መግቢያ

ክርስቲያናዊ ጥምቀት በክርስቶስ የታዘዘ የሕይወት ሥርዓት ነው፡፡ የሥርዓቱ መሥራችና ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም ተጠምቋል፡፡ ሰው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ማመኑን ለመመስከርና ክርስቶስ የፈጸመውን ጽድቅ ለመቀበል በሰው ሁሉ ፊት ይጠመቃል፡፡ ጥምቀት የእግዚአብሔርን መንግሥት ግዛት የምንረግጥበት፣ በዘላለም የሕይወት ቃል ማኅተም የምንታተምበት፣ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆንን ሥልጣን የምንቀበልበትና የማያረጅውን የጽድቅ ልብስ ኢየሱስ ክርስቶስን የምንለብስበት የጽድቅ ሥርዓት ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጥምቀት ከሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን መካከል አንዱ ምስጢር ነው፡፡ ጥምቀት ወደ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን መግቢያ በር ነው፡፡ የክርስቶስ ትምህርት ለደረሳቸውና እርሱን ማመን ለሚፈልጉ ጥምቀት ማኅተም ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የመንግሥቱን ወንጌል ሲሰብክ፤ ወንጌሉን የተቀበሉና ወደ መንግሥቱ የመጡ ሰዎች የእምነታቸውን እውነተኛነት በማረጋገጥ ያሳዩት ንስሐ ገብተው በመጠመቅ ነበር፡፡ ዮሐ. ፬÷፩-፪፡፡ **ከሙታን ከተነሣ በኋላ የመንግሥቱን** የምሥራችና የማዳኑን ዜና በዓለም ሁሉ እንዲሰብኩና ያመኑትን በስመ ሥላሴ እንዲያጠምቁ ደቀ መዛሙርቱን አዟል፡፡ ማቴ. ፳፰÷፲፱፡፡ ***የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የመጀመሪያዎቹ*** አማኞች መጠመቃቸውን ይመሠክራል፡፡ የጳውሎስ ትምህርት ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር መተባበራችንን የምንገልጽበት ለኃጢአት ሞተን ከክርስቶስ ጋር በአዲስ ሕይወት መነሣታችንን የምናሳይበትና ክርስቶስን የምንለብስበት የሕይወት ሥርዓት ነው፡፡ ሮሜ. ፮÷፫-፲፩፣ **ቆላ. ፪÷፲፪** እና ገላ. ፫÷፳፯፡፡

www.zeorthodox.org

**፩. የጥምቀት ምሳሌዎች በብሉይ ኪዳን፡-** ለጥምቀት ምሳሌ የሚሆኑ ጥላ ታሪኮች በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተመዝግበዋል፡፡ የኖህ መርከብ፣ የግዝረት ሥርዓት፣ የእስራኤላውያን ቀይ ባሕርን መሻገርና የማንጻት ሥርዓት የጥምቀት ምሳሌዎች ናቸው፡፡ **፩ጴጥ. ፫÷፳፣ ፩ቆሮ. ፲÷፩-፪** እና ሐዋ. **፪÷፴፰**፡፡

***፩.፩. የኖህ መርከብ፡-*** ከፋትና ኃጢአት ምድርን በሞላበት ጊዜ ኖህ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አክብሮ መርከብን በእምነት

አዘጋጀ፡፡ የጥፋት ውኃም በመጣ ጊዜ ወደ መርከቡ ገብቶ ከሞት ዳነ፡፡ ኖህና ቤተሰቡ የምእመናን ምሳሌ፤ መርከብ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ አማኞች ወደ መርከባቸው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ማሠማሪያ በጥምቀት በር ይገባሉ፡፡ የሞትና የጥፋት ኃይል አይነካቸውም፡፡ ወደ መርከቡ ያልገቡትና ያላመኑት የእግዚአብሔር ፍርድ ይጠብቃቸዋል፡፡ ዕብ. ፲÷፳፯፡፡ **እንደ ኖህ ማመናችንን በሥራ** /በተግባር/ ለማሳየት የደኅንነትን ጸጋ መቀበል ወደ ምንችልበት መለኮታዊ ሥርዓት ወደ ጥምቀት መቅረብ አለብን፡፡ የተጠመቀ የጸና የተስፋ ቃል፣ የኃጢአት ስርየትና የመንፈስ ቅዱስን የጸጋ ስጦታዎች ይቀበላል፡፡ ሐዋ. ፪÷፴፰፡፡

***፩.፪. የግዝረት ምልክት፦*** እግዚአብሔር ከወዳጆቹ ጋር ለሚያደርገው የማይታይ ቃል ኪዳን ምልክቱ ግዝረት ነበር፡፡ ዘፍ. ፲፯÷፯-፲፬፡፡ **በሐዲስ ኪዳን እግዚአብሔር** ከአማኞች ጋር ላለው የጸና ግንኙነት የቃል ኪዳኑ ምልክት ጥምቀት ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ሕዝብ ለመባል መገረዝ እንደሚያስፈልግ የክርስቶስ አካል ወደ ሆነችው ቤተክርስቲያን ለመግባት ጥምቀት ያስፈልጋል፡፡

***፩.፫. የእስራኤል ባሕረ ኤርትራን መሻገር፦*** እስራኤላውያን ባሕሩን ሲሻገሩ ተጠመቁ፡፡ ፩ቆሮ. ፲÷፩-፪፡፡ **ከፈርዖን ግዛት ወጥተው የእግዚአብሔርን** ግዛት ለመርገጣቸው ምልክቱ ይህ ነበር፡፡ እኛም ከሰይጣን የጨለማ ግዛት ወጥተን የብርሃን ልጆች እንድንሆን እና በብርሃኑ እንድንመላለስ መጠመቅ ያስፈልገናል፡፡

***፩.፬. የማንጻት ሥርዓት፦*** የጊደር ሥጋና ደም ቆዳና አንጀት በካህኑ ፊት ተቃጥሎ በንጹሕ ሥፍራ ከሰፈር ውጭ ይቀመጥና ከአመዱ ጥቂት ወስዶ ከንጹሕ የምንጭ ውኃ ጋር ይረጫል፤ ኃጢአትን ያርቃል፡፡ ዘኊ. ፲፱÷፩-፳፪፡፡ **የተረጨበት ውኃ የጥምቀት ምሳሌ** ነው፡፡ ሮሜ. ፮÷፬፡፡

**፪. የጥምቀት ዓይነቶች፡-** የውኃ፣ የደም፣ የእሳትና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ይባላሉ፡፡ የውኃ ጥምቀት እኛ የተጠመቅንበት ነው፡፡ የደምና የእሳት ጥምቀት ሰማዕታት የተጠመቁበት ሲሆን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሐዋርያት በጸጋ የተትረፈረፉበትን የጰራቅሊጦስ ሥርዓት ይገልጻል፡፡ ሐዋ. ፪÷፪-፭፡፡

**፫. የጥምቀት አስፈላጊነት፡-** ጥምቀት የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማየት፣ ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ጋር ለመተባበር፣ ከኃጢአት ለመንጻት፣ ክርስቶስን ለመልበስ፣ የጸጋ ስጦታዎችን ለመቀበልና የአማኞች ጉባኤ አካል ለመሆን ያስፈልጋል፡፡

**፬. ጥምቀት በማን ስም ይፈጸማል?** ጥምቀት በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም ይከናወናል፡፡ ማቴ. ፳፰÷፳፡፡ **ክርስቲያን አንድ አምላክ** በሦስት ፍጹማን አካላት ብሎ በማመን በሥመ ሥላሴ ይጠመቃል፡፡

**፭. ጥምቀት መቼ?፡-** በቤተክርስቲያን ሥርዓት ወንድ በአርባ ቀኑ ሴት በሰማንያ ቀኗ ይጠመቃሉ፡፡ ክርስቶስ በሠላሳ ዘመኑ የተጠመቀው የአዳምን ልጅነት ለመመለስና የክህነት ሥራውን ለመጀመር ነበር፤ የአሮን ልጆች የሚሾሙት በሠላሳ ዘመናቸው ነበርና፡፡ ዘሌ. ፲፪÷፮-፰፡፡

www.zeorthodox.org

**፮. የሚያጠምቀው ማነው?** በቤተክርስቲያን ሥርዓት የማጥመቅ ሥልጣን የተሰጠው ለካህናት አባቶች ነው፡፡ ክርስቶስ ሂዱ አጥምቁ የሚል ትእዛዝ ለሾማቸው ደቀመዛሙርት ሰጥቷልና፡፡

## ማጠቃለያ

ጥምቀት የሰው አዲሱ የኑሮ ሥርዓት መከፉቻ ቁልፍ ነው፡፡ ጥምቀት የእግዚአብሔርን መንግስት ለማየት የሚያስችል ጸጋ፤ ክርስቶስን ማመናችንን የምንመሠክርበት፤ ከሞትና ከትንሣኤው በመተባበር እርሱን የምንለብስበት የሕይወት ሥርዓት ነው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ "ትምህርተ ጥምቀት በቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት" በሚል ርዕስ ወጣቶች አጭር ጥናታዊ ጽሑፍ እንዲያዘጋጁ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# የትንሣኤ በዓል

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የትንሣኤውን ኃይል ወጣቶች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** **"የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ** በመከራውም እንድካፈል … እመኛለሁ፡፡" ፊልጵ. ፫÷፲፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃ. ፳፬÷፴፬-፵፱ እና ፩ቆሮ. ፲፭÷፳

## መግቢያ

የክርስቶስ ትንሣኤ የሞትን ኃይል ሰብሮአል፡፡ ሰው ተስፋ ትንሣኤ እንዳለው ማረጋገጫው የክርስቶስ ትንሣኤ ነው፡፡ የክርስቶስ ትንሣኤ በትንቢት የተነገረ፣ በሚያምኑት የተጠበቀ፣ በክርስቶስ ከሞት በፊት የተሰበከና በሐዋርያት የታወጀ፤ የድል ትንሣኤ ነው፡፡ የክርስቶስ ትንሣኤ የሐዋርያትን ልብ ያጸና ሰላም፤ ስብከታቸውንም ያረጋገጠ እውነት ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የትንሣኤ በዓል የክርስቶስ የድል ፍሬ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ ሞትን በመሻር፤ የሞትን መውጊያ ሰበረ፡፡ የጠላትን ምክር አፍርሶ የድል ሥርዓት በመመሥረት የድል በዓል ለእኛ ልጆቹ ሰጠን፡፡

በቤተክርስቲያናችን ዐበይትና ንዑሳን የሆኑ የጌታ በዓላት አሉ፡፡ ትንሣኤ ከዘጠኙ ዐበይት በዓላት መካከል አንዱ ነው፡፡ ቤተክርስቲያናችን ከጾመ ዓቢይ በኋላ መከራውን በሰሙነ ሕማማት ትሰብካለች ከዚያም ሞት የተረታበትን የድል ታሪክ በማክበር ትደመድማለች፡፡ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽሪት ስለሆነች መከራውን መከራዋ፤ ሞቱን ሞቷ፤ ድሉን ድሏ፤ ትንሣኤውን ትንሣኤዋ፤ አድርጋ ታስባለች፡፡ እስራኤላውያን ከሞት የዳኑበትን የፋሲካ ሥርዓት ለዘላለም ይከብራሉ፡፡ የፋሲካው በግ ደም በኩሮቻቸውን ከሞት ጠብቋል፡፡ አሮጌውን እርሾ ያስወገድን የሐዲስ ኪዳን ልጆች ደግሞ የትንሣኤን በዓል ለዘላለም እናከብራለን፤ ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና፡፡ **፩ቆሮ. ፭÷፯፡፡ የመጀመያዎቹ ክርስቲያኖች የፋሲካን** በዓል በደስታ ያከብሩ ነበር፡፡ በጉባኤ ኒቂያ የተሰበሰቡት ሊቃውንት የፋሲካ በዓል ከእሑድ እንዳይወጣ ዘመን የማይገድበው መስፈሪያ (የዘመን መቁጠሪያ) ቀምረዋል፡፡

www.zeorthodox.org

የትንሣኤ በዓል ታላቅ ደስታ የምናደርግበት ዓቢይ በዓል ነው፡፡ ሞት የተረታበት የድል ታሪክ በመሆኑ ክርስቶሳውያን በሐሴት ያከብሩታል፡፡ በቤተክርስቲያናችን አማኞች የክብር ልብስ ለብሰው የሚታደሙበት የቅዳሴ ሥርዓት ይከናወናል፡፡ ለሃምሣ ቀናት የትንሣኤው ወንጌል ይሰበካል፡፡ አማኞች "ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ ድል መንሣትህ የት አለ?" እያሉ የድል ዜማ ያዜማሉ፡፡

ክርስቲያኖች የትንሣኤው ምስክሮች ናቸው፡፡ ቤተክርስቲያን ሐዋርያዊት በመሆኗ የሐዋርያትን የዓይን ምስክርነት በመጥቀስ ትንሣኤውን ትሰብካለች፡፡ የበዓል ዓላማው የእግዚአብሔርን የማይለወጥ ፍቅርና የማይገደብ ምሕረት ማሰብ ነው፡፡ በዓል ስናከብር እግዚአብሔር ለሰው ያደረገውን ቸርነት እንዘክራለን፡፡ የትንሣኤ በዓልም የሰው የውድቀት እና የጉስቁልና ታሪክ ወደ ክብር የተቀየረበትን የክርስቶስን አሸናፊነት የምንመሰክርበት ነው፡፡

የትንሣኤ በዓልን ስናከብር ክርስቶስ የትንሣኤያችን በኩር እንደሆነ በማወቅ፤ ተስፋ ትንሣኤ እንዳለን በማመን፤ ሞት በክርስቶስ ሞት እንደተሻረ በመመስከር፤ የትንሣኤውን ኃይል ለማወቅ በመመኘት፤ የሞት ደጅ እንደተሰበረ በማወጅ፤ የትንሣኤውን ወንጌል በደስታ በመስማትና የፋሲካውን በግ /ቅዱስ ሥጋውን እና ክቡር ደሙን በመቀበል/ በመብላት መሆን አለበት፡፡

## ማጠቃለያ

የትንሣኤ በዓል የክርስቶስ አሸናፊነት የሚሰበክበት በዓል ነው፡፡ የክርስቶስ ትንሣኤ ትንሣኤያችን ነው፡፡ የክርስቶስ ትንሣኤ የስብከት ማረጋገጫና የእምነት መሠረት ነው፡፡ የትንሣኤ በዓል የክርስቶስ የድል ፍሬ ነው፡፡ ክርስቶስ ሁሉን አሸንፎ ሁሉን ገዝቶ የሞትና የሲኦልን መከፈቻ በመዳፉ የጨበጠ ንጉሥ ነው፡፡ ይህ ግርማው በትንሣኤው ይታወጃል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶችን የትንሣኤ በዓልን እንዴት እንደሚያከብሩ ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ዕርገት እና በዓለ ሃምሳ

**የትምህርቱ ዓላማ፦** ወጣቶች የበዓላትን መንፈሳዊ አከባበር እንዲያውቁ ማድረግ።

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፦** "ኃይልን እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ቆዩ።" ሉቃ. ፳፬÷፵፱

**ተጨማሪ ምንባባት፦** ሐዋ. ፩ እና ፪

## መግቢያ

ዕርገት ማለት ወደላይ ከፍ ከፍ ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሞተን ድል አድርጎ ከተነሣ በኋላ ዐረገ። በተነሣ በሃምሳኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ ለደቀመዛሙርቱ ቋንቋን ገለጠ። ይህ በዓል በዓለ ሃምሳ (ጴንጤቆስጤ) ይባላል። ዕርገት ክርስቶስ ወደ አባቱ በክብር መሄዱ ይዘከርበታል። በዓለ ሃምሳ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ከወጣበት ሳይለይ ወደ አመኑት መምጣቱ ይሰበክበታል።

## የሳምንቱ ትምህርት፦

### ፩. ዕርገት

ጌታችን መድኃኒታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ለማዳን የተገለጠ አምላክ ነው። የመጣበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የመዳናችንን ራስ በመከራ ፈጽሟል። ስለመተላለፋችን ቆስሏል። ሞታችንን በሞቱ ሊሽር በሥጋ ሞቷል። ሞትንም ድል አድርጎ ተነሥቷል። ለአርባ ቀናት እያስተማረ ከቆየ በኋላ "እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ። ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልን ለፍጥረት ስበኩ። አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ። ኃይል እስክትለብሱ በኢየሩሳሌም ቆዩ።" አላቸው። እስከ ቢታንያም አወጣቸው፤ እጆቹንም አንሥቶ ባረካቸው። እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ። ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው። ሉቃ. ፳፬÷፵፬-፶፫፣ **ሐዋ. ፩÷፮-፲፩። *ይህ ታሪክ ዕርገት* በመባል** በቤተክርስቲያናችን ይዘከራል።

ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣበትን ዓላማ በድል ፈጽሞ፤ መንግስቱን በምድር መሥርቶ፤ በደመና ተከቦ፤ በመላእክት ይባቤ/ምስጋና/ ታጅቦ የምድር የስበት ኃይል ሳይዘው በክብር ዐርጓል። በአባቱ ቀኝ ተቀምጧል። መላእክቱ "ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል።" በማለት ዕርገቱን አጅበው ዳግም ምጽዓቱን ሰብከዋል። ሐዋ. ፩÷፲፩። **አሁን ድል አድራጊው ጌታ የክብርና** የምስጋና ዘውድ ተጭኖ በአባቱ ቀኝ እናየዋለን። ዕብ. ፪÷፱፣ **ሐዋ. ፯÷፶፮።**

የዕርገት በዓል የወልድ ጌትነትና አሸናፊነት ይሰበክበታል። ዳግም ሲገለጥ በእርሱ የተሰወረው ክብራችን እንደሚገለጥ ይነገርበታል። ቆላ. ፫÷፩-፫። **የዕርገት በዓል የተሻለ ዓለም** እንደተዘጋጀልን፤ የምድሩን ሳይሆን የሰማዮን ተስፋ እንደምናደርግ ይወሳበታል። በአባቱ ቀኝ መቀመጡ የሥጋን መክበር እንደሚያሳይ በመግለጥ የዕርገት ወንጌል ይሰበክበታል።

www.zeorthodox.org

**፪. በዓለ ሃምሳ (ጰራቅሊጦስ)**

ክርስቶስ ባረገ በዐሥረኛው ቀን ሐዋርያት በአንድ ልብ ሳሉ፤ እስራኤላውያን የመከርን በዓል ሲያከብሩ መንፈስ ቅዱስ ወረደ፡፡ ምስጢርና ቋንቋ ገለጠላቸው፡፡ ኃይልን ሰጣቸው፡፡ የቤተክርስቲያንን ልደት በዓለም ቋንቋ በእሳትም ላንቃ አከበረላት፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ የመንግሥቱን ወንጌል ሰበከ፡፡ ሦስት ሺሕ ሰዎችም ክርስትና ተቀበሉ፡፡ ይህ ዕለት በዓለ ሃምሳ (ጴንጤ ቆስጤ) ይባላል፡፡ ሐዋ. ፪÷፩-፵፪፡፡

በዓለ ሃምሳ የቤተክርስቲያን የልደት ቀን ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች የአማኞችን ሕይወት ያስጌጠበትና ክርስቶስን አምነው የተቀበሉ እጅግ ብዙ ምርኮኞችን ያበዙበት በዓል ነው፡፡ በዓለ ሃምሳ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የተገለጠበትና የትንሣኤው ወንጌል በታላቅ ኃይል የተሰበከበት በዓል ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት የገባው ቃልና የሰጠው ተስፋ የተፈጸመበት፤ ደቀመዛሙርቱም ኃይልን በመቀበል አገልግሎት የጀመሩበትም ዕለት በዓለ ሃምሳ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ክርስቶስ በድል እና በክብር ዐረገ፡፡ መንፈስ ቅዱስ በቃል ኪዳኑ መሠረት ሲጠበቅ የነበረውን ተስፋ ሊፈጽም ወረደ፡፡ በጸጋው ስጦታዎች የደቀመዛሙርቱን አገልግሎት አጸና፡፡ እነዚህ በዓላት ዕርገትና በዓለ ሃምሳ ይባላሉ፡፡

## ተግባር

- መምህሩ “የዕርገትና የጰራቅሊጦስ በዓላት አከባበር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን” በሚል ርእስ ወጣቶች አጭር ዘጋቢ ጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# መጀመሪያው የጢሞቴዎስ መልእክት

**የትምህርቱ ዓላማ:-** የጢሞቴዎስን መልእክት አጠቃላይ ይዘት ለወጣቶች ማስገንዘብ።

**በቃል የሚጠና ጥቅስ:-** "እግዚአብሔርን መምሰል . . . ለነገር ሁሉ ይጠቅማል።" ፩ጢሞ. ፬÷፰

**ተጨማሪ ምንባባት:-** ፩ጢሞ. ፩÷፫

## መግቢያ

ጢሞቴዎስ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በልስጥራን ያገኘው ወጣት ነው። ሴት አያቱና እናቱ አይሁዳዊ ክርስቲያን ነበሩ። ፪ጢሞ. ፩÷፭፤ ፫÷፲፬-፲፭። **የቅዱስ ጳውሎስ የመንፈስ ልጅ** ነው። በቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞዎች አልተለየም። ሁለት የአገልግሎት መልእክታት የመንፈስ አባቱ ጳውሎስ ጽፎለታል።

## የሳምንቱ ትምህርት:-

የጢሞቴዎስ መልእክት የአገልግሎት መልእክት ነው። ጢሞቴዎስ ከሐሰተኛ ትምህርትና መምህራን እንዲጠነቀቅ፣ በአገልግሎቱ እንዲተጋ፣ አገልጋዮችን በተገቢው ሥርዓት እንዲመለምልና ሽማግሌዎችን እንዲያከብር የመጀመሪያ መልእክት በቅዱስ ጳውሎስ እጅ ተጽፎለታል።

1. **የመልእክቱ ዓለማ:-** ጢሞቴዎስ በእምነት ጸንቶ ከኀልማሳነት ክፉ ምኞት በመራቅ ስለወንጌል መከራን እንዲቀበልና በነገር ሁሉ ለሚያምኑት ምሳሌ እንዲሆን ማድረግ።
2. **የመልእክቱ ጸሐፊ:-** ቅዱስ ጳውሎስ ነው። **፩ጢሞ. ፩÷፪**
3. **የተጻፈበት ዘመን:-** በ፷፫/63/ ዓ.ም ገደማ እንደተጻፈ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ።
4. **የመልእክቱ ተደራሲ:-** የጳውሎስ የመንፈስ ልጅ ለሆነው ለጢሞቴዎስ የተላከ መልእክት ነው።
5. **የመልእክቱ አከፋፈል:-**

www.zeorthodox.org

**ምዕራፍ ፩÷፩:- የጳውሎስና የጢሞቴዎስ ግንኙነት**

**ምዕራፍ ፩÷፪-፲፩:- የሐሰተኛ መምህራን ማስጠንቀቂያ**

**ምዕራፍ ፩÷፲፩-፳** የመመሪያው ዓላማ

**፪÷፩-፰:- የጉባኤ አምልኮ ጸሎት**

**፪÷፱-፲፭፡- ሴቶች በጉባኤ**

**፫÷፩-፲፫** የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መመዘኛ

**ምዕራፍ ፬÷፩-፭፡- የሐሰት ትምህርት ጠባይ**

**ምዕራፍ ፬÷፮-፲፮፡- የሐሰት ትምህርት መከላከያ** መንገድ

**ምዕራፍ ፭÷፩-፪፡- ሽማግሌዎችንና ወጣቶችን የማስተዳደር** ዘዴ

**ምዕራፍ ፭÷፫-፲፮፡- መበለቶችን የማስተዳደር ዘዴ**

**ምዕራፍ ፭÷፲፯-፳፭፡- የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን** መምራት

**ምዕራፍ ፮፡-የሐሰት** መምህራን፣ ፍቅረ ንዋይ፣ ለባለጠጎች መመሪያና የጢሞቴዎስ አደራ

## ማጠቃለያ

የመጀመሪያው የጢሞቴዎስ መልእክት የአገልጋዮች መስታወት ነው፡፡ የቤተክርስቲያን ሥርዓት መነሻና የአስተዳደር መመሪያ ምንጭ የሆነ መልእክት ነው፡፡ ጢሞቴዎስ እርባና ከሌላቸው የዓለም ተረቶች በመራቅ በጽናት እንዲያገለግል ይመከራል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች የመጀመያውን የጢሞቴዎስ መልእክት እንዲያጠኑና የተማሩትን እንዲያካፍሉ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ሁለተኛው የጢሞቴዎስ መልእክት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ዘመኑን በማወቅ በጥበብ እንዲመላለሱ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፡፡" ፪ጢሞ. ፫÷፲፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፪ጢሞ. ፩÷፬

## መግቢያ

ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የመጀመሪያውን መልእክት ከጻፈለት በኋላ ሰሜናዊ ግሪክን ለቆ ሄደ፡፡ በሮም ታስሮ የሞት ፍርድ ተፈረደበት፡፡ የሞቱን ቀን እየጠበቀ የመንፈስ ልጁን በእምነቱ ጸንቶ በአገልግሎቱ እንዲተጋ የሚያጠነክር ሁለተኛ መልእክት ጻፈለት፡፡ ፪ጢሞ. ፬÷፮-፰፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**፩.** **የመልእክቱ ዓላማ፡-** ጢሞቴዎስ ቅዱስ ጳውሎስ ያለበትን ሁኔታ ተረድቶ የወንጌል ባለአደራነቱን እንዲያደጸናና የኤፌሶንን ቤተክርስያን እንዲያተጋ ዓላማ አድርጎ የተጻፈ መልእክት ነው፡፡

**፪.** **የተጻፈበት ዘመን፡-** በ፷፮/66/ **ዓ.ም ገደማ በጳውሎስ ሞት ዋዜማ እንደነበር የቤተክርስቲያን** ታሪክ ያስረዳል፡፡

**፫.** **የመልእክቱ ጸሐፊ፡-** ቅዱስ ጳውሎስ ነው፡፡ **፪ጢሞ.** ፩÷፩

**፬.** **የመልእክቱ ተደራሲ፡-** ጢሞቴዎስ፡፡ **፪ጢሞ.** ፩÷፪፡፡

**፭.** **የመልእክቱ አከፋፈል፡-**

**ምዕራፍ ፩** ቅዱስ ጳውሎስ የነበረበት መከራ ሳያሳስበው ስለ ጢሞቴዎስ መጨነቁን ይገልጻል፡፡

**ምዕራፍ ፪** ጢሞቴዎስ ከክርክር በመራቅ በትዕግሥት እንዲያገለግል ያስጠነቅቃል፡፡

**ምዕራፍ ፫** የሚያስጨንቁ ዘመናትና የመዋጊያ ጥበባዊ ዘዴዎች

www.zeorthodox.org

**ምዕራፍ ፬** የቅዱስ ጳውሎስ የመጨረሻ ቃልና ቡራኬ

መልእክቱ የማበረታቻና የማጽናኛ መልእክት ነው፡፡ የሐሰተኛ መምህራንን ሴራ እየገለጠ ጢሞቴዎስ በተማረበትና በተረዳበት እንዲጸና፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ እንዲበረታ፣ በጊዜውም አለጊዜውም ለሌሎች ምሳሌ በመሆን እንዲተጋና አደራውን እንዲጠብቅ ያስተምረዋል፡፡

የመልእክቱ ፍሊጋ ጢሞቴዎስ የቅዱስ ጳውሎስን የጽናት መንገድ እንዲከተል ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ የጽድቅ አክሊል እንደተዘጋጀለት በእርግጠኝነት በመናገር ሩጫውን መፈጸሙን ሲያበስር "የወንጌል ሰባኪነትን ሥራህ አድርግ" ይለዋል፡፡

## ማጠቃለያ

የሁለተኛ ጢሞቴዎስ መልእክት የአገልጋዮችን መከራና የድል ፍሬ ያሳያል፡፡ አገልግሎት በትዕግሥት የሚፈጸም ሩጫ እንደሆነ ያስተምራል፡፡ አገልጋይ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበትን መጽሐፍ በማንበብ በሃይማኖት ሊጎለምስና በጊዜውም አለጊዜውም ሊጸና ይገባዋል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች የሁለተኛ ጢሞቴዎስ መልእክትን ጭብጥ በማጥናት እንዲያቀርቡ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# የድንግል ማርያም ሕይወት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የድንግል ማርያምን አርአያነት በማወቅ በእምነት እንዲመስሏት መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እንደቃልህ ይሁንልኝ" ሉቃስ ፩÷፴፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃስ ፩÷፳፮-፪÷፲፱

## መግቢያ

ድንግል ማርያም ከኢያቄምና ከሐና በሕጋዊ ጋብቻ የተወለደች፤ በቤተ መቅደስ በመላእክት ሥርዓት ያደገች፤ ንጉሥ ውበቷን ወዶላት የአባቷን ቤት የተወች፤ በመቅደስ ኖራ የመቅደሱን ጌታ በድንግልና የወለደች፤ ማሪኪ የሕይወት ገጾች ያሏት ንጽሕት እናት ናት፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ድንግል ማርያም ክብርት፣ ልዕልት፣ ንግሥት፣ ውድስት፣ ብፅዕት፣ ቅድስት፣ ንጽሕት፣ ኅርይትና ስብሕት ናት፡፡ የድንግል ማርያም ሕይወት አስማሪ ነው፡፡ ድንግል የሕይወት መምህርት ናትና፡፡ በቃልም በሕይዋትም ለነፍሳችን ጌታ እንድንገዛ አስተምራናለች፡፡

**፩. የጸሎት ሕይወት፡-** ድንግል ማርያም በመቅደስ ስላደገች ጠንካራ መሠረት ያለው የጸሎት ሕይወት አላት፡፡ ቅዱሱን ከፀነሰች በኋላ "ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች" በሚል ርእስ የተመራ፤ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ክንዱን የገለጠባቸውን ታሪኮች ያካተተ ጸሎት ጸልያለች፡፡ ሉቃ. ፩÷፵፮-፶፭፡፡ **ከደቀመዛሙርቱ ጋር** - ትጸልይ ነበር፡፡ ሐዋ. ፩÷፲፬፡፡

**፪. የእምነት ጽናት፡-** ድንግል ማርያም "ያመነች ብጽዕት" ናት፡፡ ከተፈጥሮ ሕግ በላይ የሆነ ነገር መልአኩ ነገራት፡፡ "ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንደምን ይሆናል?" አለችው፡፡ መልአኩም "ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም፡፡" ሲላት "እንዳልከ ይሁንልኝ" በማለት የጸና እምነቷን አሳይታለች፡፡ የማይቻለውን የቻለችው እናትም ድንግልም የሆነችው ጽኑ እምነት ስለነበራት ነው፡፡ እምነት የሁሉም ነገር መሠረት ነው፡፡ ጸሎት ደግሞ እምነትን ያሳድጋል፡፡ የጸሎትና የእምነት ሕይወትን ገንዘብ ካደረግን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ የሆነችልን የተቀደሰ ሕይወት ይኖረናል፡፡ ያመኑ ይጸልያሉ፤ የሚጸልዩ እንደተቀበሉ ያምናሉ፡፡ ማር. ፲፩÷፳፬፡፡

**፫. የቅድስና ሕይወት፡-** ድንግል ማርያም በቅድስና ሥርዓት ያጌጠ ሕይወት ያላት ንጽሕት እናት ናት፡፡ ከሐሳብ፣ ከመናገርና

www.zeorthodox.org

ከተግባር ኃጢአቶች በመራቅ በጽድቅ ሥርዓት የኖረች እመቤት ናት፡፡ መንፈስ ቅዱስ ከርኩሰት የከለላት ቅድስት ድንግል ናት፡፡ እግዚአብሐር የቅድስና ጥሪ ለሁላችንም አስተላልፏልና በቅድስና ሕይወት ኖረን እሷን እንምሰላት፡፡

**፬. የምስጋና ሕይወት፡-** እመቤታችን ማርያም እግዚአብሔር በሷ ስላደረገው ነገር ሁሉ፤ "መንፈሴ በመድኃኒቴ በአምላኬ ሐሴት ታደርጋለች የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቷልና" በማለት አመስግናለች፡፡ ሉቃስ ፩÷፵፯-፵፱፡፡ **እግዚአብሔር በሠራው** መመስገን ይፈልጋል፡፡ ስለሁሉ ነገር የከንፈራችን ፍሬ የሆነውን ምስጋና ሳናቋርጥ ልንሠዋለት ይገባል፡፡

**፭. የትሕትና ሕይወት፡-** ድንግል ማርያም ትንቢተ ኢሳይያስ ፯÷፲፬**ን ስታነብ "የዚህች ድንግል** አገልጋይዋ በሆንኩ" ብላ ተመኘች እንጂ "እኔ በሆንኩ" አላለችም፡፡ እግዚአብሔር ይህን ትሕትናዋን አይቶ ከፍ አደረጋት ከምኞቷ በላይ በሆነ ከፍታ አስቀመጣት፡፡ መልአኩ በታላቅ ምስጋና እያከበራት "የባሪያውን ውርደት ተመልክቶአል" በማለት በትሕትና መለሰች፡፡ እግዚአብሔር የትሑታንን መንገድ ያቀናል፤ በጸጋው ያከብራቸዋል፡፡ ያዕ. ፬÷፮-፰፡፡

**፮. በመከራ መታገስ፡-** ድንግል ማርያም የጽናት አርአያችን ናት፡፡ ከቤተልሔም እስከ ቀራንዮ ልጇን ያልተለየች፤ በአማኞች ጉባኤም አብራ በጸሎት የነበረች የጽናት አብነት ናት፡፡ ስምዖን አረጋዊ "በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል፡፡" እንዳላት ስለ ልጇ ብዙ መከራን ታግሣለች፡፡ ስለልጇ ለሚነቅፋት የጽናት መምህርት ናት፡፡

**፯. ርኅራኄ፡-** ድንግል ርኅርኅተ ኅሊና ናት፡፡ ርኅራኄዋ ከሰው አልፎ ለውሻ ተርፎአል፡፡ ድንግል በአማላጅነቷ ለተደገፉ ብቻ ሳይሆን ለሚጠሏትም ጸልያለች፡፡

**፰. ምስጢር ጠባቂነት፡-** ድንግል ሁሉን በልብዋ ትጠብቀው ነበር፡፡ ሉቃ. ፪÷፲፱፡፡ **ምስጢርን እስከ ጊዜው** መጠበቅ ይጠቅማል፡፡

## ማጠቃለያ

ድንግል ማርያም የሕይወት ሰባኪ ናት፡፡ በጽድቅ ሥርዓት የተጓዘች "የሚላችሁን አድርጉ" ብላ ልጇን በቃና ዘገሊላ የሰበከች እናት ናት፡፡ ድንግልን የምንወድ ሁሉ የተቀደሰ ሕይወትዋን በአርአያነት ተከትለን እኛም የተቀደሰ ሕይወት ይኑረን፡፡

## ተግባር

መምህሩ ወጣቶች ድንግል ማርያምን በእምነት እንዲመስሏት ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ጴጥሮስ በሰማዕትነት ዐረፈ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ዋኖቻቸውን በእምነት እንዲመስሏቸው ማስገንዘብ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ፡፡" ፩ጴጥ. ፭÷፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዕብ. ፲፫÷፯

## መግቢያ

- ተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ ማን ነው?
- ስለ ዘመነ ሰማዕታት የምታስታውሱትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ክርስትና የሮምን ድንበር በብዙ ፈተና በመከራ ከተሻገረ በኋላ ክርስትናውን የሚቃወሙ አላውያን ነገሥታት በዙ፡፡ ክርስቲያኖች ከ፶፬/54/ዓ.ም-፫፻፭/305/ዓ.ም ሕይወታቸውን ሠውተዋል፡፡ ይህ ዘመን ዘመነ ሰማዕታት ይባላል፡፡ በኔሮን ቄሳር የተጫረው የተንኮል እሳት ብዙዎችን አቃጠለ፤ የዲዮቅልጥያኖስ የጥፋት ዓዋጅ የንጹሐንን ደም አፈሰሰ፡፡

የሶርያ፣ የእስክንድርያና የአርመን አብያተ ክርስቲያናት መራራ ሐዘን አጋጠማቸው፡፡ በዚያ ዘመን ነበር ተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ በእንባ በታጀበ ጸሎት የፀባዖትን ደጅ ያንኳኳው፡፡

ቅዱስ ጴጥሮስ ከግብጻዊው ቄስ ከቴዎዶስዮስ እና ከሶፍያ ተወለደ፡፡ በሕፃንነቱ እንደ ሳሙኤል ወደ ቤተ መቅደስ መጣ፡፡ የመንፈስን ጥበብ በመማር በሰውና በእግዚአብሔር ፊት በሞገስ አደገ፡፡ በአገልግሎቱ የበረታ በመሆኑ "የክርስትና ዶክተር" የሚል ቅጽል ስም ወጣለት፡፡ በ፪፻፹፭/285/ ዓ.ም በመንበረ ማርቆስ ዐሥራ ሰባተኛው የግብጽ ፓትርያርክ ሆነ፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ የእለእስክንድሮስ መምህር ነው፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ በአንድ ወቅት የአርዮስን ፍጻሜ የሚገልጥ ራእይ አየ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀደደ ቀሚስ ለብሶ በራእዩ አየና "ጌታ ሆይ ቀሚስህን ማን ቀደደብህ?" ሲለው "አርዮስ ልብሴን ቀደደብኝ" አለው፡፡ አርዮስ ልብስ የተባለ ሃይማኖትን እንደሚከድ በመንፈስ ተረድቶ አወገዘው፡፡ የአርዮስም ፍጻሜ አስቀድሞ በራእይ እንዳየው ሆነ፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ጴጥሮስ የእስክንድርያን የቀን መቁጠሪያ ከዓመተ ሰማዕታት ፪፻፹፬(284) ዓ.ም እንዲነሣ አድርጓል፡፡ በዘመነ ዲዮቅልጥያኖስ ብዙ አማኞች ደማቸውን ስለክርስቶስ ፍቅር ሲያፈሱ አይቶ አዘነ፡፡ በመከራው ጽናት ክርስቲያኖች ወደ ጥፋት መንገድ እንዳያፈገፍጉ በማሰብ "ጌታ ሆይ ሰማዕትነት በእኔ ይፈጸም የመከራን ዘመን ፈጽም" በማለት ጸለየ፡፡ እግዚአብሔርም ሰማው፤ የዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ ንግሥና ተፈጸመ፡፡ በዲቅልጥያኖስ ዘመን የመጨረሻው ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ ሆነ፡፡ በዚህም

ምክንያት “ተፍጻሜተ ሰማዕት” የሚል ስም ተሰጠው፡፡

## ማጠቃለያ

ቅዱስ ጴጥሮስ የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ዐሥራ ሰባተኛ ፓትርያርክ፣ የዘመነ ሰማዕታት መደምደሚያ ሰማዕት፤ ታማኝ መሪና እውነተኛ መምህር ነው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ‹‹የክርስትና ጉዞ ለምን መከራ በዛበት?›› በሚል ርእስ ወጣቶችን ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ምስጢራተ ቤተክርስቲያን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን እንዲፈጽሙ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ጥበብ ቤትዋን ሠራች ሰባቱንም ምሰሶዎችዋን አቆመች" ምሳ. ፱÷፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ምሳሌ ፱÷፩-፮ እና ፩ቆሮ. ፲፩÷፲፯-፴፬

## መግቢያ

ምስጢር ማለት ስውር ድብቅ ማለት ነው፡፡ ሰውን ለአንድ ነገር አላዋቂ መሃይም አድርጎ የሚያስቀር ሳይሆን እግዚአብሔር በጊዜው የሚገልጠው እውነት ነው፡፡ ከትውልዶች ጀምሮ ከዘመናት አስቀድሞ የተሰወረውን በዘመን መጨረሻ በልጁ ገልጦአል፡፡ ዕብ. ፩÷፩-፫፡፡ **መጻሕፍት የመጻፋቸው ዓላማም** የእግዚአብሔርን የዘላለም ምክር ለትውልድ ለመግለጽ ነው፡፡ የማይታየውን የእግዚአብሔር ጸጋ የሚያሰጡ አገልግሎቶች በቤተክርስቲያናችን ምስጢራት ይባላሉ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቤተክርስቲያን ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር በቃል ኪዳን የምታስተሳስርባቸው ምስጢራት አሏት፡፡ እነዚህ ምስጢራት ሰባት ናቸው፡፡ እነሱም ጥምቀት፣ ሜሮን፣ ቁርባን፣ ንስሐ፣ ቀንዲል፣ ተክሊልና ክህነት ይባላሉ፡፡ ከሰባቱ ምስጢራት ቤተክርስቲያን ጥምቀት፣ ተክሊልና ክህነት የማይደገሙ (ለአንድ ሰው ደግመው የማይፈጸሙ) ምስጢራት ናቸው፡፡ አንድ አማኝ ጥምቀትን፣ ሜሮን፣ ቁርባንና ንስሐን የግድ መፈጸም ይጠበቅበታል፡፡

ጠቢቡ ሶሎሞን በመጽሐፈ ምሳሌ "ጥበብ ቤትዋን ሠራች ሰባቱንም ምሰሶዎችዋን አቆመች፡፡ ፍሪዳዋን አረደች፤ ወይን ጠጅዋን ደባለቀች፡፡ ማዕድዋን አዘጋጀች፡፡ ባሪያዎቿን ልካ ኑ እንጀራዬን ብሉ፡፡ የወይን ጠጅ ጠጡ፡፡ አላዋቂነትን ትታችሁ በሕይወት ኑሩ፡፡" በማለት የሐዲስ ኪዳኗን መቅደስ በድግስ መስሎ ተናግሯል፡፡ ጥበብ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ክቡር ደሙን አፍስሶ ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶ "ኑ ብሉ" አለን፡፡ ዮሐ. ፮÷፶፮-፶፱፡፡

www.zeorthodox.org

የሐዲስ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን የጥበብ ድግስ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ነው፡፡ ቤተክርስቲያን ሰዎች ከርኩሰት ተለይተው በቅድስና ሥርዓት እንዲኖሩ፤ አላዋቂነትን ትተው ወደ ሕይወት ዛፍ እንዲደርሱ የጥበብ ማዕድ ደግሳለች፡፡ ሰባት ምሰሶዎች የተባሉ ሰባቱ ምስጢራት ቤተክርስቲያን ናቸው፡፡ አገልጋዮቿን ልካ "ኑ" እያለች ትጠራለች፡፡

ምስጢራቱን በመፈጸም አርአያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ የምስጢራቱ መሥራችና ባለቤት እርሱ ምስጢራትን ፈጽሞአል፡፡ ልጅነትን ለምታስጠው ጥምቀት የመጀመሪያው (በኩረ ምእመናን) እራሱ ነው፡፡ እርሱ ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም ተጠመቀ፡፡ እኛ

ደግሞ እርሱ የፈጸመውን ጽድቅ ለመቀበል ተጠመቅን፡፡

ቤተክርስቲያን በምስጢረ ጥምቀትና በምስጢረ ሜሮን የእግዚአብሔር ልጅነትን፤ በምስጢረ ቁርባን የዘላለም ሕይወትን፤ በምስጢረ ክህነት የአገልግሎት ሥልጣንና ሓላፊነትን፤ በምስጢረ ንስሐ የኃጢአት ስርየትን፤ በምስጢረ ተክሊል የጋብቻ አንድነትን (የመንፈስ ኅብረትን)፤ በምስጢረ ቀንዲል ፈውስን ትሰጣለች፡፡ ቅድስት ቤተክርስቲያን በሚታዩት የምስጢራት አገልግሎት የማይታየውን ጸጋ እግዚአብሔርን ታሰጠናለች፡፡

አማኞች የመንፈስ ቅዱስ ልጅነትን /ልደት/ በጥምቀት፤ ለሥጋና ለነፍስ ፈውስ ቀንዲልንና ንስሐን፤ ለአንድነት ጸጋ ተክሊልን፤ ለመንፈሳዊ ኅብረት ቁርባንን መቀበል ይጠበቅብናል፡፡ በሥጋዊ ኑሯችን ለማደግ እንደክማለን፤ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ግን ብዙ ሳንደክም በምስጢራት ደጋፊ ጸጋውን እንቀበላለን፡፡

## ማጠቃለያ

የሚታየው ምስጢራተ ቤተክርሰቲያን አገልግሎት ከእግዚአብሔር ጋር የማይታየውን ኅብረት ለመመሥረትና መልካም ግንኙነታችንንም ለማረጋገጥ ይጠቅመናል፡፡ ምስጢራት የማይታየው የእግዚአብሔር ጸጋ መገኛ ናቸው፡፡ በዘመናችን ሁሉ ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን መፈጸም አለብን፡፡

## ተግባር

- መምህር ወደ ምስጢራቱ እንዲቀርቡ ወጣቶችን ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ከክፉ ነገር መሸሽ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ከክፉ ነገር ሁሉ እንዲርቁ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ክፉውን ነገር ተጸየፉት" ሮሜ. ፲፪÷፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መዝ. ፴፫÷፲፪-፲፬፣ ፩ጴጥ. ፫÷፰-፲፬ እና ፪ጴጥ. ፪÷፬-፲፯

## መግቢያ

ክፉ ነገር ዲያብሎስን የሚያከብር፤ ሰውና እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ኃጢአት ነው፡፡ የክፉ ነገር ሁሉ መገኛው ከክፉው ከዲያብሎስ ነው፡፡ ከመልካሙ ከእግዚአብሔር የሆኑ የብርሃን ልጆች መልካም በማድረግ ይታወቃሉ፡፡ ከክፉ የማይሸሹ የዛሬ መልካም ሊሠሩበት የሚገባቸውን ጊዜያቸውንና ሕይወታቸውን ያበላሻሉ፤ ለነገ መከራ ያከማቻሉ፡፡ ክፉ የሚያስደስተው ክፉዎችን ብቻ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እግዚአብሔር የፈጠረው መልካም ነገርን ነው፡፡ ፍጥረታትን ፈጥሮ ሲፈጽም "እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ አየ፤ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ፡፡" በሚል ቃል ታትሟልና፡፡ ዘፍ. ፩÷፴፩፡፡

ክፉ ነገር የሚገኘው ከዲያብሎስ ነው፡፡ ክፉ ነገር የኃጢአት ውጤት ነው፡፡ አዳም ክፉና መልካሙን ከምታስታውቀው ዛፍ ከመብላቱ በፊት ክፉ ነገርን የማያውቅ ሰውነት ነበረው፡፡ ክፉ ነገር የአለመታዘዝ ውጤት ነው፡፡

ክፉ መሥራት ሠሪውንም ሌሎችንም ይጎዳል፡፡ ሙሴ "ከክፉዎች ድንኳን ፈቀቅ በሉ" ማለቱ በክፉዎች ጥፋት እንዳንጠፋ ነው፡፡ ዘኍ. ፲፯÷፳፯፡፡ **ዳዊት ሕይወትን የሚፈቅድ ሰው** ክፉን እንዲጸየፍ መክሮአል፡፡ "ሕይወትን የሚፈቅድ ሰው ማን ነው? በጎውን ዘመን ለማየት የሚወድ? አንደበትህን ከክፉ ከልክል፤ ከንፈሮችህም ሽንገላን እንዳይናገሩ፡፡ ከክፉ ሽሽ መልካምንም አድርግ፡፡" በማለት ሰው በአሳብም በመናገርም በተግባርም ክፉን እንዲጸየፍ ሰብኳል፡፡ መዝ. ፴፫÷፲፪-፲፬፡፡

የዛሬው ክፉ ሥራ ነገን ያበላሻል፡፡ በጎውን ዘመን ለማየት በጎ መሆንና መልካም መሥራት ያስፈልጋል፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ የዳዊትን ዝማሬ ጠቅሶ ከክፉ እንድንሸሽ አስጠንቅቆአል፡፡ **፩ጴጥ. ፫÷፲-፲፪፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ "ክፉውን** ተጸየፉት ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ" በማለት አስተምሮአል፡፡ ሮሜ. ፲፪÷፱፡፡

ወጣትነት በክፉ ነገር የምንፈተንበት ሕይወት ነው፡፡ አንደበታችንን ክፉ ከመናገር፣ እጃችንን ክፉ ከመሥራት፣ አእምሮአችንን ክፉ ከማሰብ መከልከል አለብን፡፡ ከክፉ ነገር ስንሸሽ በመልካም የሕይወት ጎዳና ተጉዘን በረከትን ከምንወርስበት በጎ ዘመን እንደርሳለን፡፡ ከክፉ የሚሸሹ በረከትን ይወርሳሉ፡፡ በጎውን ዘመን ዓይኖቻቸው ያያሉ፡፡ ከክፉ የሚሸሹትን እግዚአብሔር ከክፉ

www.zeorthodox.org

ይጠብቃቸዋል፡፡

ክፉ ነገር እግዚአብሔርን ያሳዝናል፤ ሰውን ይጎዳል፤ ምድርን ለርኩሰት ያጋልጣል፡፡ ክፉ ነገር መልካሙን አመል ያጠፋል፡፡ ከመልካምነት የወጡ ከክፉ ናቸው፡፡

## ማጠቃለያ

ከክፉ ነገር መሸሽ ዛሬን ማስዋቢያ፤ ነገን በበረከት መኖሪያ አቅም ያስገኛል፡፡ ከመልካም መንገድ የወጡ ሁሉ ከክፉ ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር የሆኑ መልካም እየሠሩ ከመልካሙ ይጠግባሉ፡፡ ክፉ ነገርን ማድረግ ሰውን ይጎዳል፤ እግዚአብሔርን ያሳዝናል፡፡ ክፉ የሚያስደስተው ከክፉ ነው፡፡ ከክፉዎችን ፈቀቅ በማለት መልካምን ማድርግ ሕይወትን ከሞት ይሰውራልና ክፉን መጸየፍ ይገባል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ‹‹ከክፉ ነገር እንዴት መሸሽ ይቻላል?›› በሚል ርእስ ወጣቶችን ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# መጽሐፈ ምሳሌ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የወጣትነት ጉዟቸውን በጥበብ ቃላት እንዲያቀኑ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "መልካም ጥበብንና ጥንቃቄን ጠብቅ ለነፍስህ ሕይወት ይሆናሉና፡፡" ምሳ.፫÷፳፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ምሳሌ ፩-፴፩

## መግቢያ

ምሳሌ ማለት የምስጢር መግለጫ፣ የነገር ማስረጃ፣ የትምህርት ማብራሪያና የጠቢባን አንደበት ፍሬ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነገርን በምሳሌ አስደግፎ ያስተምር ነበር፡፡ መጽሐፈ ምሳሌ የጠቢቡ ሰሎሞን ምሳሌዎች መዝገብ ነው፡፡ ምሳሌዎቹ እግዚአብሔርን የሚያመልክ ሰው እንዴት መኖር እንዳለበት ያስተምራሉ፡፡ በመጽሐፈ ምሳሌ የጥበብ ጥሪ አደባባይ ወጥቷል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

መጽሐፈ ምሳሌ ከስምንቱ የጥበብ መጻሕፍት መካከል አንዱ ነው፡፡ የሕይወት እንቅስቃሴ በጥበብ፣ በማስተዋልና በጥንቃቄ እንደሚመራ ያስተምራል፡፡ አንድ አባት ልጁን እንደሚመክር በሚያሳይ የአተራረክ ዘዴ "ልጄ" እያለ እውቀትን ያበዛል፤ የሕይወትን ጉዞ በትዕግሥትና በጥንካሬ ለመፈጸም የሚያስችል ምክር በጆሮ ያፈሳል፡፡

**፩. የመጽሐፉ ዓላማ፡-** ሰው ሕይወቱን በጥበብና እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲመራ መምከር

**፪. የመጽሐፉ ጸሐፊ፡-** ጠቢቡ ሰሎሞን ነው፡፡ ከአምስቱ መጻሕፍቱ የመጀመሪያው መጽሐፈ ምሳሌ ነው፡፡

**፫. የተጻፈበት ዘመን፡-** በሰሎሞን የንግሥና ዘመን በ፱፻፶/950/ ዓ.ዓ ገደማ እንደተጻፈ ሊቃውንት ይናገራሉ፡፡

**፬. የመጽሐፈ ምሳሌ ባሕርያት፡-** ንጽጽራዊ ምሳሌ፣ በግጥም የቀረቡ ቅኔዎች፣ ዕድሜንና እውቀትን ያገናዘበ መጽሐፍ ነው፡፡ በአእምሮ ላልበሰሉት ጥንቃቄን ያሳያል፤ በዕድሜ ለጋ ለሆኑት ዕውቀትንና ልባምነትን ይገልጣል፤ ጥበበኞችን በላቀ ጥበብ ይማርካል፡፡ ሕይወትን እንዴት መምራት እንዲቻል ተግባራዊ ትንታኔ ይሰጣል፡፡ የትጋትንና የጥንቃቄን መንገድ ይጠቁማል፤ ሰው የጥበብን ደጅ እንዲያንኳኳ ይመክራል፡፡

**፭. የመጽሐፉ አስተዋጽኦ (ጠቅላላ አከፋፈል)፡-**

ምዕራፍ ፩፡- **የጥበብ ጎዳና**

www.zeorthodox.org

ምዕራፍ ፪-፬፡- **የጥበብ ምክርና ጥቅም**

ምዕራፍ ፭-፯፡- **የኃጢአትና የጠማማ አካኪያሄድ** ውግዘት

ምዕራፍ ፰-፱፡- **የጥበብ ጥሪ**

ምዕራፍ ፲-፳፬፡- **የሰሎሞን ምሳሌዎች**

ምዕራፍ ፳፭-፳፱፡- **ሕዝቅያስ የሰበሰባቸው የሰሎሞን** ምሳሌዎች

ምዕራፍ ፴፡- **የአገር አባባሎች**

ምዕራፍ ፴፩፡- **የንጉሥ ልሙኤል አባባሎችና** የመልካም ሴት ባሕርያት

**፮. የመጽሐፉ የትኩረት አቅጣጫ**፡- እግዚአብሔርን በመፍራት መኖር፤ ጥበብን መውደድ፣ የከፉዎችን መንገድ መጸየፍ፣ ሕጉን መጠበቅ እና ተግሣጹን አለማቃለል፤ በማስተዋልና በጥንቃቄ መመላለስ፣ የጽናት ፍሬ፣ የመልካምነት ዋጋ፣ የአስተዋይ ሴት ባሕርያትና ማኅበራዊ አኗኗር የመጽሐፉ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

***፮.፩. እግዚአብሔርን መፍራት፡-*** ጠቢቡ፤ የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት እንደሆነ በአጽንዖት አስተምሯል፡፡ ምሳ. ፩÷፯፡፡ **እግዚአብሔርን መፍራት ወደ ሕይወት** እንደሚመራንና ዘመንን እንደሚያራዝም ይገልጣል፡፡ ምሳ. ፲፱÷፳፫፡፡ **እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር** ያለን ጥቂት ነገር ለሰው በቂ እንደሆነ ይሰብካል፡፡ ምሳ. ፲፭÷፲፮፡፡

***፮.፪. ጥበብን መውደድ፡-*** የመጽሐፈ ምሳሌ ዋና አሳብ ጥበብ ነው፡፡ ከምዕራፍ ፩-፱ የጥበብ ጥሪ በጎዳና በአደባባዮች ከፍታ መውጣቱን ይገልጣል፡፡ ጥበብ ከቀይ ዕንቁ የምትበልጥ የከበረ ነገር ሁሉ የማይተካከላት ሃብት እንደሆነች መክሮ "ወዳጄ ብለህ ጥራት" ይላል፡፡ ጥበብ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱ ለአባቱም ጥበብ ነው፡፡ የሕይወት ጥበቧ እርሱ ነውና "ወዳጄ" ብለን እንወዳጀው፡፡ ምሳ. ፰÷፩-፲፩፣፱÷፩-፲፡፡

***፮.፫. ሕጉን መጠበቅ፡-*** እንደ ልጅ እየመከረ "ሕጌን አትርሳ ልብህም ትእዛዜን ይጠብቅ፡፡ ብዙ ዘመናትና ረጅም ዕድሜ ሰላምም ይጨመሩልሀልና" ይላል፡፡ ምሳ ፫÷፩፤ ፪÷፩፤ ፭÷፯፤ ፯÷፩-፭፡፡ **ከጋለሞታ መንገድ፣ ከክፉዎች** ዐመጽና ከርኩሰት ኃጢአት በመራቅ ሕጉን እንደዓይናችን ብሌን እንድንጠብቅ ይመክራል፡፡

## ማጠቃለያ

መጽሐፈ ምሳሌ ከጥበብ መጻሕፍት መካከል አንዱ ሲሆን የጠቢቡ ሰሎሞን ምሳሌዎች መዝገብ ነው፡፡ ሰው በዕለታዊ እንቅስቃሴው፣ በማኅበራዊ ኑሮውና ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት በማስተዋል፣ በጥበብና በጥንቃቄ እንዲኖር ይመክራል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ "ለወጣቶች ምክር በመጽሐፈ ምሳሌ" በሚል ርእስ አጭር ጥናታዊ ጽሑፍ ወጣቶች እንዲያዘጋጁና እንዲያቀርቡ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ሕመምተኛ ሰውን ቀብዓ ቀንዲል መቀባት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ቤተ ክርስቲያን መለኮታዊ የፈውስ ሥርዓት እንደምትሰጥ ማሳወቅ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የታመመ ማንም ቢኖር የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች በጌታ ስም ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት፡፡" ያዕ. ፭÷፲፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማር. ፫÷፲፫-፲፭ እና ሉቃ. ፱÷፳፩

## መግቢያ

ቤተክርስቲያን የተቸገሩ ሁሉ መፍትሔ የሚያገኙባት የሁሉንም ጉዳይ ጉዳይዋ ያደረገች ሕሙማን የሚፈወሱባት ቤተ ሕሙማን ናት፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ "ቤተ ክርስቲያን የሕሙማን ሃኪም ቤት ናት" እንዳለ፡፡ ቤተክርስቲያን የነፍስ ሃኪም ክርስቶስ ኢየሱስ የተሰበሩትን የሚጠግንባት፣ የቆሰሉትን የሚፈውስባትና የታመሙትን የሚያድንባት መንፈሳዊት ዓለም ናት፡፡ ቤተክርስቲያን ሕሙማነ ሥጋን በቅብዓ ቀንዲል፣ በጸበልና በመስቀል፤ ሕሙማነ ነፍስን በወንጌል ትፈውሳለች፡፡ ከሰባቱ ምስጢራት ቤተክርስቲያን አንዱ ሕሙማንን የሚመለከት ነው፤ እርሱም ምስጢረ ቀንዲል ይባላል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ፤ "ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች (ካህናት) ወደ እርሱ ይጥራ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት፡፡ የእምነት ጸሎት ድውዩን ያድናል፡፡ ጌታም ያነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል፡፡" በማለት አስተምሯል፡፡ ያዕ. ፭÷፲፬-፲፮፡፡ **ይህ ቃል ለምስጢረ ቀንዲል** መነሻ ነው፡፡

የታመመ ሰውን ካህናት ቀንዲል ቀብተው በጌታ ስም ይጸልዩለታል፡፡ በሚታየው ሥርዓተ ቀንዲል የማይታይ ስርየተ ኃጢአት ያገኛል፡፡ በእምነት ከቆመ ከደዌው ፍጹም ይፈወሳል፡፡ ምስጢረ ቀንዲል የሥጋንም የነፍስንም ጤንነት ይመልሳል፡፡ መንፈሳዊው የፈውስ ሥርዓት ሞትን በሕይወት የመቀየር ኃይል አለው፡፡

www.zeorthodox.org

የታመመው ሰው በንስሐ፤ በጸሎትና በእምነት ከተመለሰ እግዚአብሔር ፈውስ ሥጋ ወነፍስ ይሰጠዋል፡፡ ለሕሙማን ፈውስ የሚሰጠው እግዚአብሔር ሲፈቅድ ነው፡፡ አንዳንድ ሕመሞች አብረውን ይኖራሉ፡፡ የመኖራቸው ዓላማ ለክብርና ለንጽሕና ነው፡፡ ጳውሎስ በመገለጥ ታላቅነት እንዳይታበይ ከባድ ራስ ምታት ተሰጥቶታል፡፡ ጢሞቴዎስ ስለ ንጽሕና ሆዱን ይታመም ነበር፡፡ **፩ቆሮ.** ፲፪÷፬-፲፡፡ **ለክብር እንድንበቃ የሚጎስመን፣** ከኃጢአት ጋር እንዳንዛመድ የሚያነቃንና ወደ ተሻለ የሕይወት ከፍታ እንድንወጣ እንደ ኢዮብ ማንነታችንን የሚፈትነን በሽታ ሲኖር በጸጋ እንቀበል፡፡

የቤተክርስቲያን የፈውስ አገልግሎት ሥጋዊውን ሕክምና አይቃወምም፡፡ በኤች አይ ቪ የተያዙ ሰዎች ፀረ ኤች አይ ቪ መድኃኒት እየወሰዱ ጠበልም መጠቀም ይችላሉ፡፡ በሁሉም ፈዋሹ እግዚአብሔር ነው፡፡ ሃኪም ይህክምና ርዳታ ያደርጋል እንጂ አይፈውስም፡፡ ፈውስ መስጠት የእግዚአብሔር ድርሻ ነው፡፡ የታዘዘልን መድኃኒት ፈውስ ሆኖ ሊያድነን የሚችለው እግዚአብሔር ሲፈቅድ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ምስጢረ ቀንዲል ለሥጋም ለነፍስም ጤንነት የሚሰጥ የቤተክርስቲያን የፈውስ ሥርዓት ነው፡፡ በእምነት በሚደረግ ጸሎትና የፈውስ ሥርዓት ያመነ እንደፈቃደ እግዚአብሔር ይፈወሳል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶችን ‹‹የቤተክርስቲያን የፈውስ ሥርዓት እንዴት ይከናወናል?›› በሚል ርእስ ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# አቡነ ተክለ ሃይማኖት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ከቅዱሳን አባቶች ጋር የመንፈስ ኅብረት እንዲያደርጉ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም፡፡" ኤፌ. ፪÷፲፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዕብ. ፲፩፤፲፫÷፯ እና (ገድለ ተክለ ሃይማኖት)

## መግቢያ

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ኢትዮጵያዊ ጻድቅ ናቸው፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከአባታቸው ከጸጋ ዘአብና ከእናታቸው ከቅድስት እግዚሐርያ በሸዋ ቡልጋ ታኅሣሥ ፳፬ ቀን ፲፩፻፺፯ ዓ.ም ተወለዱ፡፡ አባታቸው የደብረ ጽላልሽ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ካህን ነበሩ፡፡ በክርስትና ስማቸው "ፍስሐ ጽዮን" ይባላሉ፡፡ ኢትዮጵያን በወንጌል ያቀኑ፤ በጸሎት የደገፉ፤ ታላቅ አባት ናቸው፡፡ የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ታላቅ ቅዱስ ብላ አክብራ በመቀበል አብያተ ክርስቲያናትን ያነጸችላቸው ብቸኛ ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ናቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አቡነ ተክለሃይማኖት የክህነት ሥልጣንን ከአቡነ ቄርሎስ ግብጻዊ ተቀብለው ወንጌልን በማስተማር አሕዛብን አጥምቀዋል፡፡ ከአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫና ከአባ ኤዎስጣቴዮስ ጋር ሆነው በሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ከአባ ኢየሱስ ሞዓ ተምረዋል፡፡

በደብረ ሊባኖስ ደቀ መዛሙርቱን በማስተማር፣ ስለ ኢትዮጵያ በመጸለይና ደቡብ ኢትዮጵያን በወንጌል በማቅናት ሕያው ታሪክ የሠሩ ታላቅ የኢትዮጵያ ሐዋርያ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ የፓትርክና መንበር መነሻ የእርሳቸው ዕጨጌነት ነው፡፡ በግብጽና በኢትዮጵያ መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡

አቡነ ተክለ ሃይማኖት የወንጌል (ሐዋርያዊ) ጉዟቸውን ሲጀምሩ "አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የመንግሥተ ሰማያትን በር ትከፍትልኝ ዘንድ ቤቴን እንደተከፈተ ልተውልህ . . . ደካማ ለሆንኩ ለእኔ ያለ አንተ የሚያጸናኝ የለም፡፡ ለምፍገመገም ለእኔ ያለ አንተ ደጋፊ የለኝም፡፡ ለወደቅሁ ለእኔ ያለ አንተ የሚያነሣኝ የለም፡፡ ለአዘንኩ ለእኔ ያለአንተ የሚያረጋጋኝ የለም፡፡ ለድሃው ለእኔ ከአንተ በቀር መጠጊያ የለኝም፡፡" በማለት እንደጸለዩ ገድላቸው ይመሰክራል፡፡ (ገድለ ተክለ ሃይማኖት ፳፰÷፪-፫)

www.zeorthodox.org

የጸሎታቸውም ፍሬ ብዙዎችን ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ፤ ከክህደት ወደ ሃይማኖት መልሷል፡፡

## ማጠቃለያ

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዓለም አቀፋዊ ታላቅ ጻድቅ ናቸው፡፡ በሰውና በእግዚአብሔር ፊት በነበራቸው ሞገስ ብዙዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስበዋል፡፡ ታኅሣሥ ፳፬ እና ነሐሴ ፳፬ ቀን የልደትና የዕረፍት በዓላቸውን እንዘክራለን፡፡ ጽናትን፣ እምነትን፣ አጋንንትን ማሸነፍን፣ ለወንጌል መትጋትን፣ ለወገን መኖርንና የጸሎትን ሕይወት ከጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እንማራለን፡፡

## ተግባር

- መምህሩ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ያደረጓቸውን ተአምራት ወጣቶች አጥንተው ለጓደኞቻቸው እንዲያካፍሉ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ከቅዱሳን አባቶች መንፈሳዊ የሕይወት ልምድን እንዲቀስሙ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፡፡ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው፡፡" ዕብ. ፲፫ ÷ ፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘዳ. ፴፪ ÷ ፯ እና (ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መግቢያ)

## መግቢያ

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በ፫፻፵፯/347/ ዓ.ም በአንጾኪያ ከተማ ተወለደ፡፡ የግሪክን ፍልስፍና በክርስትና ትምህርት ያጠመቀ ታላቅ መምህር ነው፡፡ በክርስቲያኑ ዓለም ታዋቂና ተወዳጅ ጸሐፊም ነው፡፡ ቤተክርስቲያናትን የሥራዎቹ ወራሽና አውራሽ ናት፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እስከ ሃያ ዓመቱ ድረስ የግሪክን ፍልስፍና ከታዋቂ መምህራን ዘንድ ተምሮአል፡፡ በደቡባዊ ሶርያ በሚገኙ ገዳማት የክርስትናን ትምህርት ተምሮ፤ በክርስቶስ አምኖ በመጠመቅ የክርስትናን ጉዞ ጀመረ፡፡ የአባቶቹን መንገድ በመከተል የምንኩስና ሕይወትን መረጠ፡፡ በትምህርቱ፣ በምርምሩና በሕይወቱ ጥንካሬ ዝነኛ ሆነ፡፡ ለዚህም ከእናቱ ሞት በኋላ በቋጥኝ ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ለሁለት ዓመታት ያለ ዕረፍት ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ፣ በጸሎትና በተመስጦ መቆየቱ አስተዋጽኦ እንዳደረገለት ብዙዎች ይናገራሉ፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በጵጵስና መዓርግ የአንጾኪያ ቤተክርስቲያንን አገልግሏል፡፡ ብዙ አንድምታዊ/የትርጓሜ/ መጻሕፍትን ጽፏል፡፡ የብዙዎችን ሕይወት የቀየሩ ስብከቶቹም "አፈወርቅ" አስብለውታል፡፡ የትምህርቱ ማዕከል ለሰው የተገለጠው የእግዚአብሔር የማይለወጥ ፍቅር ነው፡፡ ጽሑፎቹ ነገረ ሃይማኖት ላይ ያተኩራሉ፡፡ ስብከቶቹ ክርስቲያን በማኅበራዊ ሕይወት እንዴት መኖር እንዳለበት ይጠቁማሉ፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "የድሆች ጠበቃ" "የቤተክርስቲያን ጠበቃ" እየተባለ ይጠራል፡፡ ለድሆች ህልውናና ለቤተክርስቲያን ልዕልና የቀና ታላቅ አባት ነበርና፡፡ "ሃብታምና ድሃ" የሚለው መጽሐፉ ይህን ተቆርቋሪነቱን በሚገባ ይገልጻል፡፡

ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጥበብን መሻትን፣ መጻሕፍትን የመመርመር ትጋትን፣ ለድሆች ህልውና መቆምን፣ ለቤተክርስቲያን ልዕልና መቆርቆርን፣ ለክርስቶስ ወንጌል መትጋትን፣ በንጽሕና የክርስትናን ጉዞ መጓዝን፣ በዓለማውያን ትምህርት ላይ የመልካምነት ተጽእኖ ማድረግንና ትውልዱን የሚዋጅ ሥራ መሥራትን እንማራለን፡፡

## ማጠቃለያ

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የቤተ ክርስቲያን ጠበቃና አዋቂ መምህር ነው፡፡ በትምህርቱ ብዙዎችን ጠቅሟል፡፡ መንጋውን ከሐሰት ትምህርትና ከዲያብሎስ ክፋት አድኖአል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ጽሑፎች እንዲያነቡ ይጋብዛቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# በክረምት የዕረፍት ጊዜዬን እንዴት ልጠቀምበት እችላለሁ?

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ጊዜን በአግባቡ እንዲጠቀሙ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች፡፡" ዮሐ. ፱÷፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፳፭÷፴፭፣ ዮሐ. ፯÷፮፣ ገላ. ፮÷፱ እና ፩ጴጥ. ፬÷፮

## መግቢያ

ጊዜ የእግዚአብሔር ውድ ስጦታ ነው፡፡ ጊዜ ካለፈ የማንመልሰው አንድ ጊዜ ካጣነው በምንም የማንተካው ዕድል ነው፡፡ ሰው እግዚአብሔር በሰጠው ጊዜ ሰጪውን ሊያከብርና መልካም ሥራ ሊሠራበት ይገባል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የክረምት ዕረፍት ጊዜ ብዙ ሥራ ለመሥራት የምንችልበትና በአግባቡ ልንጠቀምበት የሚገባ ጊዜ ነው፡፡ በክረምት ጊዜያችን ለሥጋም ለነፍስም የሚጠቅሙ ሥራዎችን መሥራት እንችላለን፡፡ የክረምት ትምህርትና መንፈሳዊ ኮርሶች የሚሰጡት በክረምት ጊዜ ነው፡፡ በሥጋዊ ዕውቀታችን ለመጠንከርና በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ ጊዜያችንን በሚገባ ተጠቅመን መማር ይጠበቅብናል፡፡

በክረምት ጊዜ ቤተሰብ መጠየቅ፣ ደካሞችን መርዳት፣ ገዳማትን መጎብኘት፣ ለሕይወታችን ጠቃሚ ዕውቀትን የሚሰጡ መጻሕፍትን ማንበብ፣ መንፈሳዊ ልምምዶችን ማድረግና በቂ ዕረፍት ማድረግ አለብን፡፡

ብዙ ወጣቶች በክረምት ዕረፍታቸው በስንፍና ሥራ ያሳልፋሉ፡፡ ሰፈር በመረበሽና ወላጆቻቸውን በማስመረር የሚታወቁ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ሥራ መፍታት ለኃጢአት ያጋልጣል፡፡ ትምህርት ቤት የፈቀደልን የዕረፍት ጊዜ ለቀጣይ የትምህርት ጊዜና ክፍል የምንዘጋጅበት እንዲሆን እንጂ ኃጢአት እንድንሠራበት በዋዛ በፈዛዛ ጊዜውን በከንቱ እንድናባክነው አይደለም፡፡

የክረምት ዕረፍት ጊዜ ራስን ለማየት፣ ጎደሎን ለመሙላትና ለቀጣዩ የትምህርት ጊዜ ለመዘጋጀት ይጠቅመናል፡፡ የክረምት ዕረፍት ጊዜ የዕድሜያችን አካል ነው፡፡ ይህን ጊዜ በከንቱ ካባከንነው ዕድሜያችንን በከንቱ እያባከንን እንደሆነ በመገንዘብ አለበን፡፡ የዘመናችን ባለቤት እግዚአብሔር ጊዜን በአግባቡ በመጠቀም አርአያችን ነው፡፡ ስድስት ቀናት ፍጥረትን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ፡፡ እርሱ ያረፈው ሠርቶ ነው፡፡ ሰው ሠርቶ እንዲያርፍ ተፈቅዶለታል፡፡ ስለዚህ በጊዜያችን የዘመናችንን ባለቤት እግዚአብሔርን በማመስገን መልካም ልንሠራ ያስፈልጋል፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

የክረምት ዕረፍት ጊዜ ለመንፈሳዊ፣ ለማኅበራዊና ለሥጋዊ ሕይወት የሚጠቅሙ መልካም ሥራዎችን በመሥራት እንድንጠቀምበት የተሰጠን ነው፡፡ የክረምት ዕረፍት ጊዜ በበጋው ወራት ካሳለፍነው ረዥም የትምህርት ጊዜ የምናርፍበት፣ በምንወስደው የዕረፍት ጊዜ ረጋ ብለን ራሳችንን በመመርመር ድክመትና ጥንካሬያችንን የምንመለከትበትና ለቀጣዩ የትምህርት ጊዜ መዘጋጀት ነው፡፡ ጊዜን በአግባቡ እንጠቀም፤ ልንሠራ የማንችልበት ጊዜ ይመጣልና፡፡

## ተግባር

- መምህሩ፤ "በክረምት የዕረፍት ጊዜዬን እንዴት ልጠቀምበት እችላለሁ?" በሚል ርእስ ወጣቶችን ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የመንፈሳዊ ሕይወት ማነቆዎች

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የመንፈሳዊ ሕይወት ማነቆዎችን በማወቅ እንዲጠነቀቁ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በእሾህ መካከል ወደቀ፤ እሾህም ወጣና አነቀው፡፡" ማቴ. ፲፫÷፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፲፫÷፩-፳፫

## መግቢያ

መንፈሳዊ ሕይወት በየጥቂቱ የሚያድግ ሕይወት ነው፡፡ መንፈሳዊ ሕይወት እግዚአብሔርን በማወቅ እግዚአብሔርን ወደ መምሰል የምናድግበት፤ ከክፉ በመራቅ መልካምነትን የምናበዛበት ሕይወት ነው፡፡ መንፈሳዊ ሰው የእድገት ማነቆዎች አሉበት፡፡ እድገቱ እንዳይገታ ከማነቆዎቹ መጠንቀቅ፣ መራቅና የተያዘበትን የክፋት ማነቆ መስበር ይጠበቅበታል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዘሪውን ምሳሌ ሲያስተምር፤ ዘሩ ያረፈበትን ሦስተኛውን መሬት "እሾህ የበዛበት" በማለት ገልጾታል፡፡ መንፈሳዊ ሕይወትም እንዲሁ በብዙ መከራ መካከል የሚያልፍ ነው፡፡ "ዘር ሊዘራ ወጣ ዘሩም በእሾህ መካከል ወደቀ፤ እሾህም ወጣና አነቀው፡፡ ይህ ቃሉን የሚሰማ ነው፡፡ የዚህ ዓለም አሳብና የባለጠግነት መታለል (ፍቅረ ዓለምና ፍቅረ ንዋይ) ቃሉን ያንቃል፤ የማያፈራም ይሆናል፡፡" በማለት ጌታ አስተምሮናል፡፡ ማቴ. ፲፫÷፩-፳፫፡፡

የመንፈሳዊ ሕይወት ማነቆዎች ብዙ ናቸው፤ በክርስቶስ አስተምህሮ ፍቅረ ዓለምና ፍቅረ ንዋይ ተብለው ተጠቃለዋል፡፡

**ፍቅረ ዓለም፡-** የዓለም ሐሳብ፣ የሥጋ ምኞትና የዐይን አምሮት ፍቅረ ዓለም ይባላሉ፡፡ የዓለም ሐሳብ የመንፈሳዊውን ሰው ጉዞ ይገታል፤ ዕድገቱን ያቀጭጫል፡፡ የዓለም ሐሳብ የመንፈሳዊ ሕይወት ማነቆ ሆኖ በልቡ ማሳ የተዘራው ሕያው ቃል ፍሬ እንዳያፈራ ይይዘዋል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ "ዓለም ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፡፡ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት . . . ከአባት ስላልሆነ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም፡፡ ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል፡፡" በማለት አስተምሯል፡፡ ፩ዮሐ. ፪÷፲፮-፲፯፡፡

www.zoorthodox.org

ፍቅረ ዓለም ማለት ዓለምንና በዓለም ያሉትን መውደድ ማለት ነው፡፡ የዓለም ፍቅር በልባችን ካለ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ውስጥ አይኖርም፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ ትልቁ ኃይል የእግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡ የሚያልፈውን የዓለምን ምኞት በመተው የማያልፈው የእግዚአብሔርን ፍቅር መያዝና መኖር አለብን፡፡

**ፍቅረ ንዋይ፡-** ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነው፡፡ የዓለም ባለጠግነትን በማሰብ የሚታለሉ በጥፋትና በመፍረስ

ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ፡፡ ይህን የተመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ስቃይ ራሳቸውን ወግተዋልና፡፡ **፩ጢሞ. ፮÷፮-፲**፡፡

ገንዘብን በራሳችን ትክክለኛ ጥረትና ሥራ ማግኘት፤ አግኝቶም ኑሮን በአግባቡ ለመምራትና መልካም ሥራን ለመሥራት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ገንዘብን ሕገወጥ በሆነ መንገድ ለማግኘት፣ ስለ ገንዘብ መታለል፣ መጥፋትና መፍረስ አያስፈልግም፡፡ የገንዘብ ፍቅር የመንፈሳዊ ሕይወት ማነቆ ነው፡፡

ጌታችን ኢየሱስን ዲያብሎስ በፍቅረ ንዋይ ሲፈትነው በጸሊዓ ንዋይ (ገንዘብን በመጥላት) ድል ነሥቶታል፡፡ ማቴ. ፬÷፱፡፡ **ገንዘብን የሚወዱ እንኳን በመንፈሳዊ** ሕይወት ሊያድጉ በብዙ ስቃይ ራሳቸውን በመውጋት ይጠፋሉ፡፡

ትዕቢት፣ ዝሙት፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንዓት፣ ቁጣ፣ አድመኝነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነትና ርኩሰት የመንፈሳዊ ሕይወት ማነቆዎች ናቸው፡፡ እነዚህን የሥጋ ሥራዎች የሚሠሩ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው መሻሻል አይታይባቸውም፡፡ በመንፈስ ፍሬዎች ያጌጠ ማንነት ግን የመንፈሳዊ ሕይወት መሠረትና ድምድማት ነው፡፡ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ አደገ የሚባለው የመንፈስ ፍሬዎችን ገንዘብ ሲያደርግ ነው፡፡ ገላ. ፭÷፲፰-፳፬፡፡

## ማጠቃለያ

የዓለም አሳብ፣ የሥጋ ምኞት፣ የዓይን አምሮት፣ የሥጋ ሥራዎች ሁሉ የመንፈሳዊ ሕይወት ማነቆዎች ናቸው፡፡ በልባችን እርሻ የተዘራው ቃሉ እንዲያፈራ ከእነዚህ የሥጋ ምኞትና ፍሬዎች ሁሉ እንራቅ፡፡

## ተግባር

- መምህሩ “በመንፈሳዊ ሕይወት እንዴት ማደግ ይቻላል?” በሚል ርእስ ወጣቶችን ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# መንፈሳዊ ቅንዓትና ትጋት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች በትጋትና በመንፈሳዊ ቅንዓት በጽድቅ እንዲመላለሱ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት፡፡" ቆላ. ፫፥፳፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሮሜ. ፲፪፥፰፣ ዕብ. ፮፥፲፩፣ ፪ጴጥ. ፩፥፳፣ ያዕ. ፫፥፲፮ እና ፪ቆሮ. ፯፥፯

## መግቢያ

***ትጋት፡-*** ለመንፈሳዊ ሕይወት ጉልበት ነው፡፡ ትጋት ለእግዚአብሔር የተለዩ ወገኖች ምልክት ነው፡፡ ለሥራ የሚለግሙና የስንፍናን ሥራ የሚያዘወትሩ ከእግዚአብሔር አይደሉም፡፡

***ቅንዓት፡-*** ሥጋዊና መንፈሳዊ ቅንዓት ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ ሥጋዊ ቅንዓት ምቀኝነት ይባላል፤ የሥጋ ፍሬ ነው፡፡ ገላ. ፭፥፳፡፡ ***መንፈሳዊ ቅንዓት እንደ ሌሎች*** ደጋግና ጠንካራ ሰዎች ለደግ ሥራ የመትጋትና መልካም የመሆን በጎ ምኞት ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ትጋትና መንፈሳዊ ቅንዓት ለወጣቶች አስፈላጊ ናቸው፡፡ መንፈሳዊ ቅንዓት ያደረባቸው ለደግ ሥራ ይተጋሉ፡፡ ሥጋዊ ቅንዓት ወጣቶችን የሚፈትንና ለኃጢአት የሚያጋልጥ የርኩሰት መንገድ ነው፡፡ በኃጢአተኞች መቅናት ተገቢ አይደለም፡፡ ምሳሌ ፳፬፥፩፡፡ ***ንስሐ በሚገቡት መቅናት ግን*** መንፈሳዊ ቅንዓት ይባላል፡፡ ራእ. ፫፥፲፱፡፡

***ትጋት***፡- የጠንካራ ሰብዕና መገለጫ ነው፡፡ ትጋት ከእግዚአብሔር ፍቅር ይመነጫል፡፡ የትጋት ፍሬ በረከት ነው፡፡ ትጉህ ሰው መከራና የጠላት ወጥመድ ጉዞውን አይገታውም፡፡ የትጉህ ሰው ልብ ሠርቶ አይጠግብም፤ በትናንት ደግነቱ ረክቶ አይቀመጥም፤ ደግ ሥራ ከመሥራት ሳይለይ መልካም መዝገብ ያባዛል፡፡ ክብሉይ ኪዳን ሰዎች ነህምያ፤ ከሐዲስ ኪዳን አገልጋዮች ቅዱስ ጳውሎስ የትጋት አርአያዎች ናቸው፡፡ መጽሐፈ ነህምያ የነህምያን የትጋት ፍሬ መዝግቧል፡፡ ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለመሥራት በመንፈሳዊ ቅንዓት ተነሣሥቶ በትጋት ጀመረ፡፡ ሰንበላጥና ጦብያ የትጋቱን ጉዞ የሚገታ ወጥመድ በመንገዱ አስቀመጡ፡፡ ነህምያ ግን በትጋት ዓላማውን አሳካ፡፡ እግዚአብሔር የትጉሃንን ክንድ እንደሚያበረታና መንገዳቸውን እንደሚያቀና የነህምያ ሕይወት ማስረጃ ነው፡፡

www.zoorthodox.org

ጳውሎስ "በአገልግሎታችን እንትጋ" በማለት ያስተማረ፤ በትጋት ያገለገለ ታላቅ ሐዋርያ ነው፡፡ ሮሜ. ፲፪፥፰፡፡ ***አማኞች በእምነትና በትዕግሥት*** የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንዲመስሉ የመጀመሪያ ትጋታቸውን ተስፋ እስኪሞላ እንዲያሳዩ

መክሮአል፡፡ ዕብ. ፮÷፲፩፡፡ **ቅዱስ ጴጥሮስም "ትጋትን አሳዩ"** በማለት አስተምሯል፡፡ **፪ጴጥ.** ፩÷፫፡፡

***መንፈሳዊ ቅንዓት፡-*** የትጋት መሠረት ነው፡፡ ለበጎ የሚቀኑ በጎ ለመሥራት ይተጋሉና፡፡ የነህምያ የትጋት ምንጭ ስለኢየሩሳሌም መቅናቱ ነበር፡፡ የጳውሎስም የትጋት ምንጭ በፊተኛው ሕይወቱ ለኦሪት የነበረው ቅንዓት በኋላም ለክርስቶስ ወንጌል መቅናት ነበር፡፡ ኤልያስ ስለ እግዚአብሔር ቀንቷል፡፡ ሮሜ. ፲፩÷፫፡፡ ***ሥጋዊ ቅንዓት ለኃጢአት ያነሣሣል፡፡*** መንፈሳዊ ቅንዓት መልካም ለመሥራት ያነሣሣል፡፡

ያለእውቀት የሆነ ቅንዓት ያጠፋል፡፡ ያለ በጎ ቅንዓት የሆነ ዕውቀትም አይጠቅምም፡፡

## ማጠቃለያ

ትጋትና መንፈሳዊ ቅንዓት ለሕይወታችን ያስፈልጋሉ፡፡ መልካም ቅንዓት ለሥራ የነሣሣል፤ ትጋት ደግሞ ሥራን ወደ ተግባር ምኞትን ወደ ፍጻሜ ያመጣል፡፡ ቅንዓት የትጋት መሠረት ነው፡፡ ትጋት ደግሞ መልካም የሆነው የመንፈሳዊ የቅንዓት ፍሬ ነው፡፡ የትጋት ፍሬ እግዚአብሔርን የሚያከብርና ሰውን የሚጠቅም ሥራ ነው፡፡ የምናደርገውን ሁሉ በትጋት እናድርግ፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ከዛሬው ትምህርት ምን እንደተማሩ ወጣቶችን ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የብዙኃን መገናኛ ተፅዕኖ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ለሕይወት መልካም የሚሆነውን ነገር መርጠው እንዲጠቀሙ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሁሉ ተፈቅዶልኛል፤ ሁሉ ግን አይጠቅምም፡፡ በእኔ ላይ አንድ ነገር እንኳ አይሠለጥንብኝም፡፡" ፩ቆሮ. ፮፥፲፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ጴጥ. ፪፥፲፩-፲፪ እና ቲቶ. ፫፥፰-፲፩

## መግቢያ

ብዙኃን መገናኛ /ሚዲያ/ በጎም ሆነ ክፉ ተፅዕኖ በሰው አእምሮ ላይ መፍጠር የሚችል የመረጃ ምንጭ ነው፡፡ ሚዲያ /ብዙኃን መገናኛ/ በድምፅ፣ በምስልና በጽሑፍ የሚቀርብ ከፍተኛ አቅም ያለው የዓለም እንቅስቃሴዎች አንደበት ነው፡፡ የመሪዎች ድምፅ፣ መልካምና ክፉ ክሥተቶች ወቅታዊ የዓለም ወሬ፣ የቴክኖሎጂ እድገት፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ ወዘተ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች፣ የማኅበረሰቡ የሕይወት ልምድ ወዘተ. . . በሚዲያ ሽፋን ያገኛል፡፡ ብዙኃን መገናኛ /ሚዲያ/ ብዙ የመልካምነት ተፅዕኖ እንዳለው ሁሉ ጉዳትም አለው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

***፩. የብዙኃን መገናኛ /ሚዲያ/ በጎ ተፅዕኖ፡-*** ብዙኃን መገናኛ /ሚዲያ/ የመረጃ ምንጭ ነው፡፡ የትምህርት፣ የሥልጣኔ፣ የታሪክ፣ የአዳዲስ ግኝቶች፣ የዓለም የውሎ ጦርነትና ሰላም፣ እድገትና ብልጽግና፣ ረኃብና ድህነት ሪፖርትና የሃይማኖታዊ መልእክት መግለጫ ነው፡፡ ብዙኃን መገናኛ /ሚዲያ/ ለበጎ ሥራ ሰዎችን ማንቂያ ደወል ነው፡፡ በአበው ሃይማኖት ተመሥርተን ከዘመኑ ጋር እንድንሄድ አስተዋጽዖ አለው፡፡ ሚዲያ ለመረዳዳት፣ ባህልንና መልካም ልምዳችንን ለመለዋወጥ፣ ዓለም የደረሰችበትን የሥልጣኔ እድገት ለማወቅ፣ ያለንን በጎ ነገር ለሌሎች ለማካፈልና ጠቃሚ መረጃዎች ለማቀበል ይጠቅማል፡፡ በውጪው ዓለም የዓየር ጠባይ ሁኔታ በየዕለቱ ስለሚገልጽ ሚዲያ የየዕለት እንቅስቃሴ መሪ ኮምፓስ ነው፡፡ ብዙኃን መገናኛ /ሚዲያ/ በርካታ በጎ ተፅዕኖዎች አሉት፡፡

www.zeorthodox.org

***፪. የሚዲያ ክፉ ተፅዕኖ፡-*** ብዙኃን መገናኛ /ሚዲያ/ ክፉ ልምዶችንና ኃጢአቶችን ለማስፋፋት መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ የዝሙት፣ የክህደት፣ የዘፈንን፣ የዓመጽ፣ የወንጀል ወዘተ ማስፋፊያ ይሆናል፡፡ በብዙኃን መገናኛ /ሚዲያ/ በሚያዩዋቸው የዝሙት ፊልሞች የርኩሰትን መንገድ የተከተሉ፤ በሚያነቡአቸው የክህደት መጻሕፍት ከሃይማኖት የወጡ፤ በሚሰሙአቸው የዘፈን ዜማዎች ዓለም የማረከቻቸው አማኞችና በሚመለከቷቸው የግድያ ፊልሞች ሰው ለመግደል የተነሡ ሰዎች ብዙ ናቸው፡፡ ሚዲያ በአዎንታዊ ወይም በጎ ተፅዕኖው የጠቀማቸው እንዳሉ ሁሉ በአሉታዊ ወይም ክፉ ተፅዕኖው የተጎዱም አሉ፡፡

**፫. ብዙኃን መገናኛ/ሚዲያ/ን እንዴት እንጠቀም?** ሚዲያን የሚከለክል የክርስትና ትምህርት የለም፤ ሚዲያ ሁሉ ግን አይጠቅምም፡፡ ክርስቲያን የተፈቀደለትን ሁሉ እያግበሰበሰ አይጠቀምም፤ መልካሙን በመምረጥ የሚጠቅመውን ይይዛል፡፡ የብዙኃን መገናኛ /ሚዲያ/ ሱሰኛ መሆን አያስፈልግም፡፡ በማኅበረሰብ ድረ ገጾች ሱስ የተያዙ ጊዜና ገንዘባቸውን የሚያባክኑ ብዙዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ሚዲያ ስንጠቀም፡-

የአምልኮ፣ የሥራና የትምህርት ጊዜያችንን በማይነካ መልኩ

ለሕይወት የሚጠቅመውን በመምረጥ

አንድ ነገር እንኳ እንዳይሠለጥንብን (ክፉ ተፅዕኖ እንዳይዘን) በመጠንቀቅና

መልካም በሆነው ለመጠቀም በመወሰን መሆን አለበት፡፡

## ማጠቃለያ

ብዙኃን መገናኛ /ሚዲያ/ ጠቃሚም ጎጂም ነገሮች ሊኖሩት ይችላል፡፡ አጠቃቀማችንና አመራረጣችን ውጤቱን ይወስናል፡፡ ክርስቲያን የተፈቀደለትን ሁሉ ሳይሆን የሚጠቅመውንና ለመልካም ሥራ የሚበጀውን እየመረጠ ያደርጋል፡፡ ሁሉን እንፈትን መልካሙን እንያዝ፡፡ **፩ተሰ.** ፭÷፳፩፡፡

## ተግባር

✍ መምህሩ "የብዙኃን መገናኛ /ሚዲያ/ በጎና ክፉ ተፅዕኖዎች ምንድን ናቸው?" በሚል ርእስ ወጣቶችን ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# በጎ ሥራ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ለበጎ ሥራ ክንዳቸውን እንዲያጠነክሩ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሁንላቸው፡፡" ሮሜ. ፪÷፲

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሮሜ. ፲፪÷፱

## መግቢያ

በጎ ሥራ ከበጎ ሕሊና የሚመነጭ የእምነት መገለጫ ነው፡፡ በጎ ሥራ በእግዚአብሔርና በሥራው ያመነ ሰው የጽድቅ ፍሬ ነው፡፡ በጎ ሥራ ከበጎው ከእግዚአብሔር የመነጨ ነው፡፡ በጎ ሥራ የሚሠሩ ሁሉ በሰውም በኢግዚአብሔርም ፊት ሞገስ አላቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የበጎ ነገር ምንጭ እንደሆነና እንደ ሐሳቡ ተጠርተው ለሚወዱት ነገርን ሁሉ ለበጎ እንደሚያደርግ ይመሰክራል፡፡ ሮሜ. ፰÷፳፰፡፡ **በጎ ሥራ በቅዱስ ጳውሎስ፣** በቅዱስ ጴጥሮስ፣ በቅዱስ ዮሐንስና በቅዱስ ያዕቆብ መልእክታት ተሰብኳል፡፡ መልእክታቱ አማኞች ሳይታክቱ በጎ እንዲሠሩ ያስተምራሉ፡፡ የበጎ ሥራ ጥሪዎች በመልእክታቱ የተብራሩበት መንገድ፡-

- ከበጎ ነገር ጋር መተባበር፡፡ ሮሜ ፲፪÷፱
- በጎ ለመሥራት ጥበበኛ መሆን፡፡ ሮሜ ፲፯÷፲፱
- ለበጎ ሥራ መብዛት፡፡ **፪ቆሮ.** ፱÷፰
- በበጎ ሥራ ፍሬ ማፍራት፡፡ ቆላ. ፩÷፲
- በጎ ለመሥራት አለመታከት፡፡ ኤፌ. ፮÷፱
- የበጎ ሥራ ባለጠጋ መሆን፡፡ **፩ጢሞ.** ፮÷፲፰-፳
- ስለ በጎ ሥራ መከራን መቀበል፡፡ **፩ጴጥ.** ፫÷፲፯
- በጎን መምሰል፡፡ **፫ዮሐ.** ፲፩
- ያወቅነውን በጎ ሥራ አለመፈጸም የሚያመጣውን ኃጢአት፡፡ ያዕ. ፬÷፲፯

www.zeorthodox.org

እኛም በጎ ሥራ የሚሠሩትን መተባበር፣ ለበጎ ሥራ መሰባሰብ፣ በጎ ለመሥራት አለመታከት፣ በጎ ሥራን በመከራም ቢሆን ጸንቶ መሥራት፣ በጥበብ እና በማስተዋል እየተመራን በጎ ሥራ በመሥራት በጎ ፍሬ ማፍራት ይጠበቅብናል፡፡ እግዚአብሔር

ከሕይወታችን የሚፈልገው ፍሬ በጎ ሥራ ነው፡፡ በጎ ሥራ የእውነተኛ እምነት መገለጫ በመሆኑ በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት ያስከብራል፡፡ በጎ ሥራ የሚሠሩ ሕይወታቸው ካለፈም በኋላ መልከም ሥራቸው ለመጪው ትውልድ ሁሉ ሲያስተምር አርአያነታቸውን ሲናገር ይኖራል፡፡ አቤል ሞቷል፤ ነገር ግን በመሥዋዕቱ እስከ አሁን ሕያው ሆኖ ይናገራል፡፡፡ በጎ ሥራ ዘመን ተሻጋሪ ባለታሪክ ያደርጋልና፡፡ ዕብ. ፲፩÷፬፡፡ **የበጎ ሰዎችን በጎ ሥራ መቃብር** አያስቀረውም፡፡

በጎ ማድረግ የሁልጊዜ ተግባር ነው፡፡ በሰንበት እንኳ በጎ ማድረግ ተፈቅዷል፡፡ ማር. ፫÷፬፡፡ **በጎ ሥራ የጊዜ ገደብ የለውም**፡፡ ሰው ከበጎ ሥራ ጡረታ አይወጣም፤ በጎ ሥራ የዘመን ሁሉ ተግባር ነውና፡፡

## ማጠቃለያ

በጎ ሥራ እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው የጽድቅ ፍሬ ነው፡፡ የእውነተኛ እምነት መገለጫ የሆነው በጎ ሥራ በማንኖርበት ዘመን ሁሉ ስለ እኛ ሲናገር መልካም ሥራችንን ሲመሰክር ይኖራል፡፡ በጎ ሥራ የጊዜ ገደብ የለውም፡፡ ሰው በዘመኑ ሁሉ በጎ ሊያደርግ በክርስቶስ ዳግም ተፈጥሮአልና፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ‹‹በጎ ሥራ ምንድን ነው?›› በሚል ርእስ ወጣቶችን ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# በጎ ኅሊና

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች በጎ ሕሊናን ገንዘብ እንዲያደርጉ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በሰውና በእግዚአብሔር ፊት ሁል ጊዜ ነውር የሌለበት ሕሊና ትኖረኝ ዘንድ እተጋለሁ፡፡" ሐዋ. ፳፬÷፲፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሐዋ. ፳፫÷፩፣ ሮሜ. ፪÷፲፭፣ ፩ቆሮ. ፲÷፳፱ እና ዕብ. ፲÷፳፪፤፲፫÷፲፰

## መግቢያ

- ሕሊና ምንድን ነው?
- የበጎ ሕሊና መገለጫዎች ምንድን ናቸው?
- ሕሊናን ማታለል ይቻላል?
- ሕሊና ክፉዎችን ለምን ይወቅሳል?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሕሊና በሰው አካል ውስጥ እንደ ዳኛ የሚያገለግል አምላካዊ ሕግ የተጻፈበት ሰሌዳ ነው፡፡ ሕሊና ክፉና ደጉን መለያ፤ የሞትን መንገድ ለጀመሩት የማንቂያ ደወል ነው፡፡ የክርስቲያን ሕሊና ንጹሕ፣ ንቁ፣ ትጉህና በጎ መሆን አለበት፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሕግ በሰው ሕሊና ላይ መጻፉን ይነግረናል፡፡ የጽሑፍ ሕግ የሌላቸው አሕዛብ በሕሊናቸው ሕግ እንደሚጠየቁ ይመሰክራል፡፡ ሮሜ. ፪÷፲፭፡፡ **ሰው የሕሊናውን ጩኸት መስማት** አለበት፡፡ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን ሕግ በልባችን ጽፏል፡፡ ዕብ. ፰÷፲፡፡ **በውስጣችን የተጻፈውን በመፈጸም** በሕይወታችን እንግለጸው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ነውር የሌለበት በጎ ሕሊና እንድትኖረው የተጋ ሐዋርያ ነው፡፡ ሐዋ. ፳፫÷፩፤ ፳፬÷፲፮፡፡ **በትምህርቱ ሕሊናን በሦስት** ክፍል አስተምሮአል፡፡

**፩. በጎ ሕሊና፡-** በጎ ሕሊና የበጎ ሥራ ምንጭ ነው፡፡ በሰውና በእግዚአብሔር ፊት ነውር የለበትም፡፡ በጎ ሕሊና የመልካም አኗኗር መሠረት ነው፡፡ ዕብ. ፲፫÷፲፰፤ **ሐዋ. ፳፬÷፲፮፡፡ የመንፈስ ልጁን ጢሞቴዎስን** "ይህችን ትእዛዝ አደራ እሰጥሃለሁ እምነትና በጎ ሕሊና ይኑርህ፡፡ አንዳንዶች ሕሊናን ጥለው መርከብ አለ መሪ እንደሚጠፋ በእምነት ነገር ጠፍተዋልና" በማለት መክሮአል፡፡ ፩ጢሞ. ፩÷፲፱፡፡ **በጎ ሕሊና የአማኝ መሪ ነው፡፡** መርከብ ያለ መሪ እንደሚጠፋ ሁሉ አማኝም ያለ በጎ ሕሊና በጽድቅ መንገድ መጓዝ አይችልም፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ጴጥሮስ "በክርስቶስ ያለውን መልካሙን ኑሮአችሁን የሚሳደቡ ለሰዎች ክፉን እንደምታደርጉ በሚያሙበት ነገር

እንዳያፍሩ በጎ ሕሊና ይኑራችሁ፡፡” በማለት በጎ ሕሊና የሃሜተኞች አፍ መዝጊያ እንደሆነ ገልጾአል፡፡ **፩ጴጥ.** ፫÷፲፮፡፡

በጎ ሕሊና ያላቸው ሰዎች ለባልንጀሮቻቸው ሕሊና ይጠነቀቃሉ፡፡ **፩ቆሮ.** ፲÷፳፱፡፡

**፪. የረከሰ ሕሊና፡-** ቅዱስ ጳውሎስ እግዚአብሔርን የማያምኑና አውቀውት በሥራቸው የሚክዱትን ሰዎች አእምሮአቸውና ሕሊናቸው ረክሷል ይለናል፡፡ ቲቶ. ፩÷፲፭፡፡ **ሕሊናን የሚያረክሰው አለማመንና** አለመታዘዝ ነው፡፡ ኃጢአት ሕሊናን የሚያቆሽሽ ነውር ነው፡፡ ያላመኑ ሰዎች በጥምቀት፤ ያመኑ ሰዎች ደግሞ በክርስቶስ ደም ተረጭተው ከክፉ ሕሊናቸው መንጻት ከረከሰ ሕሊናቸው መቀደስ ይችላሉ፡፡ ዕብ. ፲÷፳፪፡፡

**፫. የደነዘዘ ሕሊና፡-** በቅዱስ ጳውሎስ አስተምህሮ የአጋንንትን ትምህርት የሚያደምጡ፣ ሃይማኖትን የሚክዱና የሚያስክዱ ሰዎች ሕሊናቸው ደንዝዞአል፡፡ የደነዘዘ ሕሊና ያላቸው ሰዎች የሕይወት ዕውቀት ይርቃቸዋል፡፡ የደነዘዘ ሕሊና ለተንኮል የሚተጋ፣ ስቶ የሚያስትና ጠፍቶ የሚያጠፋ ማንነት ነው፡፡

## ማጠቃለያ

በጎ ሕሊና የበጎ ሥራ ምንጭ፤ የመልካምነትና የቅንነት መዝገብ ነው፡፡ በጎ ሕሊና በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት በሞገስ ነው፡፡ በጎ ሕሊና ለነገሮች ያለንን እይታ አዎንታዊ ያደርገዋል፡፡ ክርስቲያኖች ከክፉ፣ ከደነዘዘና ከረከሰ ሕሊና ርቀን በጎ ሕሊና እንዲኖረን ልንተጋ ይገባል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ‹‹የበጎ ሕሊና ጥቅም ምንድን ነው?›› በማለት ወጣቶቹን ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ቃልን ማክበር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ቃላቸውን እንዲያከብሩ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህ፤ ከቃልህም የተነሣ ትኮነናለህ፡፡" ማቴ. ፲፪÷፴፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዮሐ. ፲፯÷፮ እና ያዕ. ፩÷፳፪

## መግቢያ

- ለቃላችሁ ታማኝ ናችሁ?
- ቃልን የማክበር ጥቅም ምንድን ነው?
- ቃልን አለማክበር የሚያመጣው ችግር ምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቃል ትልቁ የማንነት መገለጫ ነው፡፡ ቃልን ማክበር የታማኝነት ምልክት ነው፡፡ በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት ያስከብራል፡፡ ቃልን ማክበር ከእግዚአብሔር የተማርነው ሥርዓት ነው፡፡ እግዚአብሔር አዳምን "ተወልጄ አድንሃለሁ" አለው፡፡ ቃሉን አክብሮ መጣ፤ ተወለደ፤ አዳነን፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ያን ሁሉ መከራ የተቀበለው ቃሉን ለማክበር ነበር፡፡ ቃሉን ለማክበር ሕይወቱን ከፍሏል፤ የእርሱ የሆኑትም ቃላቸውን ይጠብቃሉ፡፡ ዮሐ.፲፯÷፮፡፡ **በጥንት ዘመን ብዙዎች ለቃላቸው** ሲሉ ዋጋ ይከፍሉ ነበር፡፡ በአሁኑ ዘመን ግን ሰዎች ሳያስተውሉ ቃል ይገባሉ፤ ቃላቸውንም ተጠንቅቀው አያከብሩም፡፡ ቃላቸውን የማያከብሩ ባካኝ ሰዎች በዝተዋል፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ቃሉን ሊያከብር እንደሚገባ አስተምሯል፡፡ በዳግም ምጽዓት የፍርድ ቀን የከንፈራችንን ፍሬ እንደምናጭድ ተናግሯል፡፡ "ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤ ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና ከቃልህም የነሣ ትኮነናለህና" በማለት፡፡ ማቴ. ፲፪÷፴፮-፴፯፡፡ **እግዚአብሔር ለሕዝቡ** ቃል የገባውን በመፈጸም የታመነ ነውና የሚያምኑት ሁሉ ቃላቸውን በመፈጸም ይመስሉታል፡፡ ቃሉን የማያከብር ሰው በምድር ማንም አያምነውም፤ አያከብረውም፡፡ በዕለተ ምጽዓትም ይቀጣል፡፡

www.zeorthodox.org

ቃልን ማክበር ታማኝነትና ክብርን ወዳጅነትና ፍቅርን ያተርፋል፡፡ ቃላችንን አክብረን በተገኘን ቁጥር ሌሎች በእኛ ላይ የሚኖራቸው እምነት ይጠነክራል፤ እነሱም ቃላቸውን አክብረው እንዲገኙልን ያደርጋል፡፡ ቃልን ማክበር የማንነት መገለጫ ነው፡፡ ቃልን ማክበር በመርሐ ግብር የተደገፈ የኑሮ ሥርዓት እንዲኖረን እና ጊዜያችንን በአግባቡ እንድንጠቀምበት ያስችለናል፡፡

## ማጠቃለያ

የሰው ክብሩ ቃሉን ማክበሩ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን የከፈለው ለአባቶቻችንን የገባውን ቃልኪዳን ለመፈጸም ነው፡፡ ቃልን ማክበር እጅግ ታላቅ ነገር በመሆኑ ዋጋውም ሕይወትን እስከመክፈል የሚደርስ ነው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶችን ‹‹ቃልን ስለ ማክበር›› ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ገንዘብና ክርስቲያናዊ ሕይወት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የማያልፈውን ባለጠግነት ተስፋ እንዲያደርጉ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ገንዘብ መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነው፡፡" ፩ጢሞ. ፮÷፲

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃስ ፲፪÷፲፫፣፳፩፣ ፩ጢሞ. ፮÷፮-፲፱ እና ዕብ. ፲÷፴፬

## መግቢያ

- ክርስቲያናዊ ሕይወት ገንዘብን ያወግዛልን?
- የዓለም ባለጠግነትና ክርስቲያናዊ ሕይወት እንዴት አብረው ይሄዳሉ?
- ገንዘብ በክርስቲያናዊ ሕይወት ተፅዕኖ አለው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

***፩. ገንዘብ መሰብሰብ፡-*** ክርስቲያን በትክክለኛ መንገድ ገንዘብ ለማግኘት ይሠራል፡፡ እግዚአብሔርን በመፍራት እየሠራ በትክክል የሚያገኘውን የድካሙን ፍሬ ያከማቻል፡፡ እግዚአብሔርን የሚያምኑ ከክፉ ርቀው በንጽሕና መንገድ ገንዘብ መሰብሰብ ይችላሉ፡፡ "ከእኔ ጋር የማያከማች ይበትናል፡፡" እንዳለ ጌታ ከእርሱ ጋር ሆነው የማያከማቹ በታኞችን እንጂ አማኞች በየተሰማሩበት ሞያና የሥራ መስክ በትክክል ሠርተው የድካማቸውን ፍሬ እንዳያከማቹ ገንዘብ እንዳይኖራቸው የሚከለክል አስተምህሮ የለም፡፡ ማቴ. ፲፪÷፴፣ ፩ጢሞ. ፮÷፲፰፡፡

***፪. የገንዘብ አጠቃቀም፡-*** ክርስቲያን በንጽሕና ከጌታ ጋር ያከማቸውን ገንዘብ በአግባቡ ይጠቀማል፡፡ ገንዘቡን ለሥጋዊ ኑሮውና ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ጥቅም ላይ ያውለዋል፡፡

***፪.፩. በሰማይ ማከማቸት፡-*** አማኞች ብልና ዝገት በማያጠፉት ሌቦች በማይሠርቁት በሰማያዊው መዝገብ (ባንክ ቤት) ገንዘባቸውን ያከማቻሉ፡፡ ክርስቶስ "በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ" እንዳለ፡፡ ማቴ. ፮÷፳፩፡፡ **ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ባለጠጎችን** እንዲመክር ሲያዝዝ "ለሚመጣው ዘመን ለራሳቸው መልካም መሠረት የሚሆንላቸውን መዝገብ እየሰበሰቡ መልካምን እያደረጉ በበጎም ሥራ ባለጠጎች እንዲሆኑ ሊረዱና ሊያካፍሉም የተዘጋጁ እንዲሆኑ ምከራቸው" ብሏል፡፡ **፩ጢሞ. ፮÷፲፯-፲፱**፡፡

www.zeorthodox.org

ያመነ ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ የበጎ ነገር ባለጠጋ በመሆን ገንዘብን ማከማቸት ይጠበቅበታል፡፡ ሉቃ. **፲፪÷፳፩፡፡ እንደ ፈቃዱ ያከማችነውን ገንዘብ** ለድሆች በማካፈል፣ ዐሥራታችንን በማውጣትና ለቃሉ መስፋት በመሥራት በሰማይ መዝገብ

እናከማቻለን፡፡ ዕብ. ፲÷፴፬፡፡

***፪.፪. ገንዘብን በአግባቡ መጠቀም፦*** በምድር ሥርዓት ገንዘብ ትልቅ ኃይል ነው፡፡ በገንዘባችን ደግ መሥራት እንችላለን፡፡ ገንዘብ ለሥጋዊ ኑሯችን አስፈላጊ በመሆኑ እንደፈቃዱ በንጽሕና መንገድ ሠርተን የጥረታችንን ፍሬ እንሰበስባለን፡፡ የሰበሰብነውን ገንዘብ ለአስፈላጊ ነገር በአስፈላጊው ጊዜ በአግባቡ መጠቀም ይጠበቅብናል፡፡

**፫. ገንዘብን መውደድ፡-** የገንዘብን አስፈላጊነት ማወቅና ለገንዘብ ብቻ መኖር ይለያያሉ፡፡ አማኝ በትክክል ሠርቶ የሰበሰበውን ገንዘብ ለራሱም ሆነ መልካም ሥራ ለመሥራት በአግባቡ ይጠቀምበታል፡፡ ነገር ግን በገንዘብ ፍቅር ወድቆ በክፉ መንገድ በማከማቸትና በስስት ታስሮ ገንዘብን መውደድ የለበትም፡፡ ገንዘብን በመውደድ ባለጠጋ ለመሆን የሚፈልጉ በጥፋት፣ በሚጎዳ ምኞት፣ በፈተና እና በብዙ ወጥመድ ይወድቃሉ፡፡ ገንዘብ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፡፡ ገንዘብን የሚወዱ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ስቃይ ራሳቸውን ወግተዋል፡፡ **፩ጢሞ ፮÷፲**፡፡

ገንዘብን አለመውደድ ሲባል ለገንዘብ አለመገዛትን፣ ገንዘብን በወንጀል በክፉ መንገድ ለማግኘት ለመሰብሰብ አለመፈለግን፣ ስስትን፣ በገንዘብ አለመመካትንና በገንዘብ አለመደገፍን ያጠቃልላል፡፡

***፫.፩. አለመጎምጀት፦*** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "የሰው ሕይወት በገንዘብ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ፤ ከመጎምጀትም ሁሉ ተጠበቁ፡፡" በማለት አስተምሯል፡፡ ሉቃ. ፲፪÷፲፭፡፡

***፫.፪. በገንዘብ አለመመካት፦*** ክርስቲያን በእግዚአብሔር ብቻ ይመካል፤ ይደገፋል፡፡ **፩ቆሮ. ፩÷፴**፡፡ **ባዕለ ጠጎች አትርፎ** በሚሰጠው በእግዚአብሔር እንጂ በሚያልፍ ባለጠግነት መመካት የለባቸውም፡፡ **፩ጢሞ. ፮÷፲፯**፡፡ **ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "ሃብትን** ሳይሆን ከሃብት ጀርባ ያለውን ትዕቢትና ወንጀል እንቃወማለን፡፡" በማለት አስተምሯል፡፡ የክርስቲያን ገንዘብ ከዓመፃ ከወንጀል የነጻ መሆን አለበት፡፡ ክርስቲያን በገንዘቡ አይታበይም፡፡ በገንዘባቸው የሚደገፉ በገንዘባቸው ይመካሉ፡፡ ክርስቲያን ግን በማያልፈው ገንዘብ በእግዚአብሔር ላይ ትምክህቱን ያደርጋል፡፡

***፫.፫. በገንዘብ አለመደገፍ፦*** ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን "አትርፎ በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር እንጂ በሚያልፍ ባለጠግነት ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው" በማለት ክርስቲያን ባለጠጎች በገንዘባቸው እንዳይደገፉ መክሯል፡፡ **፩ጢሞ. ፮÷፲፯**፡፡ **ገንዘብን ሳይሆን የማያልፈውን** ተስፋ እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግና በእርሱ መደገፍ መመካት አለብን፡፡ የዚህ ዓለም ገንዘብ ድንገት ይበተናል ኃላፊ፣ጠፊ ነው፡፡ በእግዚአብሔር የተደገፈ ግን ለዘላለም አይወድቅም፡፡ ገንዘብ ምንም ቢበዛ የነፍስ ቤዛ አይሆንም፡፡ ማቴ. ፲፮÷፳፮፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ክርስቲያን ባለጠጋ መሆን ይችላል፤ ጉስቁልናን የሚያበረታታና ድህነትን የሚደግፍ ትምህርት በክርስትና የለንም፡፡ ቅድስት ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርጋ የሥራን ክቡርነት በማበረታታት ታስተምራለች፤ ስንፍናን ታወግዛለች፡፡ ብዙ

የእግዚአብሔር ወዳጆች ባለጠጎች ነበሩ፡፡ ኢዮብ ባለጠጋ ነበር፤ ግን በገንዘቡ እግዚአብሔርን አከበረ፡፡ በገንዘባችን ድሆችን መርዳት፣ ቤተክርስቲያንን መደገፍ፣ ቃሉን ማስፋትና ለሀገርና ለሕዝብ የሚበጅ መልካም ሥራ መሥራት በክርስቲያናዊ ሕይወት ታላቅ ተግባር ነው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ፤ ወጣቶችን ስለ ገንዘብ አጠቃቀም ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የሥጋ ፍላጎቶችን ማወቅና ማሸነፍ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የመንፈስን ፈቃድ በሥጋቸው እንዲፈጽሙ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ፡፡" ገላ. ፭÷፲፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፪ቆሮ. ፯÷፩፣ ገላ. ፪÷፳፣ ኤፌ. ፪÷፫ እና ያዕ. ፪÷፪

## መግቢያ

ሥጋ ታቦተ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ፩ቆሮ. ፮÷፳፡ ሥጋ የሰው አካላዊ ባሕርይ (ፍጥረታዊ ማንነት) ነው፡፡ ሥጋ በራሱ ኃጢአተኛ (ክፉ) አይደለም፡፡ ሥጋ በውስጡ ልዩ ልዩ ፍላጎቶች አሉት፡፡ ሆኖም እነዚህን ፍላጎቶች ማወቅና ክፉ መሻታቸውን ማሸነፍ ይጠበቅብናል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በክርስቶስ ትምህርት ደካማ ሥጋ የሚበረታው በመንፈስ ኃይል እንደሆነ ተረድተናል፡፡ ማቴ. ፳፮÷፵፩፡፡ **የሥጋ ጉልበቱ የበረታ መንፈስ** ነው፡፡ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ የሚባለው ከመንፈስ ሲወለድና በመንፈስ ፈቃድ እየተመራ ሲጓዝ ነው፡፡ ዮሐ. ፫÷፯፣ ሮሜ. ፰÷፲፬፡፡

ሰው የሥጋና የነፍስ ውሕድ ሲሆን የነፍስ ማደሪያ ነው፡፡ የዓለም ክፋትና የውስጥ ክፉ መሻት ኃጢአት ሊያሠራው ይችላል እንጂ ሥጋ በተፈጥሮው ክፉ አይደለም፡፡ ስለዚህ የሥጋን የሚገባና የማይገባ ፍላጎት ማወቅ ይጠበቅብናል፡፡

**ተገቢ የሆኑ የሥጋ ፍላጎቶች፡-** መብላት፣ መጠጣት፣ ማረፍ፣ መተኛት፣ መልበስ፣ መማር፣ መሥራት በተገቢው መንገድ መበልጸግ፣ ትዳር መያዝ ናቸው፡፡ እነዚህን የሥጋ ጥያቄዎች ለይቶ ማወቅና በተገቢው መንገድ ተገቢ ምላሽ መስጠት አለብን፡፡

**ተገቢ ያልሆኑ የሥጋ ፍላጎቶች፡-** መስከር፣ መዳራት፣ መሳደብ፣ መጣላት፣ መግደል፣ ማመንዘር፣ ምቀኝነት፣ ስስት፣ በዘርና ቀለም ልዩነት ማድረግ (ወገንተኝነት)፣መናፈቅነት፣ ትዕቢት፣ አድመኝነት ወዘተ. . .ናቸው፡፡ እነዚህን ተገቢ ያልሆኑ ፍላጎቶች ማሸነፍ (ራስን በመግዛት መኖር) ይጠበቅብናል፡፡

www.zeorthodox.org

በቅዱስ ጳውሎስ አስተምህሮ የሥጋ ፍላጎቶችን ስለመግዛት እንደሚከተለው ተብራርቶአል፡፡

- "የዚህ የተስፋ ቃል ካለን በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም አድርገን ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንጻ" ፪ቆሮ. ፯÷፩፡፡

- “የሥጋን ምኞት ከቶ አትፈጽሙ፡፡ . . . የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው፡፡ እርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንዓት፣ ቁጣ፣ አድመኝነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘረኝነት ይህን የሚመስል ነው፡፡ እነዚህን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም፡፡” ገላ. ፭÷፲፱-፳፩፡፡
- “የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን . . . የቁጣ ልጆች ነበርን፡፡” ኤፌ. ፪÷፫፡፡ **ቅዱስ ጳውሎስ የሥጋ ፈቃድን** የረታ ታላቅ መንፈሳዊ ሰው ነበር፡፡ መልእክታቱም ይህን ይመሰክራሉ፡፡
- “ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ፡፡” **፩ቆሮ.** ፱÷፳፯፡፡
- “ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፡፡ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም፡፡ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፡፡ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወዳጀችና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው” ገላ. ፪÷፳፡፡

ቅዱስ ያዕቆብ “ሥጋውን ሊገታ የሚችል ፍጹም ነው፡፡” ይላል፡፡ ያዕ. ፫÷፫፡፡ **የሥጋ ፍላጎትን ማወቅ ብልህነት** ነው፡፡ የሥጋ ፍላጎትን ማሸነፍ ግን የፍጹምነት ምልክት ነው፡፡ በሥጋ ፍላጎቶቹ ላይ ባለሥልጣን የሆነ ቅዱስ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

የሥጋ ፍላጎቶችን ማወቅ ብልህነት ሲሆን ማሸነፍ ግን የፍጹም ሰው ባሕርይ ነው፡፡ የሰማይ አባታችን ፍጹም እንደሆነ ሁሉ በሥጋ ፍላጎቶቻችንን ላይ ባለሥልጣን በመሆን ፍጹማን እንሁን፡፡ ማቴ. ፭÷፵፰

## ተግባር

- መምህሩ በሥጋ ፍላጎቶቻቸው ላይ ባለሥልጣን የሆኑ አባቶችን በመጥቀስ ወጣቶች አርአያ እንዲያደርጓቸው ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ሕግን ማክበር

**የትምህርቱ ዓላማ:-** ወጣቶች የሥነ-ምግባር ሕግጋትን እንዲያከብሩ ማስገንዘብ።

**በቃል የሚጠና ጥቅስ:-** "በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ።" ሮሜ. ፪÷፲፫

**ተጨማሪ ምንባባት:-** ማቴ. ፳፫÷፳፫፣ ሮሜ. ፪÷፲፬-፲፭፣ ገላ. ፫÷፳፬ እና ዕብ. ፲÷፯

## መግቢያ

ሕግ አንድን ነገር ለመፈጸም የሚያግዝ ወይም ከማድረግ የሚከለክል መመሪያ (ሥርዓት) ነው። ሕግ ለእግዚአብሔር ክብርና ለሰው ጥቅም ያስፈልጋል። ሕግ ሰው ለአምላኩ ያለውን መታመን መግለጫ ሲሆን ሰውን ክፉ ከማድረግ ይከለክላል።

## የሳምንቱ ትምህርት:-

**፩. ሕግ በብሉይ ኪዳን:-** እግዚአብሔር የሕግጋት ምንጭ ነው። ለሰው ደኅንነትና ለክብሩ መገለጫ ሕግን ሰጥቷል። እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ላደረገው ቃል ኪዳን ሕግ ሠርቷል። ሕግ በቃል ኪዳን ውስጥ የሰውን ድርሻ ያመለክታል። ሕግ ለሙሴ ተሰጥቶአል፤ መጽሐፎቹም የሕግ መጻሕፍት ይባላሉ። ዮሐ. ፩÷፲፯።

የብሉይ ኪዳን ሕግ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል የሚኖረውን ግንኙት ያሳያል። ለእስራኤላውያን እግዚአብሔር የሰጠው ሕግ ከሁለንተናዊ ሕይወታቸው ጋር ይዛመዳል። በግብረ ገብ /በሞራላዊ/፣ ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ሕግጋት መካከል ልዩነት አልነበረም። ሁሉም ሕግጋት መታዘዝን ይፈልጋሉና። ሕግጋቱ በማኅበረሰቡ መካከል ፍትሕን በማስፈን አግዘዋል። የብሉይ ኪዳን ሕግ በፍትሕ፣ በፍቅር፣ በጽድቅና በቅድስና የተመሠረተ ነበር። ዘሌ. ፲፱÷፪-፲፱። **የብሉይ ኪዳን ሕግ በክርስቶስ** መምጣት ለተገለጠው የምሥራች መንገድ አዘጋጅቷል። ገላ. ፫÷፳፬።

**፪. ሕግ በሐዲስ ኪዳን:-** በሐዲስ ኪዳን ሰዎች በጸጋ ለሆነው ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን መታዘዛቸውን ለመግለጽ የሚፈጽሟቸው የሥነ-ምግባር ሕግጋት አሉ። እነዚህ ሕግጋት የእግዚአብሔር የፈቃዱ ምስጢራት የተገለጡባቸው በመሆናቸው እንፈጽማቸዋለን።

www.zeorthodox.org

ክርስቶስ በተራራው ስብከት የግብረ ገብ ሕግጋትን አጽንቷል። ማቴ. ፭÷፲፯-፯÷፲፪። **ለሙሴ የተሰጡትን ዐሥር ትእዛዛት** እግዚአብሔርን በመውደድና ባልንጀራን እንደራስ በመውደድ አጠቃሎ አስተምሯል። ሉቃ. ፲÷፳፯። ሕግ የተሰጠበት ዓላማ ክፋትን ለመግታት ነው። በአዲስ ኪዳን ዘመን የብሉይ ኪዳኑን ሕግ መሠረት ያደረጉ ሦስት ዓይነት ሕግጋት አሉ።

***፪.፩. ሕገ እግዚአብሔር (ፍትሕ መንፈሳዊ):-*** እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው የቃል ኪዳን ማረጋገጫ ሕግ ሕገ እግዚአብሔር

ይባላል፡፡ ይህ ሕግ የሥነ-ምግባርና የመንጻት ሕግ በመባል በሁለት ይከፈላል፡፡ የሥነ-ምግባር ሕግ በክርስቶስም ትምህርት ጸንቷል፡፡ የመንጻት ሕግ ግን ተሽሯል፡፡ በብሉይ ኪዳን በተገለጠው የመሥዋዕት ሥርዓት (የመንጻት ሕግ) ፈንታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ራሱን ለአባቱ አንድ ጊዜ ለዘላለም በማቅረቡ የመንጻት ሕግ ቀርቷል፡፡ ዕብ. ፺÷፲፫፡፡ **ይህ የመንጻት ሕግ ለክርስቶስ** የዘላለም ቤዛነት ጥላ ነበር፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነው፡፡ ይህ ሕግ ለእርሱ መንገድ ያዘጋጃል፤ ወደ እርሱም ያመለክታል፡፡ ከእርሷ መምጣት በፊት የእስራኤል ሕዝብ በሕግ ሥር በሞግዚት ቁጥጥር ሥር እንዳሉ ሕፃናት ነበሩ፡፡ በክርስቶስ መምጣት የመንጻት ሕግ ዓለማውን ስለፈጸመ ሞግዚት ኢያስፈልግም፡፡ ገላ. ፫÷፳፫-፳፮፣ **ሮሜ.** ፲÷፬፡፡

***፪.፪. ሕገ ሕሊና (የሞራል ሕግ)፦*** እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ክፉና ደጉን የሚለይበት ዳኛ በልቡ አስቀምጧል፡፡ ይህ ዳኛ ሕሊና ይባላል፡፡ በሰብአዊነት የምንፈጽማቸው ሕግጋት አሉ፡፡ ለጽሑፋዊው ሕግ የሞራል ሕግ መሠረት ነው፡፡

***፪.፫. ሕገ መንግሥት (ፍትሐ ሥጋዊ)፦*** የእግዚአብሔርን ሕግ መሠረት በማድረግ የተደነገገ የማኅበረሰብ የስምምነት ሰነድ ነው፡፡ አማኝ ለሰማያዊ ዜግነቱ የእግዚአብሔርን ሕግ፤ ለምድራዊ ዜግነቱ የመንግሥታትን ሕግ ማክበር አለበት፡፡ የመንግሥት ሕግ የሃገር ሉዓላዊነትንና የሕዝብን ደኅንነት የመጠበቅ ዓለማ አለው፡፡ የቤተሰብ መተዳደሪያ የወንጀለኛ መቅጫና የፍትሐ ብሔር ሕግጋት በሕገ መንግሥት (በፍትሕ ሥጋዊ) ይጠቃለላሉ፡፡

## ማጠቃለያ

ክርስቲያኖች በሕግ ሥር ሳይሆን ከጸጋ በታች ናቸው፤ ነገር ግን ሕግ የሌላቸው አይደሉም፡፡ ሮሜ. ፮÷፲፭፡፡ **የክርስቶስን የነጻነት ሕግ** በመፈጸም ይታዘዛሉ፡፡ ትእዛዙን መጠበቃቸው ለክርስቶስ ያላቸውን ፍቅር ይመሰክራል፡፡ ዮሐ. ፲፬÷፲፭፡፡

## ተግባር

- መምህሩ፤ ወጣቶች "የመንጻት ሕግ" በሚል ርእስ በሙሴ መጻሕፍት ላይ የተመሠረተ አጭር ጥናታዊ ጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# የእምነት ኃይል

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የእምነትን ኃይል እንዲያውቁና እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እምነት ቢኖራችሁ የሚሳናችሁ ነገር የለም፡፡" ማቴ. ፲፯÷፳

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፰÷፰-፲፩፣ ማር. ፲፩÷፳፬፣ ያዕ. ፩÷፲፮ እና ፩ዮሐ. ፭÷፲፭

## መግቢያ

እምነት የክርስትና ትልቅ ኃይል ሲሆን ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ የሕይወት መንገድ ነው፡፡ እምነት እግዚአብሔር የሚደሰትበት የመንፈስ ፍሬ ነው፡፡ እምነት ባሕርን እንደየብስ ጎዳና የሚረማመዱበት፤ ተራራን የሚያንቀሳቅስ፤ እሳትን የዕረፍት ሰገነት የሚያደርግ፤ የገዳዮችን መንጋጋዎች ቀልፎ ምቹ ትራስ የሚያደርግ ታላቅ ኃይል ነው፡፡ ለሚያምን ሁሉ ይቻላልና፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እምነት ማለት፤ እግዚአብሔር የሁሉ መገኛ፤ ሁሉ በእርሱ የሆነ፤ የሁሉ ፈጣሪ ሁሉን ሰጭ ታማኝ አምላክ፤ ዮሐ.፩÷፫፤ **መሆኑን** በፍጹም ልብ ተቀብሎ፤ በእግዚአብሔር ቃል መመራት፤ በሥራዎቹም መደገፍ ማለት ነው፡፡ **፪ጢሞ.፪÷፲፫** ፣ቲቶ. ፫÷፰ እምነት የእግዚአብሔርን ማዳንና በረከት የምንቀበልበት የሕይወት መንገድ ነው፡፡ የእምነት ምንጭ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ "ባልሰሙት እንዴት ያምናሉ?" እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት በእግዚአብሔር ማመን፣ መታመንና መደገፍ ይችላሉ፡፡ ሮሜ. ፲÷፲፬፡፡ **እምነት ለታመነው አምላካዊ** ቃል በተግባር የሚገለጥ የሰው ምላሽ ነው፡፡ ሰው የሚችለውን እየሠራ በማይችለው ጉዳይ "አምላኬ ሁሉን ያስችለኛል" ብሎ ሲተማመን አማኝ ይባላል፡፡ እምነት ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ የእግዚአብሔር ስጠታ ነው፡፡ ገላ.**፭÷፳፫፣ ኤፌ.፪÷፰፣ ፪ተሰ.፪÷፲፫** ሰው በእምነቱ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ስለሚተባበር የጌታችንን ትምህርትና አርአያነት ተከትሎ እምነቱ የሚገለጥበትን መልካም ሥራ ይሠራል ኤፌ.**፪÷፰-፲፣ያዕ.፪÷፲፰- ፳፮**፡፡

www.zeorthodox.org

እውነተኛ እምነት የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃላት ያዘለ ግንድ ነው፡፡ እውነተኛ እምነት የሰውን ሁለንተና ለእግዚአብሔር ክብር ያስገዛል፡፡ በዓለም ሞገድና ማዕበል አይናወጽም፡፡ እውነተኛ እምነት የሰውን አካሄድ በማስተዋል፣ በጥበብና በድል ይመራል፡፡ እውነተኛ እምነት በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ የፍቅር መሥዋዕት ነው፡፡

እምነት የመንፈስ ፍሬ ነው፡፡ ገላ. ፭÷፳፫፡፡ **እምነት ከሌለ ከእግዚአብሔር** ምንም ነገር መቀበል አይቻልም፡፡ ያለ እምነት እግዚአብሔርን ማስደሰት አይቻልም፡፡ "እምነት የምግባራት ሁሉ መሠረት ነው፡፡" በማለት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

እንዳስተማረው ያለ እምነት ሌሎች ምግባራት ዋጋ አያሰጡም፡፡ ዕብ. ፲፩÷፮፡፡

ታላቁ አውግስጢኖስ፤ “እምነት ሳያዩ ማመን ነው፤ ሽልማቱም ያመኑትን ማየት ነው፡፡” በማለት እምነትን ተርጉሞአል፡፡ የክርስቲያኖች እምነት በማይታየው እግዚአብሔር ላይ ይመሠረታል፡፡ ሽልማትም በዘመን መጨረሻ ንጉሣችንን በውበቱ ማየት ነው፡፡ ክርስቶስ “ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው፡፡” በማለት እንዳስተማረ፡፡ ዮሐ. ፳÷፳፱፡፡ **በማይታየው በእግዚአብሔር** ላይ የተመሠረተ እምነት ከሚታየው የዓለም መከራ ይሰውራል፤ የሚታየውንም በረከት ያቀዳጀናል፡፡ በማመናቸው እጅግ ብዙ በረከትን የተቀበሉ፣ ሞትን ረግጠው ያለፉ፣ ባሕርን የከፈሉ፣ ያለ መሣሪያ ያሸነፉ፣ ሳይታገሉ የጣሉ፣ ከተፈጥሮ ሕግ በላይ ተአምራትን የሠሩ፣ ታሪክ የለወጡና የማይቻለውን የቻሉ የእምነት አብነቶች አሉን፡፡

የመቶ አለቃው ክርስቶስን “ቃል ብቻ ተናገር ብላቴናዬም ይፈወሳል፡፡” ሲል ክርስቶስ ኢየሱስ “በእስራኤል እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም፤ እንዳመንህ ይሁንልህ፡፡” አለው፤ ሆነለትም፡፡ ማቴ. ፰÷፰-፲፫፡፡ **ሰው እንዳመነ** ይሆንለታል፡፡ ሳይጠራጠር የሚለምን ይቀበላል፡፡ ያዕ. ፩÷፮፣ **ማር.** ፲፩÷፳፬፡፡ **የሚጠራጠር ሰው** የተረጋጋ ሕይወት የለውም፡፡ ተጠራጣሪ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለምኖ መቀበል፣ ሠርቶ መባረክና ፈልጎ ማግኘት አይችልም፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ ምዕራፍ ፲፩÷፩-፵ ጥልቅ የሆነ የእምነት ትምህርት አስተምሯል፡፡ እምነት ተስፋ ለምናደርገው ነገር ማረጋገጫ፣ የማናየውን የምናይበት መንፈሳዊ ዓይን፣ ከሞት የምንሰወርበት ሕይወት፣ እግዚአብሔርን የምናስደስትበት መሥዋዕት፣ ነገን የምናይበት መስታወት፣ እግሮቻችንን በበረከት ምድር የሚያቆም ካርታ፣ ያጣናቸውን የምንቀበልበት ኃይልና መብዓ ያቀረብንበት እጅ እንደሆነ ይመሰክራል፡፡ ዕብ. ፲፩÷፯-፲፪፡፡ **የእምነት ኃይል** ከሞት እንደሚበረታ፣ ባሕርን ያለ መርከብ የሚያሻግር፣ በረሐን ያለስንቅ የሚያቋርጥ፣ የኢያሪኮን ቅጥር ያለ መዶሻና ደማሚት የሚጥል ኃይል እንደሆነ ይገልጻል፡፡ የእምነት ኃይል የነገሥታትን ትጥቅ ያስፈታል፤ የዲያብሎስን ቀስት ያስጥላል፤ የኃያላንን ጉልበት ያርዳል፤ የአናብስትን አፍ ይዘጋል፤ የሰይፍን ስለት ይሰብራል፤ ደካሞችን ያበረታል፡፡ ዕብ. ፲፩÷፴፫፡፡ **የእምነት ኃይል** ፀሐይን በገባዖን ያዘገያል፡፡ ኢያ. ፲÷፲፪፡፡ **የእምነት ኃይል** ተራራን ሜዳ ያደርጋል፡፡ ማቴ. ፲፯÷፳፡፡ **ለሚያምን ሁሉ ይቻላል**፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

የእምነት ኃይል ከሁሉ ይበልጣል፡፡ በሞት ላይ ባለሥልጣን ያደርጋል፡፡ ሁሉን ያስችላል፡፡ የእምነት ኃይል ባህርን እንደየብስ ረግጦ ሊረማመዱበት የሚያስችል ጎዳና፤ ተራራን የሚያንቀሳቅስ፤ እሳትን አቀዝቅዞ ለዕረፍት የሚመርጡት መናፈሻ የማድረግ ልዩ ኃይል ነው፡፡ የእምነት ኃይል ኃያላንን ትጥቅ ያስፈታል፡፡ የጻድቅ ሰው የኑሮ ጉልበት እምነት ነውና በእምነት እንመላለስ፡፡ **፩ሮሜ. ፲÷፯፤ ዕብ. ፲÷፴፰፡፡**

## ተግባር

- መምህሩ በዕብራውያን ፲፩ ላይ የተጠቀሱትን የእምነት ሰዎች ታሪክ ወጣቶች እንዲያጠኑና በእምነታቸው እንዲመስሏቸው ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ጊዮርጊስ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች በእምነትና በትዕግሥት የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንዲመስሉ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "መከራን መቀበል መረጠ፤ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቶአልና፡፡" ዕብ. ፲፩÷፳፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፲፮÷፳፬፣ ማቴ. ፲÷፴፪፣ ማር. ፲፮÷፲፰፣ ዮሐ. ፲፬÷፲፪ እና (ገድለ ቅዱስ ጊዮርጊስ)

## መግቢያ

ቅዱስ ጊዮርጊስ ከክርስቲያን ቤተሰብ የተወለደ ሰማዕት ነው፡፡ አባቱ ዞሮንቶስ እናቱ ቴዎብስትያ ይባላሉ፡፡ አባቱ የዲዮቅልጥያኖስ ሰው ነበር፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከአባቱ ሞት በኋላ የአባቱን ሹመት፣ የዓለምን ክብርና ደስታ ንቆ የክርስቶስ ምስክር ሆነ፡፡ በዲዮቅልጥያኖስ ትእዛዝ ብዙ መከራ ቢቀበልም እስከ ሞት ድረስ ጸንቶ ለክርስቶስ ታምኖአል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**፩. የቅዱስ ጊዮርጊስ ጽናት፡-**

ቅዱስ ጊዮርጊስ በእምነትና በትዕግሥት የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን አብነት በማድረግ የክርስቶስን ቃል በመፈጸም የክርስትናን ጉዞ ጀመረ፡፡ ብዙዎች ስለ እግዚአብሔር ከመመስከርና ክርስትናን ከማስተማር ዝም እንዲሉ መከሩት፡፡ ዲዮቅልጥያኖስም ለጣዖት እንዲሰግድ መከረው፤ ፈቃዱን ከፈጸመ አባቱ ከነበረው ሥልጣን እጅግ የበለጠ ሹመት እንደሚሰጠው ቃል ገባለት፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ግን ሰማያዊውን ክብር በማሰብ ምድራዊውን ሹመት ናቀ፤ በእምነቱም ጸና፡፡

ቅዱስ ጊዮርጊስ ወደ ሸንጎ ቀረበ፡፡ የመንኳንንቱ አሽከሮች አሰቃዩት፡፡ በመከራና በስቃይ ቢሆንም የአምላኩ ቅዱስ መንፈስ አበረታው፡፡ መርዝ አጠጡት፤ ቅዱስ ጊዮርጊስ ግን አልሞተም፡፡ "በእኔ የሚያምኑትን የሚገድልም ነገር ሁሉ ቢጠጡ አይጎዳቸውም" ያለው አምላካዊ ኪዳን ተፈጸመ፡፡ ማር. ፲፮÷፲፰፡፡ መርዙ እንዳልጎዳው ያወቁ ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ፡፡ ያመኑትን ንጉሡ አስገደላቸው፡፡

www.zeorthodox.org

የቅዱስ ጊዮርጊስ ጽናት ብዙዎቹን ማረከ፡፡ የአማኞች መጽናት አሕዛብን ከጨለማ ግዛት ወደ ብርሃን ዓለም ያፈልሳል፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ በሾለ ብረት በምስማር ጫማ ላይ በባዶ እግሩ እንዲሄድ፤ በጋለ ብረት ላይ ራቁቱን እንዲተኛ ተደረገ፡፡ በእምነቱ ጸና እንጂ ስቃይ ስለበዛበት አምላኩን አልካደም፡፡ በወፍጮ አጥንቱን ፈጭተው በደብረ ይድራስ በተኑት፡፡ አልአዛርን ከሞት ያስነሣውን ጌታ

ኢየሱስ ክርስቶስን አምኖአልና ከሞት አስነሣው፡፡ በመጨረሻም ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስም ጸንቶ መከራን እየተቀበለ ከሰባት ዓመት ተጋድሎ በኋላ ሚያዝያ ፳፫ በሰማዕትነት ዐረፈ፡፡

**፪. የቅዱስ ጊዮርጊስ ተአምር፡-**

ቅዱስ ጊዮርጊስ በመከራ ጊዜ በአንዲት መበለት ቤት በደረቅ ግንድ ላይ ታስሮ ሳለ የታሰረበት ግንድ ለመለመ፡፡ በዚህ ሰዓት ሴቲቱ "የክርስቲያኖች አምላክ ወደ ቤቴ ገብቶአል" ብላ ስትጮህ ቅዱስ ጊዮርጊስ "እኔ የክርስቲያኖች አምላክ አይደለሁም፤ የክርስቲያኖች አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እኔ የእርሱ አገልጋይ ነኝ፡፡" በማለት መከራት፡፡ በተጨማሪም በቤሩት ሃገር ቡርክታዊትን ከሞት በማዳንና እንደ አምላክ የተፈራውን ዘንዶ በመግደል የክርስቶስን አምላክነት ሰብኳል፡፡

**፫. ከቅዱስ ጊዮርጊስ ሕይወት ምን እንማራለን?**

***፫.፩. የዓለምን ክብር መናቅን፡-*** ቅዱስ ጊዮርጊስ የዓለምን ክብር፣ ሹመት፣ ሽልማት፣ ውበት፣ ሃብት፣ ደስታ የናቀ ሰማዕት (ምስክር) ነው፡፡ በኃጢአት ከሚገኙ ጊዜያዊ ደስታና ክብር ይልቅ የክርስቶስን ብድራት መርጧል፡፡ በምድር ያለውን ከሰማይ አንጻር ተመልክተን በኅሊና ሚዛን ስንመዝነው የምድሩ በጣም ቀላል ይሆንብናል፡፡ የማያልፈውን ማሰብ፣ ለመጪው ሕይወት መዘጋጀትና ለዘላለማዊ ክብር መሥራት ይጠበቅብናል፡፡ ለዘለዓለም ለማንኖርበት ጊዜያዊ ዓለም ስንደክም የምንኖርበትን ዘለዓለማዊና ሰማያዊውን ርስታችንን እንዳናጣ፡፡

ሙሴ የዓለምን ክብር በመናቁ ለዘላለም ከበረ፡፡ በታቦር ተራራ ክብሩን ለማየት ታደመ፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስም የምድርን ሹመትና ሽልማት ንቆ ለክርስቶስ ክብር ቆሞ በጽናት መከራን በመቀበሉ ዘመን ተሻጋሪ ባለታሪክና የጽናት አርአያ ሆነ፡፡ በማይኖርበት ዘመን ሁሉ ስለ እርሱ የሚነገረው በኖረበት ዘመን ለእግዚአብሔር ዓለማ በፍጹም እምነት በጽናት ቆሞ ስለኖረ ነው፡፡

***፫.፪. ጽናትን፡-*** ቅዱስ ጊዮርጊስ ዘግናኝ መከራዎችን በጽናት ያለፈ ቆራጥ ሰማዕት ነው፡፡ የጽናቱ ፍሬ ብዙዎችን ወደ እግዚአብሔር ፍቅርና ዘለዓለማዊ መንግሥቱ አፍልሷል፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ የጸናውን ክርስቶስን በማሰብ የጸና ምስክር ነው፡፡ ስለ ስሙ ስንሠራ ነቀፌታ ሊያጋጥመን፣ ስለ ፍቅሩ ስንኖር ዲያብሎስ ሊፈትነንና ስለ ጽድቅ ስንቆም ሥጋዊ ፍላጎት ሊያደክመን ይችላል፡፡ የከበቡንን ቅዱሳን ምስክሮቻችንን አብነት በማድረግና የሚያጸናውን ክርስቶስን በማሰብ በፊታችን ስላለው ደስታ እስከመጨረሻው እንጽና፡፡

## ማጠቃለያ

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ጊዮርጊስ መከራና ሞት ያልበገረው የክርስቶስ ምስክር ነው፡፡ በጽናቱ፣ በእምነቱ፣ በትዕግሥቱና በፍቅሩ አብነታችን ነው፡፡ በረከቱ አይለየን፡፡

## ተግባር

- መምህሩ እንደቅዱስ ጊዮርጊስ ወጣትነታቸውን ለእግዚአብሔር እንዲሠዉ ወጣቶችን ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ሱሰኝነት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ወደ ሱስ የሚወስዱ መንገዶችን በመዝጋት በንጽሕና እንዲመላለሱ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ማንም ራሱን አያታልል፡፡" ፩ቆሮ. ፫÷፲፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ቆሮ. ፫÷፲፮ እና ኤፌ. ፭÷፲፭-፲፱

## መግቢያ

ሱሰኝነት ከገባንባት ለመውጣት የሚያደክም፤ ሥጋን የሚጎዳ ነፍስንም የሚያቆስል ክፉ ልምድ ነው፡፡ ሱሰኝነት የሰውን አእምሮ አስሮ ሰው በራሱ ፈቃድና በአእምሮው እንዳይሠራ የሚያደርግ የኃጢአት መሣሪያ ነው፡፡ ሱሰኝነት ለብዙ ኃጢአቶች፣ በሽታዎችና የገንዘብ ብክነቶች የሚያጋልጥ የኃጢአት ቀንበር ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አልኮል መጠጥ፣ ሲጋራ፣ አደንዛዥ ዕፅ፣ ጫትና የዝሙት ፊልሞች ወዘተ ሰውን አስረው የያዙ ጎጂ ሱሶች ናቸው፡፡ ሰዎች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እነዚህን የኃጢአት ማሠሪያዎች ይለማመዳሉ፡፡

***፩. ወደ ሱስ የሚያመሩ መንገዶች፡-***

- የስሜት ባዶነት
- ጭንቀት
- የትምህርት (የግንዛቤ) እጥረት
- የጊዜ ማሳለፊያ ቦታዎችንና ሁኔታዎችን በትክክል አለመምረጥ
- የጓደኞች ክፉ ተፅዕኖ
- የደስታን ትክክለኛ ምንጭ ለይቶ አለማወቅ፤
- የመንፈሳዊ ሕይወት ዝለት

www.zeorthodox.org

***፪. ሱሰኝነት የሚያስከትለው ጉዳት፡-***

*ሀ. በሥጋዊ ሕይወት*

- ጤናን ይጎዳል (ለተለያዩ በሽታዎች ያጋልጣል፤ ለምሳሌ፡- ካንሰር፣ ሳንባ፣ ጨጓራና ግፊት ይጠቀሳሉ፡፡)፡፡

- ገንዘብን ያባክናል፡፡
- ከማኅበረሰቡ ጋር ያለንን መልካም ግንኙነት ያበላሻል፡፡
- ጊዜን ያባክናል፡፡
- ዕድሜን ያሳጥራል፡፡
- ክብርን ይነካል፡፡

ለ. በመንፈሳዊ ሕይወት

- የቅድስና ሕይወትን ገንዘብ እንዳናደርግ ያደርጋል፡፡
- ቅዱሱን ሰውነታችንን ያረክሳል፡፡ 1**ቆሮ.** 3÷06፡፡
- ለትልልቅ ኃጢአቶች ያጋልጣል፡፡ ለምሳሌ፡- ለዝሙትና ለግድያ
- መንፈሳዊ ሥራዎች የምንሠራበትን ጊዜ ያባክናል፡፡
- ሱሶች የሰይጣን ዓላማ ማስፈጸሚያዎች በመሆናቸው ከእግዚአብሔር የጸጋ በረከት ያሳጣሉ፡፡

**፫. ከሱሰኝነት እንዴት መላቀቅ እንችላለን?**

- የሱስን ጉዳት በማወቅና ጨክነን በመወሰን
- የእግዚአብሔርን ቃል በመማርና በመተግበር
- ራሳችንን በመግዛትና የጽድቅን መንገድ በመጀመር
- ለሱስ ከሚጋብዙን ሥፍራዎች፣ ሁኔታዎችና ሰዎች በመራቅ
- የምንባብና የጸሎት ሕይወትን በመለማመድ

## ማጠቃለያ

ሰው በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረ፤ ነጻ አእምሮ ያለው ክቡር ፍጡር በመሆኑ ማንኛውም ነገር ሊገዛው (ሊሠለጥንበት) አይገባም፡፡ ሰው የእግዚአብሔር ሕያው መቅደስ በመሆኑ የሚያረክስ ነገር በሰውነቱ አይፈጽምም፡፡ ተገዥነቱም ለሱስ ሳይሆን ዓለምን ፈጥሮ ለሚገዛው ሕያው አምላክ ለእግዚአብሔር ነው፡፡

## ተግባር

www.zeorthodox.org

- መምህሩ ወጣቶች በሱስ ምክንያት የሚመጡ የጤና ችግሮችን አጥንተው ለጓኞቻቸው እንዲያካፍሉ ያድርግ፡፡

# ወጣቶችና ፈተናዎቻቸው

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ፈተናቸውን በድል እንዲወጡ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከማይቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሐር የታመነ ነው፡፡" **፩ቆሮ.** ፲÷፲፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፳፯÷፲፣ ሉቃ. ፰÷፲፫፣ ፩ጢሞ. ፯÷፱፣ ፪ጴጥ. ፪÷፱ እና ያዕ. ፩÷፪

## መግቢያ

- የወጣቶች ፈተና ምንድን ነው?
- የወጣትነት ፈተናዎችን እንዴት ማሸነፍ ይቻላል?
- ፈተናዎቻቸውን በድል የተወጡ የወጣቶች አብነት እነማን ናቸው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የወጣትነት ሕይወት በእሾህ የተከበበች ጽጌሬዳ አበባን ይመስላል፡፡ ወጣትነት የችኩልነት፣ የኃይል፣ የዕውቀት፣ የውበትና የሃብት ሰገነት በመሆኑ ፈተናዎች ይበዙበታል፡፡ ሰይጣን በዚህ ዘመን ወጣቶች ያላቸውን ለማስጣል ይተጋል፤ ለኀሊና ፀፀት የሚዳርጉ ኃጢአቶችን እንዲሠሩ ሁኔታዎች ያመቻቻል፤ በውበታቸው፣ በሃብታቸው በኃይላቸውና በዕውቀታቸው ተጠቅሞ የክፉዎችን መንገድ እያቀና የምድርን ሸክም ያበዛል፡፡

ሰው በሕይወቱ እየተፈራረቀ የሚያጋጥመውን ፈተና አቻችሎ ስለሚኖር የመከራና የደስታ አምባ ነው፡፡ የወጣቶች ፈተና ግን በአብዛኛው ከዕድሜ ጋር የተያያዙና ከራሳቸው የሚመነጩ ፈተናዎች ናቸው፡፡ በወጣትነታቸው እግዚአብሔርን የሚያስቡ ከሚያጋጥማቸው ፈተና መውጫ በር ይዘጋጅላቸዋል፡፡ **፩ቆሮ.**፲÷፲፫-፲፬፡፡ **የወጣቶች ፈተና ከዓለም፣ ከሰይጣንና** ከውስጣዊ ባሕርያቸው ይመነጫል፡፡

### ወጣቶች በምን ይፈተናሉ?

www.zeorthodox.org

ወጣቶች በዝሙት፣ በትዕቢት፣ በፀብ፣ በክርክር፣ በዓለም ፍቅር፣ በስንፍና፣ በክህደትና በአድመኛነት ይፈተናሉ፡፡

**፩. በዝሙት፡-** የዝሙት መንፈስ በወጣትነት ይሰፍናል፡፡ ዮሴፍ ግን በዝሙት ተፈትኖ በድል ተወጣው፡፡ ለረዳው ለእግዚአብሔር ታምኖ "በሚያየኝ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አልሠራም" በማለት ዝሙትን ሸሸ፡፡ ዝሙትን ታግላን ሳይሆን ሸሽተን እናሸንፈዋለን፡፡ **፪ጢሞ** ፪÷፳፪፡፡ **ዝሙት መንፈስን የሚያረክስና** ሰውነትን የሚያቆሽሽ ነፍስንም የሚወጋ ትልቅ ኃጢአት ነው፡፡ ወጣቶች ዝሙትን ካሸነፉ ብፅዕናን ያገኛሉ፡፡

**፪. በትዕቢት፡-** ትዕቢት የጸጋ እንቅፋት ነው፡፡ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ያዋርዳል፡፡ ያዕ. ፬÷፮፡፡ **ወጣቶች በትዕቢት መንፈስ ይወድቃሉ**፡፡ ሌላውን ማዳመጥ አይፈልጉም፤ ሌሎችን ይንቃሉ፤ የበላይነት ስሜት ይሰማቸዋል፡፡ እግዚአብሔር በጸጋ ከፍ እንዲያደርገን በትሕትና መኖር አለብን፡፡

**፫. በፅብና በጥላቻ፡-** የወጣትነት ኃይላቸውን ተጠቅሞ ዲየብሎስ የማይወጡት ወንጀል ውስጥ የሚከታቸው ወጣቶች ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ፅብና ጥላቻ ለግድያ ወንጀል ይጋብዛል፡፡ ዮሴፍ ወንድሞቹ ሸጠውት እንኳ በይቅርታ መንፈስ ተቀበላቸው እንጂ በጥላቻ መንፈስ አልተበቀላቸውም፡፡ የበቀል፣ የጥላቻና የፅብ መንፈስን ልንቃወም በፍቅር፣ በይቅርታና በትዕግሥት ልንኖር ይገባል፡፡

**፬. በክህደት፡-** ወጣቶች ተረጋግቶ ማሰብ ባለመቻላቸው ምክንያት ሃይማኖታቸውን በስሜት ተነድተው እስከመካድ ይደርሳሉ፡፡ ዳንኤል፣ አናንያ፣ አዛርያና ሚሳኤል አምላካቸውን እንዲክዱ የሚያዝዝ አዋጅ ወጥቶ የሚደርስባቸውን ከባድ ቅጣት በመፍራት እግዚአብሔርን አልካዱም፡፡ በጽናት የማያምኑትን ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ያመጡ የእምነት አርበኞች ናቸው፡፡ በእምነት ጸንቶ መቆምን እንደ እነርሱ ገንዘበ እናድርግ፡፡

**፭. በዓለም ፍቅር፡-** የብዙ ወጣቶችን ልብ ፍቅረ ዓለም ሸርሽሮታል፡፡ የሚታየውን የዓለም መልክ ተስፋ በማድረግ እየተታለሉ ከዘላለማዊው በረከት የራቁ ብዙዎች ናቸው፡፡ እንደ ሙሴ የማይታየውን ብድራት አስተውለን በመጽናት በእግዚአብሔር ፍቅር ተደግፈን የወጣትነት ኀዳናችንን በቅድስና ሕይወት በመጠበቅ ልናነጻ ይገባል፡፡

## ማጠቃለያ

ወጣትነት በጊዜያዊው ዓለም በሚያልፍ ፈተናዎች የተከበበ ሕይወት ስለሆነ፤ የማያልፈውን ዘለዓለማዊ ክብር ለማግኘትና ከሕሊና ፀፀት ለመዳን በማስተዋልና በጥንቃቄ መጓዝ ይጠበቅብናል፤ የእግዚአብሔር ሰው በጽድቅና እግዚአብሔርን በመምሰል መኖር ይገባዋልና፡፡ ፩ጢሞ. ፮÷፲፩፡፡

## ተግባር

- መምህሩ "የወጣትነት ፈተናዎችን በድል ለመወጣት ምን ማድረግ አለብን?" በሚል ርእስ ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ወጣትነትን መገንዘብ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የወጣትነትን ዕድሜ በመገንዘብ በጥበብ እንዲያልፉት መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጕብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፡፡" መክ. ፲፪÷፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዳን. ፫፣፮

## መግቢያ

ወጣትነት እግዚአብሔርን የምናስብበት ዕድሜ፣ ለሽምግልና ዘመን ለጭንቅ ወራት ድጋፍ የሚሆነንን የጽድቅ ዛፍ አስቀድመን የምንተክልበት ዘመን ነው፡፡ ወጣትነት በማስተዋል የሚደገፍ በጥንቃቄ የሚመራ ሕይወት ነው፡፡ በክፉም በደግም የምንፈተንበት፣ በመከራ እንደወርቅ ነጥረን በመውጣት ማንነታችን የሚገለጥበት የሕይወት ዘመን ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሰው የልጅነት፣ የወጣትነትና የሽምግልና ወራቶች ተሰጥተውታል፡፡ በሦስቱም ዘመናት በሕይወቱ የተለያዩ ስሜቶች፣ አመለካከቶችና ጠባዮች ይንፀባረቁበታል፡፡ ወጣትነት የመካከለኝነት ዘመን ነው፡፡ አለመረጋጋት፣ ስሜታዊነት፣ ችኩልነት፣ ስግብግብነትና ትምክህተኝነት በወጣትነት ዘመን ይበረታል፡፡ የወጣትነት ዘመን የተለየ መልክ አለው፡፡ በዚህ ዘመን ስንሆን የበላይነት ወይም የበታችነት ስሜት ይፈታተነናል፤ ኃይላችንን አለአግባብ መጠቀምና በተቃራኒ ጾታ መታለል እንጀምራለን፡፡ ከራሳችን በቀር ሌሎችን ማድመጥ አንፈልግም፡፡ ትዕግሥት ያጥረናል፡፡ ለውሳኔ እንቸኩላለን፡፡ ሁሉን መያዝ እንፈልጋን፡፡ የነገሮችን ላይ ላዩን እንጂ ውስጥን መመርመር አንችልም፡፡ ቶሎ መከፋትና ቶሎ መደሰት ይንፀባረቅብናል፡፡ በአጠቃላይ የወጣትነት ዘመን አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ ለውጦች ይታዩበታል፡፡

ወጣትነትን መገንዘብ አስተዋይነት ነው፡፡ የወጣትነትን ጠባያት ካልተገነዘብን ለብዙ ፈተናዎችና መከራዎች እንጋለጣለን፡፡ በወጣትነታቸው የሚታዩባቸውን ጠባያትና የሚያጋጥሟቸውን ፈተናዎች ተገንዝበው በማስተዋል በጥንቃቄ ያልተመሩ ወጣቶች ሕሊናቸውን የሚያቆስል የፀፀት ታሪክ ይፈጽማሉ፡፡ ወጣትነት ተገቢ የሆነ ርዳታና ምክር የሚፈልግ ማንነት ነው፡፡ በወጣትነት ዕድሜ የሚመጡ አካላዊ ለውጦች ተፈጥሮአዊ ናቸው፡፡ አንዳንድ ወጣቶች ድምፃቸው ሲጎረንን ወይም ሲቀጥን፣ ሴቶች የሴት ልጅ ልማድ ምልክት ሲያዩና ወንዶች የተለየ ለውጥ በአካላቸው ሲያዩ ይደነግጣሉ፤ ይረበሻሉ፡፡ የሥነ-ልቦና ለውጦች ወጣትነታችንን ተደግፎ ይመጣል፤ ይህ ለውጥ በአግባቡ ካልገዛነው ለኃጢአት ያጋልጣል፡፡ በየትኛውም ዕድሜ ያለ ክፉ ጠባይ ተፈጥሮአዊ አይደለም፡፡ በመንፈስ ኃይል ሊሸነፍ የሚችል ጊዜያዊ ችግር ነው፡፡

ስለዚህ ጊዜያዊው ችግር ዘላቂ ሆኖ የከፋ ውድቀት እንዳያስከትልብን በወቅቱ በመረዳትና አስተውለን በመጓዝ በጥበብ

www.zeorthodox.org

ልናልፈው ይገባል፡፡ የወጣትነት ጊዜ ትዕግሥትንና አስተዋይነትን ይጠይቃል፡፡ በመረጋጋት መወሰን፣ በማስተዋል መጓዝ፣ በጥበብ መመላለስና በመንፈስ ኃይል መመራት ይጠበቅብናል፡፡

በወጣትነት ዘመን የሥጋ ባሕርይ ያይላል፡፡ የሥጋን ምኞት ላለመፈጸም ለመንፈስ ፈቃድ መገዛት አለብን፡፡ ወደፊት የጭንቅ ወራት ይመጣል፡፡ ዛሬ በጉብዝናችን ወራት ፈጣሪያችንን ብናስብ በኋላ በመከራችን የሚያስብልን ወዳጅ አፈራን ማለት ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ወጣትነት እንደ አቤል በደግነት በመጓዝ፤ እንደ ዮሴፍ በልበ ሰፊነት በመኖር፣ እንደ ኢያሱ በአገልግሎት በመበርታት፤ እንደ ጌዴዎን ለወገን ጥቅም በመቆምና እግዚአብሔርን በማምለክ፤ እንደ ዳንኤል በጸሎትና በታማኝነት በመጽናት፤ እንደ ሦስቱ ወጣቶች በጽናት፤ እንደ ዮሐንስ ወንጌላዊ እግዚአብሔርን በመውደድ፣ እንደ ጊዮርጊስ በሰማዕትነት በመጽናት መሆን አለበት፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ‹‹የወጣትነትን አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ ለውጦች እንዴት መገንዘብ እንችላለን?›› በሚል ርእስ ወጣቶችን ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ሴቶች በሐዲስ ኪዳን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በሐዲስ ኪዳን ያለውን የሴቶች አስተዋጽዖ ወጣቶች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ከእኛ ውስጥ ማልደው ከመቃብሩ ዘንድ የነበሩት ሴቶች አስገረሙን ሥጋውንም ባጡ ጊዜ፡- ሕያው ነው የሚል የመላእክት ራእይ አየን ሲሉ መጥተው ነበር፡፡ ከእኛም ጋር ከነበሩት ወደ መቃብር ሄደው ሴቶች እንደተናገሩት ሆኖ አገኙት፡፡" ሉቃስ ፳፬÷፳፪-፳፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሐዋ. ፲፰÷፳፮ እና ሮሜ. ፲፮÷፩፤፲፪-፲፬

## መግቢያ

ሴቶች በፊተኛይቱ ኪዳን ባለ ጸጋ እንደነበሩ ሁሉ በሐዲስ ኪዳንም ለበለጠው የክብር አገልግሎት ታጭተዋል፡፡ ሴቶች ከክርስቶስ ፅንሰት እስከ ዕርገት በደቀ መዛሙርቱም አገልግሎት በቤተ ክርስቲያንም ጉዞ በድርሻቸው አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ የክርስቶስን ፅንሰትና ትንሣኤ ቀድመው ያወቁት ሴቶች ናቸው፡፡ ኤልሳቤጥ የጌታችን ፅንሰቱን በማኅፀኗ በነበረው ሕፃን ደስታ ተረድታ አመሰገነች፡፡ ማርያም መግደላዊት ትንሣኤውን ከመላእክት ራእይ ተረድታ ለምሥራች ነጋሪዎቹ ምሥራች ነገረች፡፡ የብሉይ ኪዳኗ ነቢይት ዲቦራ መስፍኑን (ባርቅን) እንዳገዘች ሁሉ የሐዲስ ኪዳንም ሴቶች ደቀ መዛሙርቱን በነገር ሁሉ አግዘዋል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በ ዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ሴቶች ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደረጉ የክርስትና ባለውለታዎች ናቸው፡፡ የክርስትና መጠለያ የነበረችው የማርቆስ እናት የማርያም ቤት ናትና፡፡ ሐዋ. ፩÷፲፬፡፡ **ሴቶች በክርስቶስ አገልግሎት** ሕይወታቸውን የለወጡ፣ በስቅለቱ ከመስቀሉ ሥር፤ በመከራውም ሌሊት በመቃብሩ አጠገብ የነበሩ፣ የመላእክትን ራእይ ያዩ፣ ትንሣኤውን የሰበኩና በድሉ ማግሥት በክብሩ ዙሪያ የታዩ በጽናት የቆሙ ቅዱሳን ናቸው፡፡ ማቴ. ፳፰÷፩-፲፭፡፡

ከሰው ወገን ትንሣኤውን ቀድማ ያየችና የትንሣኤው የዓይን ምስክር የነበረች ማርያም መግደላዊት ናት፡፡ ዮሐ. ፳÷፩-፲፯፡፡ **ሴቶች በሐዲስ ኪዳን የሰባኪዎች** ሰባኪ ናቸው፡፡ ማርያም ትንሣኤውን ለሐዋርያት፣ አቂላ እና ጵርስቅላ ማዳኑን ለአጵሎስ ሰብከዋልና፡፡ ሐዋ. ፲፰÷፳፬-፳፯፡፡

www.zeorthodox.org

**፩. ሴቶች በክርስቶስ አገልግሎት፡-** ከክርስቶስ መቶ ሃያ ቤተሰብ ሠላሳ ስድስቱ ሴቶች ቅዱሳን ነበሩ፡፡ ሴቶች በክርስቶስ አገልግሎት በሚገባ ተጠቅመዋል፡፡ በእምነታቸውም የተመሰከረላቸው ታላላቅ ሴቶችም አሉ፡፡

- ደም ይፈሳት የነበረችው ሴት ማር. ፭÷፳፰-፴፬፡፡
- ከነናዊቷ ሴት፤ ማቴ. ፲፭÷፳፪-፳፰፡፡

ክርስቶስን ቆመው ያገለገሉ ሴቶች፡-

- የጴጥሮስ አማት፤ ማቴ. ፰÷፲፬-፲፯
- ማርታ፤ ሉቃ. ፲÷፴፰-፵፪

በክርስቶስ የተመሰገኑ ሴቶች፡-

- ማርያም ቃሉን በመስማቷ፤ ሉቃ. ፲÷፴፰-፵፪
- መበለቷ በደስታ በመስጠቷ፤ ማር. ፲፪÷፵፩-፵፬

ለክርስቶስ ምስክር የሆኑ ሴቶች፡-

- ነቢይት ሐና፤ ሉቃ. ፪÷፴፰
- ሳምራዊቷ፤ ዮሐ. ፬÷፳፱-፵፪
- ማርያም መግደላዊት፤ ዮሐ. ፳÷፲፯

**፪. ሴቶች በሐዋርያት አገልግሎት**፡- ከሐዋርያት ጀርባ ጠንካራ የሆኑ ሴቶች ነበሩ፡፡፡ የክርስትና ሕያው እውነት አድማሳትን እንዲያካልል ሴቶች በነገር ሁሉ ዋጋ ከፍለዋል፡፡ በቅዱስ ጳውሎስና በሐዋርያት አገልግሎት የተመሰከረላቸው ሴቶች፡-

- ፌበን ፤ ሮሜ. ፲፮÷፩
- የሩፎን እናት፤ ሮሜ. ፲፮÷፲፬
- ጦርሲዳ፤ ሮሜ. ፲፮÷፲፪
- አቂላና ጵርስቅላ፤ ሐዋ. ፲፰÷፳፮
- ሮዴ፤ ሐዋ. ፲፪÷፲፫

ቅዱስ ዮሐንስ በቀጥታ ለእመቤቲቱ መልእክት ጽፏል፡፡ ይህች ሴት እውነትን ያወቁ ሁሉ የሚወዷት የተመረጠች እመቤት ነበረች፡፡ **፩ዮሐ. ፪**፡፡

**፫. ሴቶች በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን**፡- በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በዕድሜ ትልቅ የሆኑ ሴቶች ሲጠመቁ ቀሳውስትን ሴቶች ያግዙ ነበር፡፡ ይህ የአገልግሎት ድርሻ የሚሰጣቸው ሴቶች ስልሣ ዓመት የሞላቸው ነበሩ፡፡ በዚህ አገልግሎት የምትኖር ሴት ዲያቆናዊት ትባል ነበር፡፡ **፩ጢሞ.** ፫÷፲፩፡፡ **ሴቶች በሐዋርያት የተጻፉ ክርስቲያናዊ** መልእክታትን ወደ አማኞች ጉባኤ ያደርሱ ነበር፡፡ የሮሜ መልእክት በፌበን እጅ እንደተላከ ይታመናል፡፡ ሮሜ. ፲፮÷፪፡፡

በጥንቷ ቤተክርስቲያን ወንዶች ሰማዕታት እንዳሉ ሁሉ ሴቶች ሰማዕታትም ነበሩ፡፡ በክርስትና ሕይወት ጻድቃን ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ ጻድቃን እናቶችም ነበሩ፡፡

በአሁኑ ዘመን ሴቶች በሰንበት ትምህርት ቤትና በሰበካ ጉብኤ አገልግሎቶች ይሳተፋሉ፡፡ በአምልኮ፣ በምስጋናና በጸሎት ሴቶች አይለዩም፡፡ የቅኔ መምህራንና መጻሕፍትን የጻፉ ሴቶች አሉ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ሴቶች በሁለቱም ኪዳናት የጎላ ሚና አላቸው፡፡ በሐዲስ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን ሕይወታቸውን እስከመሠዋት ደርሰው ክርስትናን ያስፋፉ ሴቶች አሉ፡፡ በሐዲስ ኪዳን ሴቶች የሰባኪዎች ሰባኪ ናቸው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶችን "ምን ተማራችሁ?" በማለት ስለ ሴቶች እኩልነት በሚነሡ ጥያቄዎች ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ሴቶች በብሉይ ኪዳን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በብሉይ ኪዳን የነበረውን የሴቶች ሚና ወጣቶች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ማርያም እየዘመረች በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር ዘምሩ አለች፡፡" ዘጸ. ፲፭÷፳

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** አስቴር ፪÷፲፯ እና መሳ. ፬÷፬

## መግቢያ

ሴቶች በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ በሰው ፊት ተደማጭነት አላቸው፡፡ ሴቶች በእግዚአብሔር መንግሥትና በማኅበራዊ ሕይወት የሥራ ድርሻ አላቸው፡፡ የኃያላን የጀርባ አጥንት ናቸው፤ ከእያንዳንዱ ኃያል ስኬታማ ወንድ ጀርባ ብልህ ሴቶች አሉና፡፡ ሴቶች በብልሃት፣ ሓላፊነትን በመወጣት፣ በቆራጥነት፣ በእምነትና በማኅበራዊ ሕይወት ስኬታማ ናቸው፡፡ በሁለቱም ኪዳናት ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በብሉይ ኪዳን የሚናገር ታሪክ፣ የሚወሳ ድልና የሚያስተምር ሕይወት ያላቸው በርካታ ሴቶች አሉ፡፡ የሴቶች እኩልነት በሁለቱም ኪዳናት ተገልጿል፡፡ ከአፈጣጠራቸው ጀምሮ የሴቶች የእኩልነት ሥዕል ተንጸባርቋል፡፡ ከጎኑ መፈጠሯና "ግዟቸው" የሚለው የጋራ ጸጋ የእኩልነት ነፀብራቅ ነው፡፡ ዘፍ. ፩÷፳፰፡፡ **የገዥነት ጸጋ ለወንዱ ብቻ** የተሰጠ አይደለም፡፡ በብሉይ ኪዳን በሁሉም ነገር የሴቶችን ሚና እናያለን፡፡

### የሴቶች ሚና በብሉይ ኪዳን፡-

***፩. በምስጋና፡-*** በብሉይ ኪዳን የምስጋና ሕይወት ሴቶች መዘምራን ነበሩ፡፡ ዕዝራ ፪÷፷፭፡፡ ማርያም እኅተ ሙሴ ከበሮ አንሥታ ሕዝቡን ለምስጋና አነቃቅታ "በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር ዘምሩ" ያለች ታላቅ ዘማሪ ናት፡፡ ዘጸ. ፲፭÷፳-፳፩፡፡ **ይህ የዝማሬ ጸጋ ሴቶችንም እንደሚመለከት ያሳያል፡፡ ምስጋናቸውንም በአደባባይ** ያቀርቡ ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

***፪. በትንቢት፡-*** የትንቢት ጸጋ ለወንዶች ብቻ አልተሰጠም፡፡ በሁለቱም ኪዳናት በነቢይነት የሚታወቁ ሴቶች አሉ፡፡ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ጾታ አይለይም፡፡ በነቢይነት ጸጋ የሚታወሱ፡-

ነቢይት ዲቦራ መሳ. ፬÷፬
ነቢይት ሕልዳና ፪ነገ. ፳፪÷፲፬
ነቢይት ሐና ሉቃስ ፪÷፴፮-፴፰

የፊልጶስ ልጆች ሐዋ. ፳፩÷፱

እነዚህን በነቢይነት ጸጋ እግዚአብሔር ያስነሣቸውን ሴቶች በጊዜው የነበረው ማኅበረሰብ በደስታ ሰምቷቸዋል፡፡ ወንዶች ለጦርነት ሲወጡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከእነዚህ ሴቶች ነቢያት ጠይቀው ነበር፡፡ መሳ. ፬÷፬-፲፡፡

***፫. በጦርነት፡-*** በእስራኤላውያን የጦርነት ታሪክ የድል ባለቤት እግዚአብሔር ነው፡፡ የእርሱ ኃይል ደግሞ በሁለቱም ጾታዎች ሰርቷል፡፡ ዮዲት የምትባል እስራኤላዊት ሴት ሆሎፎርኒስ የሚባለውን የእስራኤል ጠላቶች የጦር መሪ ገድላለች፡፡ (መጽሐፈ ዮዲትን ይመልከቱ)

***፬. ለወገን በመቆም፡-*** አስቴር ለወገኗ በንጉሡ ፊት ቆማለች፡፡ የእስራኤል ልጆች ከሞት የሚድኑበትን አዋጅ አሳውጃለች፡፡ አስቴር በጾም ሕይወቷም የተመሰከረላት ታላቅ ሴት ናት፡፡ (መጽሐፈ አስቴርን ይመልከቱ)

***፭. በጸሎት ሕይወት፡-*** በጸሎት ሕይወት ራሔልና የሳሙኤል እናት ሐና የታወቁ ናቸው፡፡ ኤር. ፴፫÷፲፭-፳ ፩ሳሙ. ፩÷፲፪-፳፰፡፡ የሐና ጸሎት አስተማሪ ስለሆነ በቀለመወርቅ ተከትቦአል፡፡ ፩ሳሙ. ፪÷፩-፲፩፡፡ እመቤታችን ማርያም በጸሎት፣ በትህትና፣ በቅድስና፣ በእምነትና በምስጢር ጠባቂነት አርአያችን ናት፡፡

***፮. በቆራጥነት፡-*** ከብሉይ ኪዳን ባታሪኮች በቆራጥነት የምትታወቀው ሞአባዊቷ ቆንጆ ሩት ናት፡፡ ሩት ዋጋዋን ተምና የወጣች፣ ከሩት ጋር እስከመጨረሻው የተጓዘች፣ በቆራጥነት የበረከት ምድር ቤተልሔምን የተረገጠችና ቦኤዝን በማግባት የክርስቶስ ቅድመ አያት የሆነች ታላቅ ሴት ናት፡፡ (መጽሐፈ ሩትን ይመልከቱ)

***፯. በብልሃት፡-*** ሴቶች ብልህ ናቸው፡፡ ሴቶች ከወንድ የተሻለ ተፈጥሮአዊ ጥበብ አላቸው፡፡ በአንድ ወቅት የእስራኤል ሰላዮች ኢያሪኮን ሊሰልሉ በገቡ ጊዜ በረዓብ ቤት አረፉ፡፡ የንጉሡ መልእክተኞች ሰምተው የእስራኤልን ሰላዮች ሊማርኩ መጡ፡፡ ረዓብ ግን በጓዳ ደበቀቻቸው፤ እንጀራ በሰገነቱ ደፍታ "መጥተው ነበር፤ እንጀራ በልተው፤ በዚህ ወጡ፡፡ ወዴት እንደሄዱ አላውቅም" አለቻቸው፡፡ በዚህም ብልሃት የእስራኤል ሰላዮችን ከሞት አዳነች፤ ስለዚህ ውለታዋ እርስዋም ከሞት ዳነች፡፡ ኢያ. ፪÷፩-፳፩፣ ዕብ. ፲፩÷፴፩፡፡

***ባልን በማክበር፡-*** እግዚአብሔርን በመፍራትና ባሏን በማክበር የተመሠከረላት የጽናት አርአያ እናታችን ሣራ ናት፡፡ ሣራ በሁሉ ለአብርሃም የታዘዘችና በድካሙ ሁሉ ያበረታችው ታላቅ እናት ናት፡፡ መጻሕፍት ሴቶች ሁሉ ሣራን በእምነት እንዲመስሏት ያዛሉ፡፡ ኢሳ. ፶፩÷፪፣ ዕብ. ፲፩÷፲፩ እና ፩ጴጥ. ፫÷፮፡፡ እናታችን ሣራ ተስፋ የሰጠውን እግዚአብሔርንም በማመን አርአያችን ናት፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

በብሉይ ኪዳን ሴቶች በእኩልነት ከፍታ እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል፡፡ በዝማሬ፣ በፈራጅነት በትንቢት ጸጋ የተሾሙ፤ በጦርነት በጥበብ የተሞላ የጦር ጥበብ ያስተማሩና ታግለው የጣሉ፤ ለወገናቸው ጥቅም የኖሩ፤ በቆራጥነት፣ በጸሎት፣ በእምነት፣ በጾምና በብልሃት በግል ሕይወታቸው የተመሰከረላቸው ሴቶች ነበሩና፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች ከዛሬው ትምህርት ምን እንደተማሩ ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ዋቢ መጻሕፍት


- ሃብተማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም
- ሃይማኖተ አበው፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1986 ዓ.ም
- አባ መልከ ጼደቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ትምህርተ ክርስትና፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም።
- አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1974 ዓ.ም።
- ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓት አምልኮና የውጭ ግኝኙነት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም.
- ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና ዛሬ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም.
- ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1997 ዓ.ም።
- መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ መጽሐፈ ሐዲሳት ሠለስቱ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም
- ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም
- ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም)፣ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር፣ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2003 ዓ.ም
- ደረጀ ጅማ (መጋቤ አእላፍ)፣ ምን ያስጨንቃችኋል ክፍል ፪፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ዓ.ም።
- መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም
- ሐረገ ወይን ቸርነት፣ ሴትና አህያ፣ አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም።
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ዶ/ር)፣ ጠቅላላ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም
- ጎሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ መዝገበ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም


www.zeorthodox.org

- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1996 ዓ.ም።
- ቸርነት አበበ (መምህሩ)፣ የመጽሐፍ ቅድስ ጥናት፣ አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም
- H.G. Bishop Moussa@ The Characteristics of Orthodox Teaching@ Bishopric of Youth@ Harmony Press, 2007.
- H.G. Bishop Mouusa, An Introduction to the New Testament, Bishopric of youth, Dar EL Geel Press, 2001.
- H.G. Bishop Raphail, The Meaning of Miracles, Bishopirc of Youth, 2010.
- Sunday School Curriculum, Grade 1 to Grade 12. The Coptic Orthodox Diocese of The Southern USA.
- Sunday School Lessons, Class 1 to Class 10, E.O.T.C Latin America Diocese.
- በጠቅላይ ቤተ ክህነት። 2000 ዓ.ም። የኢትዮ. ኦርቶ.ተዋ. ቤ.ክ ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም። አዲስ አበባ ፣ ሜጋ ማተሚያ ቤት
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፤ ዶ/ር )። 2000። በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግዕዝ ቋንቋ ። አዲስ አበባ። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ
- የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። 1996 ዓ.ም። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ። ንግድ ማተሚያ ቤት።
- ጎርጎርዮስ(ብፁዕ አቡነ)። 1996 ዓ.ም። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ። አዲስ አበባ። ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።
- መሐሪ ትርፌ (በሊቀ ሊቃውንት)። 19 ዓ.ም። የጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው። አዲስ አበባ።
- ዳንኤል ተሾመ። 19 ዓ.ም። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮችና የትርጉም ስልቶች። አ.አ
- Pulpet ; 19 A.D; Bible commentary The Epistle of paul to the ROMAN;
- Tadros Yakob Malaty (Father); 2007-2008 A.D; The Epistle of Saint Paul to the Romans; Alexandria,Egypt.
- መብራቱ ኪሮስ (ዲያቆን)። አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ። የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ያልታተመ መማሪያ።

www.zoorthodox.org

- ጎርጎርዮስ (በብፁዕ አቡነ):: 1981 ዓ.ም:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ:: አዲስ አበባ::
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፤ ዶ/ር ):: 2001:: የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ 1ኛ እና 2ኛ:: አዲስ አበባ::
- Lule Melaku (Asst. Professor); 2010; History of the Ethi. Orthodox Tewahido Church; A.A ; Elleni p.p.plc.
- ሰሎሞን መላኩ(ዲያቆን):: 2001ዓ.ም:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት:: አዲስ አበባ:: ባናዊ ማተሚያ::
- Syrian Sunday school curriculum.
- Introduction to Coptic orthodox Church ; Father Tadros Y Malaty
- Ian Gillman,Hans-Joachim Klimkeit ; Christian in asia before 1500 ;
- ዜና ሐዋርያት
- ገድለ ቅድስት አርሴማ
- ሺኖዳ(ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ) ቅንዓት
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ.ክ ፤ ስንክሳር ፤ በትንሳኤ ዘጉባዔ ማተሚያ
- ያረጋል አበጋዝ (ዲ/ን):: ቅዱስ ዩሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ ፤ አዲስ አበባ
- በጌታቸው ኃይሌ(ፕሮፌሰር):: 1997 ዓ.ም:: የአባ ባሕርይ ድርሰቶች
- ዳንኤል ክብረት(ዲ/ን):: 1998ዓ.ም:: የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች:: አዲስ አበባ:: ሜጋ ማተሚያ ቤት::
- .........:: አዋልድ መጻሕፍት:: ሐመረ ተዋሕዶ::
- Douglas J.D and Tenney M.c (1987) New International BIBLE DICTIONARY. ZONDERVAN'S.Grand Rapids,MICHIGAN USA
- Holy Trinity College.(2004) Patrology: Holy Trinity College module/ unpublished./
- Malaty T.Y( Father)Patrology ;

www.zeorthodox.org

- Malaty T.Y( Father).(199). Tradition and Orthodoxy. Alexandria .Egypt.
- ማኅበረ ቅዱሳን፡፡ 2004 ዓ.ም፡፡ ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ የማዕረግ ቃል ማተሚያ ቤት፡፡
- ነገረ ማርያም
- Shenoda - Pope (1999). The Holy virgin Saint Mary. Cairo,Egypt.
- ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡፡ (1988) ወንጌል ቅዱስ ትርጓሜ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
- የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት መማሪያ ፤ ካናዳ
- ሺኖዳ ሰው ምንድነው ፤ በብጹዕ ወቅዱስ ፤
- ክርስቲያን አንትሮፖሎጂ
- ሺኖዳ (ብጹዕ ወቅዱስ ፤ አቡነ)፡፡ መንፈሳዊው ሰው
- John Mark (Father). 19 . Ascending the heights ; A lay man guide to the ladder of divine ascent
- አበራ (በሊቀ ጉባዔ ፤ አባ)፡፡ 1996 ዓ.ም፡፡ ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን፡፡
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)፡፡ 200 ዓ.ም፡፡ መሽኮርመምና ማሽኮርመም፡፡ በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡ ቅድመ ጋብቻ፡፡ በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ
- ተስፋ ገብረ ሥላሴ፡፡ 1988፡፡ መጽሕፍተ መነኮሳት፡፡ አዲስ አበባ
- ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት፡፡
- ጥዑመ ልሳን፡፡() ያሬድና ዜማው፡፡ አዲስ አበባ፡፡
- ሙሳ (ሊቀ ጳጳስ)፡፡ ወጣትነትና የቅድስና ኑሮ፡፡ በመምህር ወንድወሰን ሶርሳ የተተረጎመ፡፡


www.zeorthodox.org